# ራዕይ፡ ምዕራፍ አራት ክፍል 3

እናመሰግናለን ወንድም ኔቪል። አንተንም ጌታ ይባርክህ። እንደምን አደራችሁ፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች። ዛሬ ጠዋት ሁላችሁም እንዴት ናችሁ? ደህና እንደሆናችሁ፡ ተስፋ አደርጋለሁ። ኣሜን። እንደአጋጣሚ ሆኖ… ዛሬ ጠዋት እዚህ እንድንገኝ በሰጠነው አጭር ማሳሰቢያ ተሰብሰበናል፡ የዚህ ዋና ምክንያት… የጉዞዬ መርሃ ግብር ገና ስላልወጣና መቼ እንደምሄድ ስላልታወቀ ነው። ይህም ለቀጣዮቹ ስድስት ወራት የሚዋቀረው ከአሁን ይጀምራል፡ ስለዚህም፡ እንግዲህ፡ ዛሬ ጠዋት ጉባኤ ቢኖረን መልካም ነው አልሁ ምክንያቱም ከሄድኩበት ለመመለስ ረዘም ያለ ጊዜ ስለሚወስድብኝ ነው፡ እኔ እንደማውቀው፡ በመኸር ወራት እመለሳለሁ።

2 ይመስለኛል… አሁን በሚቀጥለው ሳምንት ወደ ቤውመንት፡ ቴክሳስ እንጓዛለን፡ በሚቀጥለው ሳምንት ከገለልተኛ ማሕበራት እና ከልዩ- ልዩ አብያተ-ክርስቲያናት ጋር እዚያ እንጀምራለን የሰምንት ወይም የአሰር——ቀናት ሰብሰባ እዚያ ውስጥ እናሳልፋለን። ከተወሰነ ጊዜ በፊት ይህ ፎቶ ግራፍ ከተነሣ በኋላ ብዙም ሳይቆይ **ታላቅ ጉባኤ** ባደረግንበት፡ በቤውሞንት፡ ቴክሳስ ውስጥ በሚገኘው **በጂሰስ ኔም**፡ አብያተ ክርስቲያናት ስፖንሰር የተደረገ ነው። ወደዚያም… ሲመጡ በፉርጎዎች እንደመጡ አውቃለሁ ባለ፡ ሃያ-ሰባት ፉርጎ፡ ይመስለኛል… ማለት ባለ ሃያ-ሰባት ፉርጎ ባቡር፡ ወደ ቤውመንት ጉባኤ ይዘው መጡ። በዚያም የከተማው ከንቲባ እና ሌሎቹ፡ በየጎዳናዎቹ እያለፉ የሰልፍ ትዕይንት ያደረጉበት ነበር። በቤውመንት ላይ ጥሩ ጊዜ አሳልፈናል፡ በሚቀጥለው ሳምንት ተመልሰን እንሄዳለን። ከዚያም ሳን አንቶኒዮ ይጠበቅብናል፡ ይሁን እንጂ ሰንመለስ ካልሆነ በቀር፡ በዚያ በቂ ጊዜ አይኖረንም።

3 ከዚያም ወደ ፊኒክስ፡ ሎስ አንጀለስ፡ እስከ ሎንግ ቢች ድረስ እንሄዳለን። እናም ጌታ ቢፈቅድ፡ ወደ ምሰራቅ ዳርቻዎች ተመልሰን፡ ወደ ቨርጂኒያ እና ደቡብ ካሮላይና እናልፋለን። ያን ጊዜ ወደ ብሉሚንተን፡ ኤሊኖስ እንመለሣለን። እና ከዚያ ወደ ሌን ቴክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፡ ባለፈው ሳምንት በሚያዝያ ወር፡ ወደ ክርስቲያን ቢዝነስ ሜን። ከዚያ ተነሰቼም ወደ ሰሜናዊ ብሪቲሽ ኮሎምቢያ፡ ወደ አላስካ እጓዛለሁ፡ በዚያም እስከ ሰኔ ድረስ እቆያለሁ። በዚያም፡ ጥሩ ጊዜ እንደሚኖረን፡ ተስፋ አደርጋለሁ።

4 እስከዚያ ድረሰም ሰለዚህች ቤተ ክርስቲያን በተመለከተ… ላለፉት ጥቂት ወራት ሰመረመር የቆየሁበትን፡ የገቢ ግብር ምርመራ ጉዳይ፡ እንዲጠናቀቅ እንጸልያለን። ከዚያ በኋላ እንዲህ እናደርጋለን… ምናልባት በሰኔ ወር፡ ወደ ባሕር ማዶ ጉዞ አደርጋለሁ፡ በቀጥታ ወደ አፍሪካ ይሆናል፥ ሰኔ፡ ሐምሌ፡ እና ነሐሴ፡ በ——በአፍሪካ እቆያለሁ። ስለዚህ ጸሎታችሁም በእርግጥ ያስፈልገኛል።

5 እንግዲህ የጌታን መምጣት እየጠበቅን ነው። ይህ ሁሉ የሚሆነው “የጌታ ፈቃድ ከሆነ ብቻ ነው፡” እያችሁ። እና እናውቅም፡ ሊመጣም ይችላል… እነዚህ ቀጥተኛ ምሪቶች አይደሉም፡ ግብዣዎችን አንድ ላይ አጣምረን ጸለይንበትና፡

“የት የት መሄድ አለብን፡” ብለን ጌታን ጠየቅን? እና—ይመስለኛል፡ እንግዲህ፡ ሁሉንም ለራሴ ብቻ አልተውም፡ ሌሎች እንዲያስቡበት፡ እንዲጸልዩበት አደርጋለሁ። በዚህ ጊዜ ሁላችንም ወደ ምዕራብ፡ ወደ ደቡብ እና ምዕራብ እንድንሄድ የተመራን ይመስለኛል። ስለዚህ በዙሪያችን ግብዣዎች ስለነበሩን፡ በዚህ መልኩ ጀመርን። እና በልቤ ላይ የመጣብኝ የመጀመሪያ ቦታ ቤውሞንት ወይም ሳን አንቶኒዮ ነበር። ስለዚህ አየነውና፡ በሁለቱም ቦታዎች ግብዣዎች ነበሩን። ስለዚህ...

6 በቦሞንት ውስጥ አንዱን ጠራን። ከዩናይትድ ጴንጤቆስጣል እና ከሌሎች የተውጣጡ አርባ-ሁለት አብያተ ክርስቲያናት፡ በአንድነት ተባብረው ያሉበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ፡ ትልቅ አዳራሽ ይዘን ለሁለቱም ቦታዎች አምስት አምስት ከማካፈል ይልቅ አስር ቀናት ብንሰጣቸው ይሻላል ብለን አሰብን። እንዲህ ማማከል ይሻላል ብዬ አሰብኩ። ስለዚህ፡ በቤውመንት እና ነዳጅ በሚገኝበት የቴክሳስ ወረዳዎች ዙርያ—ብዙ ችግረኞች አሉ፡ ስለዚህ በቤውመንት ጥሩ ጊዜ ይኖረናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

7 እና፡ አሁን፡ ትልልቅ ማዕከሎች እና ትላልቅ ቦታዎች ባሉበት ለመሄድ በጭራሽ አንሞክርም። ነገር ግን ምንም ያህል ትንሽም ይሁን ትልቅ፡ ጌታ ወደሚመራን መንገድ፡ ለመሄድ እንሞክራለን። እንግዲህ፡ በማንኛውም ጊዜ፡ **የመቄዶንያ** ጥሪ ሊደርሰን ስለሚችል በማንኛውም ጊዜ እርሱ ወደሚጠራን ማንኛውም ነገር ለመሄድ፡ በየትኛውም ጊዜ መሰኩን መተው እንችላለን።

8 እናም በዚህ በእግዚአብሔር ቃል ዙሪያ ከናንተ ከመልካም ሰዎች ጋር የመገናኘት ጊዜው በእውነት ተባርከንበታል። አሁንም ከዚህ ታማኝ ሰው ወንድም ኔቪል ጋር ታማኝ ሆናችሁ ወደ ቤተክርስቲያን እንደምትመጡ ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትም እንደምትታዘዙ አምናለሁ፡ ታማኝ በሆነው በጌታ እግዚአብሔር ባሪያ ነው ብዬ፡ እጅግ አድርጌ እደግፈዋለሁ፡ በየጊዜውም በእግዚአብሔር ነገር ላይ እጅግ እያደገ ነው፡ በዚህም ደስ ይለኛል።

9 እናንተም ትንሿ ቤተ ክርስቲያን ሆይ፡ በእግዚአብሔር ጸጋ ታድጉ ዘንድ በጌታ በኢየሱስ ስም እመክራችኋለሁ፡ ተግታችሁ ዘወትር ወደ ቀራንዮ እየተመለከታችሁ፡ እግዚአብሔርም በማንኛውም ጊዜ እንዲጠቀምባችሁ፡ ከልባችሁ እና ከነፍሳችሁ መራራውን ሥር ሁሉ አሰወግዱ። የሆነ ነገር ለማድረግ ሲሰማችሁ፡ ወይም ራዕይ ወይም ማስጠንቀቂያ ወይም የሆነ ነገር፡ በሚገርም ሁኔታ ወደ እናንተ ቢመጣ፡ ተጠንቀቁ! ሰይጣን በቻለው ሁሉ ክፉ እና ተንኮለኛ ነው። አያችሁ? በእግዚአብሔር ቃል መርምራችሁ ከፓስተራችሁ ጋር ተማከሩ። አያችሁ?

10 እና ስጦታዎች እና የመሳሰሉት ነገሮች ወደ ቤተክርስቲያን ዘልቀው ሲገቡ፡ እና የስጦታዎቹ አሰራር ታያላችሁ። ወደ ስራ ከማስማራታችሁ እና ከማስቀጠላችሁ በፊት፡ አስቀድማችሁ... ልባችሁ እስኪሞላ ድረስ ጠብቁ... እንግዲህ፡ ጠላት ተንኮለኛ ነው። አያችሁ? አብያተ ክርስቲያናትን በየጊዜው የሚበጣጥሱት፡ እውነተኛ ስጦታ በተሳሳተ መልኩ ሲሰራ ነው። አያችሁ? እግዚአብሔር አንዳች ነገር ማድረግ ይፈልጋል፡ በተሳሳተ መንገድ ይደረጋል፡ ይህ ማለት—በቀላሉ... ይጎዳችኋል ብቻ ሳይሆን፡ መላውን ቤተ ክርስቲያን ያፈርሳል። አያችሁ? አማክሩ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለውስጥ ፈትሹት፡

ከዚያ በኋላ ከእግዚአብሔር ዘንድ መሆኑን እና አለመሆኑን መርምሩት እዩትም። ምርመራውን እና ፍተሻውን ቀጥሉበት፡ በቃሉ ዘንድ እና በሐረጉ ዘንድ ፍጹም ትክክለኛ መሆኑን እዩ። ያን ጊዜ ደህና ትሆናላችሁ፡ አያችሁ።

11 ቃሉ እንዲህ ይሆናል፡ በዚህ መንገድም ይሰራል እስካለ ድረስ፡ አጥብቃችሁ ያዙ። ማንም ሰው ምንም ቢያደርግ፡ ምንም እውነት ቢመስልም፡ መቼም ቢሆን አትናወጡ። ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የማይስማማ ከሆነ፡ ተዉት። ሰይጣን በተቻለው ሁሉ እያታለለ ባለበት በመጨረሻ ዘመን ውስጥ ነንና፡ በማንም ምክንያት አታድርጉ።

12 አለቃ ለመሆን በመሞከሬ ይቅርታ አድርጉልኝ፡ አለቃ አይደለሁም። ነገር ግን ጳውሎስ በአንድ ወቅት ስለ ጉባኤው "የአክሊሌ ውስጥ ኮከቦች ናችሁ፡" ብሎ እንደተናገረ ለእናንተም እንዲሁ ይሰማኛል። ከአድማስ ማዶ ወዳለው ምድር ስሻገር፡ በዚያም በከበረው ሁኔታ ውስጥ ሳገኛችሁ፡ በአክሊሌ ውስጥ እንዳሉ ከዋክብት አብርታችሁ እንድትቆሙ እፈልጋለሁ። አያችሁ? እና እኔ—እዛ እንድትገቡ እፈልጋለው፡ እኔም መግባት እፈልጋለሁ።

13 የጌታን መገኘት ወይም ህዝቡንም፡ በዚያች በከበረች ምድር በራዕዬ ባየሁት ጊዜ ትዝ ይለኛል፡ ዙርያውን እየሁና፡ እንዲህ አልኳቸው... እነርሱም እኔ በሰበኩኩት ወንጌል መሰረት አስቀድሞ እኔን እንደሚፈርደኝ ነገሩኝ። እኔም "ጳውሎስ እንደሰበከው ነው፡" አልኳቸው!

14 በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችም በታላቅ ድምጽ "እኛም በዛ ላይ አርፈናል፡" አሉ! አያችሁ? አያችሁ። ስለዚህ፡ እንዲሁ እንዲሆን እፈልጋለሁ። እና አንድ ቀን እዚያ እንገናኛለን።

15 እና እግዚአብሔር እኔን እና ወንድም ኔቪልን አለቃ እንድንሆን አልላከንም፡ በጭራሽ። እኛ ወንድሞቻችሁ ብቻ ነን፡ አያችሁ፡ የወንጌል አስተማሪዎች ነን። ስለዚህ ሁላችንም አብረን እንስራ።

16 አንዳንድ ጊዜ የ—የሚሰራ ነገር ከተነገረ ወይም—ወይም አንድ ነገር ከተባለ፡ ከተነገረ ወይም በዚያ አካሄድ አንዳች ነገር ከተተቸ፡ ባለ ስጦታውም ካልተቀበለው፡ ይህን አስታውሱ... ካልተቀበለው፡ አስታውሱ፡ ስጦታው ልክ አልነበረም። በመጀመሪያም እግዚአብሔር አልነበረም። የእግዚአብሔር መንፈስ ሁል ጊዜ ለመታረም ዝግጁ፡ መልካም እና ትሁት፡ ፈቃደኛም ነው። አያችሁ። "ምንም ይሁን አደርጋለሁ፡" በማለት ከቀጠለ፡ አንዳንዴ እንዴት እንደሆነ ታውቃላችሁ... ይህን አስታውሱ፡ ግትር መናፍስት የእግዚአብሔር አይደሉም። አያችሁ? ስለዚህ ምድር ሁሉ፡ በእግዚአብሔር ክብር ተሞልታ ሳለች፡ ሌላ መተካት ለምን ያስፈልጋል፡ አያችሁ፡ በእውነተኛ የእግዚአብሔር ኃይል ተሞልታለች። ሌላ መተካትስ ለምን ያስፈልገናል? ቀኑ ረፍዶብናል፡ ግን፡ አስታውሱ፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር እንደ ምን ይመጣል ብሏል... የቻለውን ያህል ተንኮለኛ በመሆን፡ ቢቻለውስ የተመረጡትን ለማሳት ነው። አያችሁ?

17 እና፡ አሁን፡ አንዳንድ ጊዜ የተመረጥን ነን ብለን እናስባለን፡ እንደሆንን ተስፋ አደርጋለሁ፡ ግን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በትክክል እንኑር። ከዚያም ሁሉም ነገር በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በቅደም ተከተል፡ ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር ትክክል በመሆን፡ ለእግዚአብሔር ክብር ለቤተ ክርስቲያንም ሞገስ፡ የሚያመጣ ከሆነ፡ መጽሐፍ ቅዱስ ስለሚደግፈው ከእግዚአብሔር

ዘንድ እንደሆነ እናውቃለን። የእኛ ጽንሰ ሐሳብ ግን አይደግፈውም፡ ምንም አይጠቅምም፡ ይወድቃል።

18 ስለዚህ አንድ ነገር ሲመጣብን፡ ምንም እውነት ቢመስልም እንኳ፡ ልክ ካልሆነ፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ካልሆነ፡ አሁኑኑ አስወግዱት፥ ምክንያቱ የሚጠብቃችሁ እውነተኛው—አለ፡ አያችሁ።

19 ስለዚህ፡ አሁን ጸልዩ። በምታደርጉት ሁሉ፡ ዘወትር፡ ስለ እኔ ጸልዩ። ጸልዩልኝ፡ ምክንያቱ መስኩን የምናጠቃው ለመጨረሻ ጊዜ ይመስለኛል። አሁን እነወጣለን...

20 እና፡ ታላላቅ ነገሮች እየተከናወኑ ናቸው፡ በአለም ዘንድ የማይታወቁ መሆናቸውን፡ አስታውሱ። ኢየሱስ መጣ፡ ኖረ፡ ሞተ፡ እና መስዋዕትነት ከፍሎ፡ ወደ ክብር ተመለሰ፡ ሚሊዮኖች ስለሱ ምንም እንኳን አያውቁም። አያችሁ? በአበባ ያጌጠ፡ ታላቅ፡ ትልቅ አልነበረም፡ ብቻ "የራሱ ወደ ሆኑት መጣ፡" አያችሁ። ስለዚህ... "መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን፡ ጆሮ ያለው ይስማ።" በውጭ ላሉት ሳይሆን፡ "ለቤተ ክርስቲያን።" የምትቀሰቀሰው ቤተክርስቲያን ናት።

21 አንድ ቀን እሱ እኔን እስከተናገረኝ ቀን ድረስ በሌላ መልኩ አስብ ነበር፥ ወደ ቃሉ ተመልሼ ዮሐንስ በመጣ ጊዜ የሚሆነው ነቢያት ሁሉ እንዴት እንደተናገሩ መለስ ብዬ እንዳስብ አደረገኝ፡ እንዲህ በማለት፡ "ኮረብቶች ዝቅ ይላሉ፡ ሸለቆውም ሜዳ ይሆናል።" የእግዚአብሔር ኃይል እንዴት እንደሚሰራ ሁሉ! እና ኮ—ኮ... "ኮረብቶች እንደ አውራ በግ ይዘላሉ፡ ቅጠሎችም ያጨበጭባሉ።" እና፡ አንድ የተለየ ነገር ለመሆን የተዘጋጀ ይመስላል። አያችሁ? በመጣ ጊዜ ግን፡ ምን ሆነ? ጺሙ እስከመጨረሻ ድረስ ያሳደገ፡ ያረጀ የበግ ለምድ ሰውነቱ ላይ የጠመጠመ ምስኪን ሰው ከምደረ በዳ ወጣ። በምድረ በዳ ውስጥ ምንም ሞቾት አልነበረም። ከዘጠኝ ዓመቱ ጀምሮ እዚያ ይኖር ነበር፡ አሁንም ሰላሳ አመቱ ነበር፡ በቆራጥነት፡ ከምድረ በዳ ወጥቶ መጣ፡ ምናልባትም፡ በዮርዳኖስ ዳርቻዎች፡ እስከ ጉልበቱ ድረስ ጭቃ ላይ ቆሞ፡ ንስሐን ሰበከ። ኮረብቶች ዝቅ ያሉት፡ ሸለቆውም ሜዳ የሆኑት ያኔ ነበር። አያችሁ? ይህ ማለት...

22 መንፈሳዊ ግንዛቤ ሊኖራችሁ ይገባል። አስታውሱ፡ እግዚአብሔር በዚህ ምድር ላይ፡ በውበት ኖሮ አያውቅም፡ ወደፊትም አይኖርም። አይደግፍም። በጭራሽ... ታላላቆቹ መልእክቶች "**እከሌ-እና-እከሌ** ወይም **እከሊት-እና-**... " የሚባሉትን በጭራሽ አያደርጉም በዚያ ዓይነት መልኩ አይሰራም። አገልጋዮቹ በዚህ መንገድ አይሠሩም። ውበቱና ክብሩ ከላይ ነው።

23 ትላንትና፡ ወይም ከሁለት ቀናት በፊት፡ በኬንታኪ ውስጥ፡ ከጥሩ ጓደኛዬ ከወንድም ባንክስ ዉድ ጋር፡ ወደ ኬንታኪ እየተጓዝን፡ አንዲት ፖሊስ መንገድ ላይ ቆማ ነበር፡ እና እንዲህ አለ፡ "ጓዴ፡ ፍጥነት ብንቀንስ ይሻላል፡" "ከባድ ሰው ናት፡" አለኝ።

24 እኔም "አዎን፡ ልክ ነህ፡" አልኩት። ከዛ እንዲህ አልኩት፡ "ሚልዮኖች ቅጥረኛ ሰራተኞች ባሉባት አንዲት አገር ሴቶችን እያመጡ፡ የፖሊስ መኪና እንዲነዱ በማድረግ፡ እና ፖሊሶች እንዲሆኑ በማድረግ ሲያስማሯቸው፡ በሀገራችን ላይ ካሉት ከባባድ እድፈቶች አንዱ ነው።" ልክ የ—የቀለጠ ግሪስ በሞላበት እንሥራ ውስጥ እንደገባች ጥንቸል ፋይዳ ቢስ ስራ ውስጥ

እንደመግባት ነው። አያችሁ? እንደው በቃ—በቃ—ሰፍራዋ አይደለም። አልኩትም፡ “ይህ ነገር እጅግ ያሰጨንቀኝ ነበር፡ አሁን ግን ይህን ማስታወስ ጀምሬአለሁ፡ ‘ምክንያቱ፡ ምንም አይገርምም፡ ይህ—መንግስታችን ይህ አይደለም፡ ከዚህ ዓለም አይደለንም።’” በእነርሱ ዘንድ... ያለ ነገር...

25 ሴቶች (ሴቶቻችን) ለምን—የእነርሱን ቁምጣዎች፡ ሜክ አፖች፡ እና ሮክ-ኤንድ-ሮል፡ እና ኮተታቸው ሁሉ አይለብሱም? ምክንያቱ፡ ሰዎች ወደ ተራ ቸርቾች እና ወደ ሌሎች ስለሚገቡ፡ “ምንም ማለት አይደለም፡” ብለው ያስባሉ። ለምን? እ... እ—አሜሪካውያን ናቸው፡ ሁሉም አሜሪካውያን ናቸው፡ አሜሪካዊ መንፈስ አለባቸው። እኛ አሜሪካውያን አይደለንም፡ ክርስቲያኖች ነን። አኗኗራችን... መንፈሳችን የሌላ መንግሥት በመሆን ነው። መንፈሳችን የዚህ መንግሥት ቢሆን ኖሮ በእነዚህ ነገሮች እንስግድ ነበር፡ ከዚያም እነዚህን ሁሉ ጸያፍ ዘፈኖች እና ሮክ-ኤንድ-ሮል ባመለክን ነበር። “ገንዘብህ ባለበት፡ በዚያ ልብህ ይኖራል።” ገንዘባችን በሰማይ ነው። ሰለዚህ ወደ መንግሥት እየተጓዝን ነን።

26 ይህ ቤታችን አይደለም፡ እዚህ የምንኖረው ሌሎች ዜጎችን ከጨለማ ለማውጣት እየሞከርን ነው። እና ወደ አንዲት ከተማ ገብቼ፡ ምናልባት አንድ ድንቅ እና ብቸኛ-ነፍስ በሆነ ቦታ ላይ ተቀምጦ ለማግኘት ለአንድ ሳምንት፡ ወይም ለአስር ቀናት፡ ስለ አንዱ፡ ከተማ አቀፍ ዘመቻ በማድረግ እርሳለሁ።

27 “ጉባኤው ድንቅ ነበር፡ አምስት ሺ ወደ መሰውያው መጡ፡” ማለት ትችላላችሁ፥ ማናቸውም፡ አንዳቸውም ላይድኑ ይችላሉ። አያችሁ? እንዲህም ሊሆን ይችላል... “ወደ መሠዊያው የመጡት ሁለት ሰዎች ብቻ ነበሩ፡” ብላችሁ ታስቡ ይሆናል፡ ከሁለቱ ምናልባት አንዱ ብቻ ጌጥ ይሆናል። እኛ በውኃው ዳር መረባችን እንጥላለን። ዓሣውን የሚመርጠው እግዚአብሔር ነው፡ የትኛው ዓሣ እንደሆነ እና እንዳልሆነ ያውቃል።

28 ስለዚህ፡ አያችሁ፡ እኛ ዝም ብለን እንሰብካለን። እናንተም በዚህ ተበርናክል ውስጥ የምታደርጉትም ያው እንደሆነ አስታውሱ። ነገር ግን ዘወትር ይሄን አትርሱ፡ “በጎቼ ድምጼን ያውቃሉ።” የእግዚአብሔር ድምጽ ማለት ቃሉ ነው።

29 በቀደም እንዲህ አይነት ነገር የለም ብለው ስለሚናገሩ አንዳድንድ ሰዎች እያሰብኩ ነበር... አንዳንድ የኢብያተ ክርስቲያናት የእምነት ተቋማት እንዲህ ይላሉ፦ “መለኮታዊ ፈውስ ልክ አይደለም። ከቅዱስ ጳውሎስ ወይም ከሐዋርያት በቀር በሰገነት ላይ ከነበሩት ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት በቀር፡ የመለኮታዊ ፈውስ ስጦታ ለማንም አልተሰጠም። እነሱ የመለኮታዊ ፈውስ ስጦታ ተሰጥቷቸዋል፡ ያኔ አበቃለት። ይኸው ነው።”

30 ነገር ግን፡ ወንድም ዊሊ፡ እዚህ፡ ለእኛ በሚያስደንቅ ሁኔታ ባዘጋጀልን በዚህ አስደናቂ ቻርት፡ ማየት ትችላላችሁ፡ ያቺ ትንሿ ፈትል ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በኢብያተ ክርስትያናቱ ሁሉ ተሸጋግራለች። እኔ የሚገርመኝ ያው የእምነት ተቋም ስለ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፡ ስለ ኢሬኔዎስ፡ ስለ ቅዱስ ማርቲን ምን ይላል ነው? ሐዋርያት ካረፉ ከመቶዎች አመታት በኋላ፡ በዘመናት ሁሉ የነበሩ እነዚያ ሰማዕታትስ፡ በልሳን ተናገሩ ድውያንን ፈወሱ ሙታንን

አሰነሱ ተአምራትን አደረጉ፡ መላ ቤተ ክርስቲያን። ለሐዋርያቱ ብቻ ቢሆንስ፡ ስለ እነርሱስ?

31 ምን ያህል ጠባብ እንደሆነ ተመልከቱ? መንፈሳዊ ግንዛቤ የላቸውም፡ ያ ነው። አያችሁ፡ “እውር! በኃጢአት እና በመተላለፍ የሞቱ!” **ኃጢአት** ማለት “አለማመን” ማለት ነው። በአለማመን ውስጥ ያለ ማንኛውም ነገር ኃጢአት ነው። አንድ ሰው **ይሄን** ያህል—ረዘም ያለ ሹመት ኖሮት (ዲ.ዲ.፣ ደብል ኤል.፣ ፒኤች.ዲ.፣ ኤል.ኤል.ዲ።) “መለኮታዊ ፈውስ ወይም የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የሚባል ነገር የለም” ባይ ከሆነ፡ ሰውየው በኃጢአት ሞቷል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሁሉንም ዓይነት ምስጢራትን ማብራራት ይችል ይሆናል፡ ህይወቱ (ምስክርነቱ) ግን መሞቱን ያረጋግጣል። ኃጢአተኛ ነውና በኃጢአት እና በመተላለፍ ሞቷል።

32 ኃጢአት አለማመን ነው። ሰው ሁሉ ይረዳ... ኃጢአት፡ ዝሙት መፈጸም ሲጋራ ማጨስ እና መደነስ እና—እና የመሳሰሉ ነገሮች አይደለም። ኃጢአት ያ አይደለም፡ ያ’ማ የአለማመን መገለጫ ነው። አማኝ—ግን... አንድ ሰው ምንም ባይጠጣ፡ ባያጨስ፡ እነዚህን ነገሮች ባያደርግ፡ ክፉ ቃል ባያወጣ፡ አስሩ ትዕዛዛት ሁሉ ቢጠብቅ፡ እልም ያለ ኃጢአተኛ ሊሆን ይችላል፡ እያችሁ፡ ከመጠን በላይ ክፉ ሊሆን ይችላል። የእግዚአብሔርን ኃይል የሚክድ ከሆነ፡ ኃጢአተኛ ነው! **ኃጢአት** የሚለው ቃል “አለማመን” ነው። አሁን፡ ልክ እንደሆነ እና እንዳልሆነ፡ መርምሩት። በእግዚአብሔር ቃል የማያምን ሰው፡ ኃጢአተኛ ነው ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባት አይችልም።

33 አሁን፡ ኦህ፡ በጌታ ፈቃድ በመንፈስ ቅዱስ ትእዛዝ፡ ዛሬ ማለዳ እንደገና ወደ ተበርናክሉ እንድትመጡ፡ እና ምናልባት ሁላችሁንም፡ ሁለት ወይም ሶስት ሰዓት እዚህ እንዳስጠብቃችሁ ብዬ አሰብኩ። ከመሄዴ በፊት ግን የራዕይ መጽሐፍ 4ኛውን ምዕራፍ መጨረስ እፈልጋለሁ። አሁንም አድካሚ እንደማይሆንባችሁ ተስፋ አደርጋለሁ፡ ክብር እንደሚሆንላችሁ—ተስፋ አደርጋለሁ። በሚቀጥሉት ቀናት በደንብ የሚጠቅማችሁ እና የሚረዳችሁ ነገር እንደሆነ ተስፋ አደርጋለሁ።

34 አሁንም ምናልባት... እኛ ስለምንሄድ በመካከላችን እንግዶች ሊኖሩ ይችላሉ ብዬ ቢሊን ዛሬ ጠዋት እዚህ እንዲወርድ እና የጸሎት ካርዶችን እንዲሰጥ ነገርኩት፡ እና... አሁንም፡ መቼ እንደምንመለስ አላወቅኩም። እግዚአብሔር ብቻ ነው የሚያውቀው። ምናልባት የመጨረሻው ስብሰባ ከሆነ... እንዲሁ እንዲሆን ፈልጌ ነበር... እሱ በደወለልኝ በ—በዘጠኝ ሰዓት ገደማ ግን እንዲህ አለኝ፡ “አባዬ፡ ጸሎት ፈልገው የመጡ አንዳንድ ሰዎች አሉ። እኔም ጠይቄአቸዋለሁ፡ ግን” አለኝ፡ “እነዚህ ሰዎች—ወደ ቤተ ክርስቲያን በተደጋጋሚ የሚመጡ ሰዎች ናቸው።”

35 እኔም “እንግዲያውስ፡ የጸሎት ካርዶችን እንዳትሰጥ፡” አልኩት። እንዲህ አልኩት፡ “ምክንያቱ እነዚያን ሰዎች... ምናልባት ዛሬ ለበሽተኞች የምንጸልይ ከሆነ፡ እነዚያን ሰዎች ጠርተን እንጸልይላቸዋለን።” ነገር ግን “ወደ ተበርናክሉ የመጡ ሰዎች—የምናውቃቸው ከሆነ ግን... አቆየው፡ እኔ የፈለግኩት እንግዶችን ነው፡” አልኩት።

36 ከዚያ በኋላ፡ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት እዚያ ቆሜ ሳለሁ ወደዚያ መጣና፡ “በቃ፡ ጥቂት የጸሎት ካርዶችን ሰጥቻለሁ፡” አለኝ። “በዚህ አካባቢ፡ ጥቂት

የጸሎት ካርዶች ብቻ ሰጥቻለሁ፡” አለኝ። “አንተም የተሰማህን ማድረግ ትችላለህ፡” አለኝ።

37 እኔም አልኩት፡ “እሺ፡ የመልእክቱ ሁኔታ በማየት፡ ምን ላይ እንደደረስን አውቀን፡ እንቀጥላለን። እ… ”

38 እርሱም አለኝ፡ “መቼም፡ እርግጥ ነው፡ ብዙ ሰዎች የጸሎት ካርዶቹን ፈልገው ነበር፡ ግን” አለኝ “ሰዎቹ የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ናቸው።” አያችሁ?

39 እንግዲህ፡ እግዚአብሔር አምላክ እንደሆነ እናውቃለን። እና፡ የሚያደርጋቸውን ነገሮችም፡ ያስገርማሉ! ለምን፡ ሰ—ሰልኩ ሁል ጊዜ ይጮኻል፡ የተለያየ ነገር ያላቸው ሰዎች ይደውላሉ፡ አንዳንድ ጊዜም ስለ ጥቃቅን ነገሮች፡ እግዚአብሔር ግን እንዴት ጸሎትን እንደሚመልስ!

40 በቀደም ከሌሊቱ አሰራ ሁለት ወይም አንድ ሰዓት ላይ ከኒው አልባኒ የመጣች ምስኪን ሴት ወይም ባለቤትዋ፡ በሳምባ-ምች ምክንያት፡ ትን ያለው ህጻን ልጅ ይዘው፡ ወደ ቤቴ የመጡ ሰዎች፡ እዚህ ይኖራሉ ብዬ አሰባለሁ? እዚያ ጋር፡ እሺ። ልጁ እንዴት ሆነ? [ያ ወንድም “በጎ ነው፡” አለ።—እርታዒ።] እሺ፡ መልካም፡ በጣም ጥሩ።

41 እንደው እስኪ ላሳያችሁ፡ አያችሁ፡ ይህ የማትረዱት ነገር ነው፡ መንፈስ ቅዱስ ሲናገር የማይታዘዝ የለም። ፍሬድ ሶትማን፡ ውድ ወንድማችን፡ ፍሬድ፡ ከጥቂት ጊዜ በፊት፡ “አሜን፡” ሲል ሰምቼዋለሁ፡ የት እንዳለ ግን ማወቅ አልቻልኩም። የት አለ? አለ እዚህ? ይኸው፡ እዚህ አለ፡ ወንድም ፍሬድ ሶትማን። እጅግ ቀላል መሆኑን ለማሳየት… ከእሱ ጋር የመጡ አንዳንድ ወዳጆች ነበሩት፡ እኔ አላውቅም፡ እነ ወንድም ዌልች ኢቫንስ፡ ይመስሉኛል። ተጎታች ይዘው ነበር፡ በሮቹን ቆላለፉት እና ፍሬድ ቁልፎቹን ጣለ፡ በሁሉም ቦታ ፈልጎ የትም ሊያገኛ አልቻለም። እና ወንድም ዌልች ገና እየመጣ ነበር። እና የመድረሻው ቀን ደረሰች እና፡ ቁልፋን የትም ሊያገኙት አልቻሉም፡ ስለዚህ ወደ ቤት ደውሎ፡ እንዲህ አለኝ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ቁልፎቹ የት ነው ያሉት? የት እናገኛቸዋለን? ”

42 አሁን፡ አንድ ሰው እንዲህ አይነት ጥያቄ ሲጠይቅ፡ አንዳንዶቻችሁን ሊያደናቅፍ ይችላል። እስቲ አንዴ ቆይ፡ የእሴይ ልጆች አህዮችን ፍለጋ እንደወጡ ታስታውሳላችሁ? “እጅ መንሻ በእጄ ቢኖረኝ ኖሮ፡ ወስጄ በሰጠሁት… በጠየቅኩት፡ ለነብዩ በሰጠሁት ነበር፡ ምናልባት አህዮቹ የት እንዳሉ ይነግረን ነበር።” ያንን ትዝ ይላችኋል?

43 በመንገድ ላይ ሲሄዱ ሳሙኤል ነቢዩን አገኙት። እርሱም “አህዮችን እየፈለጋችሁ ነው፡” አላቸው። “በሉ፡ ወደ ቤታችሁ ተመለሱ፡” አላቸው፡ “ተገኝተዋልና፡” አላቸው። ልክ ነው?

44 እኔም ጸለይኩላቸው። ከዚያም ፍሬድ ወጣና ሄዶ ቁልፎቹን አገኛቸው። በቃ። አያችሁ?

45 ወንድም ኤድ ደልተን፡ የት ነህ? ኤድ ደልተን የት አለ? የሆነ ቦታ እንዳለ አውቃለሁ፡ ቀደም ሲል አይቼዋለሁ። ኦህ፡ ያውና… ከኋላ አለ። በኢንተርኮም ወይም በመገናኛ ዘዴ ሰምቶኛል። በቀደም ማታ ሰልክ ተደወለ እና ወንድም ኤድ ከባድ ችግር ውስጥ ገባ። እኔም ልረዳው ፈለግኩ። “አይ፡” “ከእግዚአብሔር

እንድትጠይቅ እፈልጋለሁ፡” አለኝ። እኔም እርዳው ብዬ ጌታን ጠየቅኩት። እና በሚቀጥለው ቀን ሚሰቱ ደወለች፡ እነሆ አንድ ሰው ሊታደጋቸው መጣ። እሺ። ልክ ነው፡ ወንድም ኤድ?

46 እያችሁ፡ እሱ አምላክ ነው። በቃ፡ አምላክ ነው። እያችሁ፡ እሱ... በየትኛውም ጊዜ ያለማቋረጥ ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ፡ ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ያው ነው። ምንም ችግር ቢያጋጥም፡ እርሱ አምላክ ነው። ስለ እነዚህ ነገሮች እየጎረርን፡ መዞር አያስፈልግም፡ ያንን ማድረግ የለብንም። ቀኝ እጅ የሚሰራውን ቀኝ እጅ ወይም የግራ እጅ እንዲያውቅ አትፍቀድ። በመካከላችን እናወራዋለን በየቦታው ግን ጥሩምባ አንነፋም። ይህ ማለት፡ “እግዚአብሔር በአንድ ሰው ብቻ ያደርጋል፡” እንደማለት የራስ-ትምክህት ነው። እርሱ ለ—ለሚያምነው ለማንም ሰው ያደርግለታል። አመኔታ ነው፡ እምነት! ምንም—ምንም ማድረግ ብትፈልጉ፡ አሳባችሁ ምንም ይሁን፡ ወደ እግዚአብሔር አቅርቡት። እ—እ—እ—እሱ ራሱ ሁሉንም ነገር ያቀርባል። ልክ አይደለምን? ስለዚህ ለጸሎት መልስ ይሰጣል። እሱ... እግዚአብሔር ጸሎትን-የሚመልስ አባት ነው።

47 አሁን፡ ስለዚህ... በዚህ የመጨረሻ ሰብሰባዎች መዝጊያ፡ እና የመሳሰሉትን፡ እንደ እኛ አሳብ... እያደረግን እንዳለን፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ ምናልባት በጉባኤው መጨረሻ ላይ—ጥቂት የመለየት ጸጋ አገልግሎት ሊኖረን ይችላል፡ ምናልባት ጉባኤው እየተካሄደ ሳለም እንዲሁ። እሱ እራሱ ምን እንደሚያደርግ አናውቅም። እኔም እንደዛ መሆኑ ደስ ይለኛል። ነገሮችን ወሰናችሁ አታስቀምጡበት፡ እሱ እንደፈለገው እንዲያደርግ ይፍቀዱለት።

48 አሁን፡ የራዕይ መጽሐፍን 4ኛው ምዕራፍ እንክፈት፡ እና ሰዓቱን አቁሙት።

49 [አንድ ወንድም ወንድም ብራንሃምን አነጋገረው—አርታዒ።] እዎ። አዎን፡ ወንድሜ። [ያ ወንድም ንግግሩን ቀጠለ። ባዶ ቦታ በቴፕ ላይ።] በእርግጠኝነት፡ ያንን እምናለሁ። ሙሉ በሙሉ፡ እምናለሁ።

50 ይኸው፡ ወንድም ዌልች ኢቫንስ፡ እዚያ የተቀመጠው እሱ ይመስለኛል። ራዕይ ምዕራፍ 4 እየከፈትን... ይህን ልንገራችሁ።

51 በቅርብ ጊዜ፡ እዚህ በሎይቪል ውስጥ ስላለው መኪኖች ስለሚስርቀው አንድ ቡድን ሁላችሁም በጋዜጦች ላይ ሰምታችኋል አንብባችኋል፡ ወደ ኬንታኪ ዙርያ፡ በፍጥነት ይወስዷቸዋል። እና በኬንታኪ ውስጥ የባለቤትነት መታወቂያም አያስፈልጋችሁም፡ ኬንታኪ ውስጥ ይሰሩላችኋል። ስለዚህ... ማድረግ ያለባችሁ እዚያ ወሰዳችሁ መሸጥ ብቻ ነው። ስለዚህ እነዚህን መኪኖች ወሰደው አስገብተው እንደገና ቀለም ቀብተው፡ እነዚያን መኪኖች አውጥተው ይሸጧቸዋል። ከእናንተ የሚጠበቀው የመኖሪያ ሰፈር ቁጥር ብቻ ነው—ከዚያ የባለቤትነት ደብተር ይሰሩላችኋል። እናም መኪናውን ከመንገድ ወሰደው በፍጥነት ያነሱት እና የሆነ ቦታ በሆነ መጋዘን ውስጥ ያጣድፉታል፡ ወዲያውኑ ሙሉ በሙሉ ይቀይሩታል፡ እያችሁ፡ እንደገና—ይቀባል ወዘተ፡ ከዚያ በኋላ ወጥቶ ይሸጣል። እንዲህ አይነቱ የማጭበርበር ስራ፡ በተለይ በዩናይትድ ስቴትስ ሁሉ አለ፡ ከሌሎቹ—ሁሉ በበለጠ ግን በኬንታኪ አለ። በቅርብ ጊዜ ስለዚህ ጉዳይ በጋዜጣ ላይ አንድ ጽሑፍ አነበብኩ።

52 እና፡ ይህ ታላቅ፡ ደግ-ልባም፡ ውድ ውንድማችን ኢቫንስ እና ቤተሰቡ፡ ወንጌል ለመስማት ዘወትር እሁድ ከማኮን፡ ጆርጂያ፡ እዚህ ድረስ መኪና

እየነዱ ይመጣሉ። ኦህ፡ እንዴት ያሉ ታማኝ፡ እና እውነተኛ ወዳጆች ናቸው! እና እዚህ ወዳለው ሚለርስ ካፊቴሪያ ይሄዳል…

53 ለሚለርስ ማስታወቂያ ለመስራት አይደለም፡ ግን በኬንታኪ ውስጥ ምርጥ ምግብ እንዳላቸው እሰባለሁ፥ በሎይቪል፡ ኬንታኪ፡ ነው። ይህ ማለት… አባባሌ ገብቼ የበላሁባቸው የግለሰብ ቤቶች ማለቴ አይደለም፡ ማለቴ፡ (እንደምታውቁት) ከውጭ ነው። እዚያም፡ እበላለሁ። ቤተሰቦቼን እቤት ውስጥ ከምመግባቸው በላይ በአነስተኛ ዋጋ እዚያ መመገብ እችላለሁ። ትክክል ነው።

54 ስለዚህ እኔም እዚያ እገባለሁ፡ ወንድም ኢቫንስም ገባ መኪናውን ከውጭ ፓርክ አርጎ ምግብ አምጥተውለት እየበላ ነበር። ሲወጣ (ከነሙሉ ልብሶቹ ጋር) የቤተሰብ እና ሁሉም ጨምሮ፡ መኪናውንም ወይም ምንም ነገር አላስቀሩለትም። ሁሉም ነገር ጠፋ። እንግዲህ፡ ምስኪኑ፡ ወንድም ኢቫንስ እንደ ሁላችንም ሰው ነው፡ አነስ ያለ ንግድ ቤት አለው፡ በመኪናዎች ላይ ይሰራል፡ የተበላሹ ዕቃዎች እየገዛ ይጠግናል። ምስኪን ሰው ነው፡ እናም በዚህ አይነት ወንጌል ስለሚያምን ገንዘቡን ወደዚህ ለመምጣት ይጠቀምበታል። እግዚአብሔር ወደዚያ አገር፡ የሚረዳቸው መልእክተኛ እንዲልክላቸው እጸልያለሁ።

55 እና፡ ወንድም ኢቫንስ መጣ፡ ምን ማድረግ እንዳለበት አያውቅም። ለፖሊስ አሳውቆ ነበር ሊያገኙት አልቻሉም። ስለዚህ ወደ ቤት መጣ፡ እሱና ወንድም ፍሬድ እና ሌሎች ነበሩ፡ ክፍሉ ውስጥ ገብተን ስለ ጉዳዩ ተነጋገርን። እንዲህ አልኳቸው፡ “አሁን… ” እንዲህ አደረግን፡ ቤት ውስጥ ቁጭ አልን፡ ምን እንደተፈጸመ ተረዳን፡ ከዚያ በኋላ ወደ እግዚአብሔር አቀረብነው። ስለዚህ፡ ያን ጊዜ፡ የትም ይሁን “መኪናውን የወሰደ ያን ሰው፡ አዙሮ እንዲመለስ አድርገው፡” ብለን ጌታን ጠየቅነው።

56 ብዙውን ጊዜ በቦውሊንግ ግሪን ዙሪያ ወይም የሆነ ቦታ ይነዷቸዋል፡ ወዲያውኑ እዚህ ካለው ግርግር ያሰወጣቸዋል፡ አያችሁ፡ እንዲህ የሚያደርጉት… እንደገና እስኪቀቧቸው እና እስኪያስተካክሏቸው ድረስ ነው። ይሄኛው በጣም ቆንጆ መኪና ነበር፡ ስቴሽን ዋገን ይመስለኛል። ልክ ነው፡ ወንድም ኢቫንስ? ስቴሽን ዋገን—ነበር።

57 እና፡ ከዚያስ ምን ሆነ፡ ወርደን ጸለይን። ጌታም—ምስክርነትን አደረገልን፡ ሰላም ሆነ፡ ሁሉም ተረጋጋ። ስለዚህ የጌታ ኃይል ከእኛ ጋር ገባ። ወንድም ኢቫንስ ወጣ እና ጀመረ፡ በሆነ መንገድ እንዲወርድ ተሰማው።

58 ወደዚህ ወደ ጀፈርሰንቪል ተመልሶ መጣ። መኪናው የተሰረቀው በሎይቪል ውስጥ ነበር፥ እነሆ መኪናው ቆሞ ተገኘ በውስጡም በቂ ነዳጅ ነበረው… እንደውም፡ በዚያ ውስጥ፡ ወደ ቦውሊንግ ግሪን ደርሶ የተመለሰ ያህል ነበር። ከመኪናው ወርደው፡ መኪናውን አሰቁመው፡ ቁልፉን ውስጥ ትተው፡ አስተካክለውለት ትተው ሄዱ፡ እሱ ማግኘት በሚችልበት እዚሁ በጀፈርሰንቪል፡ ሎይቪል ውስጥ ሳይሆን፡ እዚሁ ጄፍ.፡ ከርቀት መልሰው አመጡት።

59 ታውቃላችሁ፡ ጌታ ወፎች እንዲታዘዙት፡ ሰዎች እንዲታዘዙት፡ ጠላት እንዲታዘዘው ማድረግ ይችላል። እርሱ… አዎን፡ ጌታዬ፡ እርሱ’ኮ አምላክ ነው።

ወደ ቦውሊንግ ግሪን ያህል ርቀት ከተጓዘበት ከግማሽ ታንከር ነዳጅ በስተቀር፡ ከመኪናው ምንም ሳይጠፋ ቆሞ ተገኘ፡ መንፈስ ቅዱስ ራሱ እንዲህ ሳይለው አይቀርም፡ “ተመለስ! መኪናውን ወደ ጀፈርሰን ቪል አድርስ። እዚህ መንገድ ዳር አቁም፡ እና **እዚህ** ፓርክ አርገው፡ (እኔም መጥቶ እንዲያገኛት **በዚህ** መንገድ እና **በዚህ** መንገድ እልከዋለሁና)።” ትክክል ነው ወንድም ዌልች? በትክክል። እያችሁ።

60 እሱ አምላክ ነው! ወንድም ሮይ ሆይ፡ ጸሎትን ይመልሳል። እንዲሁ ነው... አንተንም፡ ወንድም ሰላውተር፡ ተመሳሳይ ነገር ነው፡ ትንሿን ውሻህን ፈውሶልሃል። እናም እንደሚፈውስ፡ ጸሎቱን እንደሚመልስ፡ አሁንም ተአምራትን እንደሚያደርግ አውቃለሁ፡ አሁንም አምላክ ነው፡ ሁልጊዜም አምላክ ነበር፡ ሁልጊዜም አምላክ ይሆናል!

> እሱ—በሰገነት ላይ አምላክ ነው፡ (እዚህ ቤተ ክርስቲያን የሚዘምረው ወንድም፡ ምን ነበረ? )
> በኩሽናም አምላክ፡ በእርሻ ውስጥ አምላክ፡
> በተሽከርካሪ ውስጥ አምላክ፡ በሁሉም ሰፍራ አምላክ ነው፡
> የሙላት አምላክ—በሁሉ ለሁሉ፡ አምላክ።

61 ኦህ፡ እንዴት ድንቅ ነው! ከአፍታ በኋላ ወደ ሰብከት እንገባለን ወደዚህ ማብራሪያ በጭራሽ አንገባም።

እሺ፡ ለጸሎት ለአፍታ ብቻ አንገታችንን ዝቅ እናድርግ።

62 ቸር የሰማይ አባት ሆይ፡ ልባችን በውስጣችን እስኪነድ ድረስ መንፈስህ በመካከላችን እንደ ወረደ፡ በዚያም እንደሚናገረን ልባችንን ዘርግቶ እንደሚይዝ ተረድተናልና፡ ቅዱስ ቃልህን በጣም እንወዳለን። ጌታ ሆይ፡ ስለዚህም በዚህ ደስ እንደሚለን ይሰማናል።

63 እና ብዙ ግራ መጋባት ባለበት በዚህ ጨለማ ሰዓት ውስጥ ይህን እውቀናል... ነቢዩ እንደተናገረው፡- “በመጨረሻው ዘመን ረሃብ ይመጣል፡” እንደዚህ ባለው ሁኔታ፡ “እውነተኛውን የእግዚአብሔርን ቃል ስለመስማት እንጂ፡ ስለ እንጀራና ስለ ውሃ አይደለም፥ ሰዎችም እውነተኛውን የእግዚአብሔርን ቃል ፍለጋ፡ ከምስራቅ ወደ ምዕራብ፡ ከሰሜን ወደ ደቡብ ይኳትናሉ።” ቃል! ቃሉ ምንድን ነው? ኢየሱስ ቃል ነው፡ “ቃል ሥጋ ሆነ በእኛም አደረ።” የእውነተኛው የእግዚአብሔር ቃል መገለጥ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተነገረለት ሲገለጥ እና ሲፈጸም ለማየት፡ ሰዎች፡ ከቦታ ወደ ቦታ ይኳትናሉ እያገኙትምም። አምላክ ሆይ፡ ደስ ብሎናል፡ እኛስ ከብዙ አመታት በፊት አገኘነው፡ እና አንዳች ግራ መጋባት እንደሌለን ሰናይ፡ ለልባችን እጅግ ድንቅ ነው።

64 አምላክ ሆይ፡ “አምላካቸውን የሚያውቁ በዚያ ቀን ያደርጋሉ፡” ብለሃል። አሁንም ኢየሱስ ይፈጸማል ብሎ የተናገረውን ሁሉ ሲፈጸም እያየን፡ በመጨረሻው ዘመን ላይ እንገኛለን፡ በመካከላችንም ተገለጠ። እርሱ እንዳሰደረገ አሁንም ምልክቶች፡ ድንቆች፡ ተአምራት ሁሉ፡ ይደረጋሉ። እርሱ “በሰዶም ዘመን እንደ ሆነ፡ በሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናል፡” እንዳለ ሆነ።

65 አሁንም፡ ጌታ ሆይ፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ ወደዚያ ቃል እንድንደርስ፡ እና እነዚያን እውነተኛ ነገሮች እንድናገኝ ፍቀድልን በቃልም፡ ወደ ቀራንዮ እስራቸው፡ በእርሱ ዘንድም ሙሉት እንዳለን እንይ። ባለጠግነት በረከት ክብርም ሁሉ ወደተገባው ወደ እርሱ ይድረስ፡ መጥቶ በዙፋኑ ላይ ከተቀመጠው ከቀኝ እጁ መጽሐፉን ወደ ወሰደው፡ በራሱም ወደ ተቀመጠ ይድረስ፡ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ታርዷልና።

66 አባት ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት ስለሱ እንናገራለን። ልባችንን እንድትባርክ እንጸልያለን። መንፈሱ በመካከላችን ይንቀሳቀስ እና ይባርከን፡ ልምምዳችንን ያበለጽግ፡ በመካከላችን ያለውን በሽታ ይፈውስ፡ ድል የመንሳት ጸጋ ይሰጠን።

67 አሁንም፡ አምላክ ሆይ፡ ጠላትን ለመጋፈጥ ወደ መስክ ሰወጣ፡ በጸሎት ትጥቅ መታጠቄን ዘወትር እንዳስብ እርዳኝ። አቤቱ፡ በዚያ ትጥቅ እታመናለሁ፡ ጠላት ይመጣልና፡ ነገር ግን እናቶች አባቶች እና ወንዶችም ሴቶችም፡ ክርስቲያኖች ሁሉ፡ ከልምምድ ጋር ዳግም የተወለዱ ሁሉ፡ የሰማይ-ወገን የሆነው ህዝብ በጉልበታቸው ተንበርክከው ስለሚጸልዩ፡ ትጥቅ እንደጠበቀ አውቃለሁ፡ “አምላክ ሆይ፡ ማዳንን ሰጠን!” እናም፡ አባት ሆይ፡ ወደዚያው የጠላት ምሽግ እንድንወጣ እንድትፈቅድልን እንጸልያለን በዚያም በመጠባበቅ የሚገኙትን ድንቃድንቅ ነፍሳት እንድንማርክ ፍቀድልን። አድርግ፡ ጌታ ሆይ፡ ከጨለማም ወደ ብርሃን አውጣቸው። በኢየሱስ ሰም እንጠይቃለን። አሜን።

68 አሁን፡ በራእይ መጽሐፍ ምዕራፍ 4 ላይ። 3ኛውን ምዕራፍ ጨርሰናል፡ እና በትህትና ተረጋግተን እንቀመጥ እኔም ብዙ እንዳላቆያችሁ እሞክራለሁ። በዚህ 3ኛው ምዕራፍ፡ ዮሐንስ በተወሰደ ጊዜ፡ ቤተክርስቲያን በተምሣሌት ተወሰደች። ቤተክርስቲያኑ ተወሰደች፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ ዳግም ምጽአት ድረስ፡ ከእስራኤል ጋር ስራውን ይሰራል። እንዴት እንደሆነ አታዩምን? ዛሬ ሰዎች፡ ምን ይላሉ፡ “ታላቅ ነገር መላውን ዓለም እና ሁሉንም ነገር ያናውጣል።” ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም! አይደለም፡ ጌታዬ። የሚቀጥለው ስርዓት የቤተክርስቲያን መወሰድ ነው። በቤተ ክርስቲያን ዘመንን አንብቡ፡ ምን ታያላችሁ...

69 አሁን፡ እነዚህ የሚከናወኑ ሌሎች ነገሮች፡ ቤተ ክርስቲያን በክብር በምትገኝበት የሠርግ ሥነ ሥርዓት ወቅት ነው። እግዚአብሔር በታላቅ ድንቆች፡ በአለማቀፋዊ ተአምራት እና ነገሮች ተመልሶ ይመጣል፡ ያን ጊዜ በአይሁዶች ነውና፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን በጭራሽ አትሂዱ።

70 በ 3ኛው ምዕራፍ ላይ የቤተክርስቲያን ዘመን ያበቃል። ትክክል። የቤተክርስቲያን ዘመንም አስቀድመን እንዳየነው ከጥቂት መንጋ ጋር ያልቃል... አሁን በደንብ ሰሙኝ። ዛሬ ጠዋትም ይህን ክፍል ደግሜ አ—አነበብኩትና፡ ውስጤን እጅግ ሰባበረኝ፡ በቤተክርስቲያን ዘመን መጨረሻ ላይ የክርስቶስ ቦታ እና ሁኔታ፡ በራዕይ ምዕራፍ 3 ከቁጥር 20 እስከ 22 ድረስ። ክርስቶስ፡ በፍጻሜ ዘመን፡ የት እንዳለ አስቡት! በቤተክርስቲያን ዘመን መጨረሻ የት ነው ያለው? በእምነት ተቋማት እና በሐይማኖት ስርዓቶች ተገፍቶ፡ ከቤተክርስቲያኑ ውጭ ይገኛል። ሁኔታውስ ምን ይመስላል? ወደ ውስጥ ለመመለስ የሚሞክር ሰው። አሳዛኝ ሁኔታ ነው!

71 ከዚያ እዚህ እንደምናየው፡ “ከእነዚህ ነገሮች በኋላም፡” እንዲህ ብሎ የሚናገረውን ድምጽ ሰማ… ኦህ፡ ምን ነበረ? መንፈስ ከምድር ተለየ። “ከእነዚህ ነገሮች በኋላም፡” 1ኛ ምዕራፍ ጀመረ፡ ወ—ወይም 1ኛ ቁጥር፦

**ከዚያ በኋላም፡ አየሁ፡ እነሆም፡ በሰማይ የተከፈተ ደጅ ነበረ፥…**

72 ራዕ 4፡1፣ ቤተክርስቲያን ከሄደች በኋላ፡ ያን ጊዜ በ—በር ተከፈተ። በእነዚያንም ሁሉ አለፍን፡ በሩም ክርስቶስ እንደሆነም አወቅን። በሰባቱም የወርቅ መቅረዞች መካከል ይመላለስ የነበረው ድምፅም በሰማይ፡ “ወደዚህ ውጣ፡” ሲለው የሰማው ያው ድምጽ ነበር። ዮሐንስ ወደ ላይ ወጣ። በመነጠቅ የምትሄደውን ቤተክርስቲያን ተምሣሌት ነበረ።

73 ዮሐንስ በመንፈስ ወጣ፡ ወደ ሰማይም ተወሰደ እግዚአብሔር ለደቀ መዛሙርቱ ይሆናል ያላቸውን ነገሮች ሁሉ አስቀድሞ አየ፡ “እኔ እስክመጣ ድረስ ቢቆይ ምን እግዶህ? ” የጌታን መምጣት እና የሚሆነውን አየ። በምድር ላይ የሚሆነውን አየ ለቤተክርስቲያን መነጠቅ በምድር የሚሆነውን አየ፡ ከዚያም አልፎ ተወሰዶ የሺ አመት መንግስት ገብቶ አየ። ኦህ፡ አይገርምም ወይ?

74 አሁን፡ ባለፈው እሁድ በ 4ኛው ምዕራፍ እና 4ኛ ቁጥር ላይ ደርሰን ነበር።

**በዙፋኑ** ዙሪያም **ሀያ አራት ዙፋኖች ነበሩ፥ በዙፋኖቹም ላይ ነጭ ልብስ ለብሰው፡ በራሳቸውም የወርቅ አክሊል ደፍተው፥ ሀያ አራት ሽማግሌዎች ተቀምጠው ነበር።**

75 አሁን፡ እነዚህ ሽማግሌዎች መሆናቸውን ተምረናል። ለመልአክ ወይም ለሌላ ፍጡር **ሽማግሌ** ተብሎ አያውቅም። ሽማግሌዎች፡ የተቤዡ የሰው ወገኖች ናቸው! ምክንያቱም… ዙፋኖች፡ አክሊሎች፡ እና ግዛት ለመላእክት እንደሚገባ፡ በፍጹም ተነግሮ አያውቅም። ዘውዶች እና ዙፋኖች፡ እና ሌሎች፡ ለሰው ልጆች የተመደቡ ናቸው። እነዚያም ሽማግሌዎች አክሊል ደፍተው እና ለብሰው በዙፋን ላይ ተቀምጠዋል። በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችም አሥራ ሁለቱ ሐዋርያትና አሥራ ሁለቱ ነገዶች ሆነው እናገኛቸዋለን። ከነሱም **አራት እና ሃያ** ማለት፡ “ሃያ-አራት”፥ ስለመሆናቸው ነው፥ አሥራ ሁለት ሐዋርያት አሥራ ሁለት ነገዶች።

76 ከሰማይም፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ የምትወርድ ከተማን፡ እናያለን… ምድር ከፈነዳች በኋላ ሁሉም ተሰባብሮ በምድር ላይ ከእሳተ ገሞራ አመድ በቀር ምንም በማይቀር ጊዜ (የሚቀርላት ይህ ብቻ ነውና)፡ ከእንግዲህ ባህር አይኖርም። ባሕሩም ይደርቃል።

77 ማታ ለአንድ ሰው፡ ወይም ትናንት፡ የሆነ ቦታ ላይ ሳወራ፡ ምድር በአንድ ወቅት፡ ልክ፡ በጸሐይ ዙርያ **እንዲህ** ቆማ ነበር፡ ከላይ እስከታች ድረስ እኩል ሙቀት ያገኛት ነበር። በዚያ በብሪቲሽ በረዶዎች ስር፡ አምስት መቶ ጫማ ወደ ታች ወርዳችሁ ዘንባባዎችን ታገኛላችሁ። በድንገት መጣና፡ እንደነዚህ ማቀዝቀዣዎች በረዶ አደረጋቸዋል። ልክ እንደ እነዚህ **ማዳረቂያዎቻችሁ**፡ እና ልዩ ልዩ ነገሮች፡ ስትሮቤሪዎችን እና ሌሎች ነገሮችን **የሚያቀዘቅዙ** ዲፕ ፍሪዞች ለሚመጡ ዘመን እና ዘመናት እንደሚያቆዩ። አያችሁ? ያን ጊዜ የነበረውም ተመሳሳይ ነው። ወዲያውም ከጥፋት ውሃ በፊት የነበረውን ምድርን ያጠፋ

ጥፋት እና ጎርፍ ተከሰተ። ይህ በሆነ ጊዜ፡ አቶሚካዊ ኃይሎች ከመዞርያ ቀለበቷ እንድትወጣ አደረጓት፡ እና ያን ጊዜ በረዶ ሆነች አሁንም በዚያ ቆማ ትገኛለች። አያችሁ? በዚያ በአርክቲክ ዙርያ እና አካባቢ ላይ፡ ወደ ታች ወርዳችሁ ብትቆፍሩ፡ የዘንባባ እና ልዩ ልዩ ዛፎች ታገኛላችሁ። ጸንተው፡ በአንድ ወቅት ውብ በሆነ ሁኔታ ይኖሩበት እንደነበር ያሳያል። አሁን ግን ወድሟል።

78 አሁን፡ እግዚአብሔር ያንን ውሃ ያገኘበት ይመስለኛል፡ ዘፍጥረት ሲጀምር፡ ዘፍጥረት 1 ላይ፡ "ምድር ቅርጽ አልባ፡ እና ባዶ ነበረች፡ ውኃም በጥልቁ ላይ ነበረ። የእግዚአብሔርም መንፈስ በውኃ ላይ ተንቀሳቅሶ፡ 'ብርሃን ይሁን' አለ።" እግዚአብሔርም ምድርን ሠራ፡ ምድርንና ውኃን ለየ። ምድር ሁሉ ግን ተሸፍኖ ነበር። አሁን፡ ያደረገው ነገር፡ እንዲህ ነው... ጠፈር ውስጥ፡ እንዲህ ነው... ጠፈር ሆነ... ጠፈርም በሃይድሮጅን እና በኦክሲጅን፡ እንዲሁም በልዩ ልዩ ነገሮች የተሞላ ነው። ከዚያም ልክ ከምድር ላይ ለይቶ ከፍ አደረገው። ያኔ በምድር ላይ ባህር አልነበረም። ያን ጊዜ ዝናብ አይዘንብም፡ እግዚአብሔር ምድርን ያጠጣ ነበር። እንደ መስኖ፡ በምንጮች እና በሌላ ነገሮች ያጠጣት ነበር። ያን ጊዜ እርሱ... ያኔ ያደረገው ብቸኛው ነገር...

79 ሰው ከምህዋሯ ወደ ሌላ ጥግ ባላተማት ጊዜስ፡ ምን ሆነ? እንዲህ ወዳለው ሁኔታ ጣላት... **እዚህ** ጋር ሙቀት፡ **እዚያ** ጋር ብርድ። እሺ ሙቀት እና ብርድ፡ ምን ያጠራቅማል? ማዶ ላይ ባሉት መስታወቶች ተመልከቷቸው፡ እዚህ ሙቀት ከውጭ ብርድ አለ። ላበቱን አያችሁት? ዝናብም ላብ እንጂ ሌላ አይደለም፡ እንፋሎት ነው። ውኃም አመድ ነው። እና እንግዲህ ይህ ነገር...

80 እንዲህ የሚለውን መዝሙር እወደዋለሁ፥

ጌታ ሆይ፡ ድንቅ እጅህን፡ ሜዳው ላይ አኖርከው፡
ግሩም እጅህ በግጦሽ ላይ አኖርከው፥
ጌታ ሆይ፡ ከምንጭ አፈሰስክበት፡
ተራሮችን ከፍ አደረግካቸው፡
አቤቱ ጌታ ሆይ፡ ድንቅ እጅህ በላዬ ጫንብኝ።

ደመናን አበጀህ፡ የዝናብ መውጫ ደመና ሰርተሃል፡
ከዝናብ ባህርን አደረግህ፡
ከባሕር ደመናን አወጣህ፡
ሕይወትን ታትረፈርፍልን ዘንድ፥
ጌታ ሆይ፡ ምድር እና ሰማይን በትእዛዝህ ታሰማራለህ፡
አቤቱ፡ ድንቅ እጅህ በላዬ ጫንብኝ። (ኦህ፡ እንዴት ድንቅ ነው! አዎን፡ የሰማይ አምላክ እርሱ ነው።)

81 ከዚያም በዚህ ታላቅ ዘመን፡ አሁንም እንደገና **እንዲህ** ዘንበል እያለ ነው፡ ቃል ገብቶልናል፡ "በዚህ ጊዜ ግን እሳት እንጂ፡ ውኃ አይደለም!" ከመወርወር ይልቅ... ምድርን ከፀሀይ አርቀው ወረወሯት፡ ስለዚህም፡ ቀዘቀዘች። ወደ ጸሐይ ከወረወራችኋት፡ ትነዳለች። በውኃም እንዳጠፋት ቀስቱንም በሰማይ እንዳደረገው፡ እርሱ "ከእንግዲህ ያንን አያደርግም፡" እርሱ፡ ቃል ኪዳን እንደገባ "ያቃጥላታል!" እንግዲያውስ ኃጢአትና ውበት ርኩሰትም ወደሚገኝበት ቦታ መጣችሁ...

82 በቅርብ ጊዜ ሜዳ ላይ እየነዳሁ እሄድ ነበር። ህጻን ልጅ ሳለሁ እንዲህ አስብ ነበር፡ የታሪክ እና የጂኦግራፊ መጽሐፍቶቼን ይዤ ስለ ምዕራባዊ ሜዳዎች አስብ ነበር። "አንድ ቀን፡" እላለሁ፡ "ኃጢአት በሌለበት በጸጥታ እና በእርጋታ እኖራለሁ፡ መስኮቹን እዞራቸዋለሁ እንደ ኢንዲያኖች አደን እወጣለሁ። በዚያም፡ ህይወቴን ሙሉ፡ በሰላም እ—እኖራለሁ።" አሁን ግን... ነጭ ሰው ገብቶበታል። ነጭ በገባበት ሁሉ፡ ኃጢአት ከእርሱ ጋር አለ። በምድር ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ ትልቁ ገዳይ እና ነፍስ አጥፊ፡ ነጭ ሰው ነው። ከሁሉም ዓይነት ቀለሞች ከዳተኛ ነው!

83 ቅርብ ጊዜ እዚህ ጋዜጣ ላይ (ወንድም ቶም፡ ከአፍሪካ)፡ ከሁለት ሳምንት በፊት ጋዜጣ ላይ አንዲት አንቀጽ አይቼ ነበር፡ በዚያ ይመስለኛል፡ እንዲህ አለ... እንዲህ ይላሉ፡ "አሜሪካውያን አሁንም ወደ አፍሪካ እንዲገቡ ከተፈቀደላቸው፡ የዛሬ አሰር አመት ታላቁ የአፍሪካ አንበሳ፡ እና ዝሆኖች ፈጽመው ይጠፋሉ።" እነዚህ ከሃዲዎች በሄዱበት ይተኩሳሉ። የቆሰለውን ለመደገፍ ሲሞክሩ የሚያሳይ የሁለት ትልልቅ ወንዶች ምስል ነው። እንባ ከዓይናቸው የሚወርድ ይመስላል። እንዲህ እንዲሆን አልፈለጉም... ወንዶች ሴቷ እንድትሞት አልፈለጉም። ሁለቱም በየፊናቸው ከጎኗ፡ **እንዲህ** ደግፈዋታል፡ ወደ መሬት... እንዳትወድቅ ይጠብቋታል። በተኩስ ተበሳስታለች። እንዲህ አይነት አተኳኮስ የሚተኩስ ሰው በእጁ ጠመንጃ መያዝ አይገባውም። እውነት ነው። ያንን የመቆጣጠር በቂ ሐሞት የለህም።

84 አሁን፡ ከጥቂት አመታት በፊት፡ ጥቂት የአጋዘን መንጋዎችን፡ ወደ ጓደኛዬ፡ ወደ ወንድም ሮይ ሮበርስን፡ ለማስማራት እየሞከርኩ እና ያን ጊዜ በዚያ፡ በኮሎራዶ በማስማራበት ጊዜ፡ ጥሩ መንጋ እንደነበረን አስታውሳለሁ። እኔና ጄፍ በመንጋው ውሰጥ ወደ ሰማንያ የሚጠጉ አጋዘኖችን፡ ለዓመታት እና ለዓመታት እናስማራ ነበር። አንዳንድ ቢሮ ውሰጥ የሚሰሩ የተንዘላዘለ፡ እና የተገመደ ሱሪ የለበሱ ወንዶች ከዴንቨር ወጥተው ይመጡ ነበር። አዳኞች ናቸው። እምም! ሲመጡም፡ በጂፕ እና በመሳሰሉት ነገሮች ላይ፡ ተሰብሰበው፡ ወደ ክልላችን ይገቡ ነበር።

85 እናም እነዚህን አጋዘኖች ከኋላቸው ባለው ተራራ፡ አንድ ወይም ሁለት ማይሎችን ርቁ፡ እሰማራቸዋለሁ። እና ትልልቆቹ በሬዎች እና ሌሎች፡ በስነ ስርዓት መግራት ይኖርባችኋል፡ ካልሆነ ግን፡ መንጋው ሁሉ ይበታተናል። ልክ እንደ ከብቶች ወይም ማንኛውንም ነገር የሚራቡ ናቸው። የዱር አራዊት ለኛ ተመሳሳይ መሆን አለበት። ዒላማ አይደሉም። ዒላማን መለማመድ ከፈለጋችሁ የምትተኩሱበት ዒላማዎች እዚህ ጋር አለላችሁ። በትክክል። እንደዚህ አይነት ዕርድ መፈጸም ነውር ነው። ኃጢአተኝነት ነው፡ የእግዚአብሔር አይደለም!

86 እና አንድ መቶ ሃያ-ሶስት የመትረየስ ተኩስ ቆጠርኩ፡ ልክ፡ ከትከሻቸው እንደሚተኮሰ ዓይነት ይመስላል። እና በማግስቱ ጠዋት፡ ወንድም ባንክስ ዉድ ከእኔ ጋር ሆነን፡ ወደ ተራራው ወጣን፡ ደም የፈሰሰበት አሰራ ዘጠኝ ቦታዎች ቆጠርኩ። ስለ አደን ምንም ካላወቃችሁ፡ ያን የሚያክል ትልቅ እንሰሳ፡ የሚገድለውን ጥልቅ ምት ልትመቱት ትችላላችሁ። አንዱን መትተው ሌላውን በማስከተል፡ "ባንግ፡ ባንግ፡ ባንግ፡" እንደው ዝም ብለው ተለቀቁ። ምክንያቱ፡ ይሞታሉ። ከዚያስ... ከዚያማ ትኩሳቱ ከገባባቸው በኋላ፡ ስታዩአቸው ለምንም

አይጠቅሙም፡ ወዲያው ይበሰብሳሉ፥ ጥንብ አንሳዎች፡ ቀበሮዎች እና ሌሎች፡ ይበሉአቸዋል። በደም የጨቀዩ አስራ ዘጠኝ ቦታዎች፡ ትላልቅ ኮርማዎች፡ **ይሄን** የሚያክሉ ትላልቅ ሶኮናዎች፡ በእነዚያ ጠመንጃዎች ከወደቁበት ስፍራ ሁለት ፊት ያህል ርቀት በደም ጨቅይቷል። እንደዚህ ያለ ከሃዲ በእጁ ጠመንጃን እንዲይዝ መፍቀድ የለባቸውም። በትክክል። ጠመንጃን የመቆጣጠር ሐሞት የለውም። ኦህ፡ ያንን ማድረግ፡ አስከፊ ኃጢአተኝነት ነው።

87 አስቃቂ ነገር ነው፡ ይሁን እንጂ አሜሪካውያን እንዲህ ናቸው። ካናዳ፡ እናንተ ድንቅ የካናዳ ሰዎች ሆይ! አሜሪካ በዚህ ከቀጠለች፡ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ፡ ካናዳ እንደ አሜሪካ ወራዳ-ትሆናለች። የካናዳ ድንበሮችን በየትኛውም ቦታ ዙሩ፡ እና ያንን የአሜሪካን ድባብ ታዩታላችሁ። ይህች አሜሪካ የዓለም መንግስታት ሁሉ አመንዝራ ናት። በትክክል እንዲሁ ናት፡ አሁንም ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ክፉ ትሆናለች። ወደ ፍጻሜዋ ተቃርባለች! መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጥፋቷ ይናገራል፡ እንዴት እንደምትሆን ይነግራል። አሜሪካ፡ ተራ-የማትረባ፡ የበሰበሰች፡ የቆሸሸች፡ ክፉ ናት። ይህ ትክክል ነው። ታላቅ አገር ነበረች። የወንጌል መልእክት ተሸክማ ነበር። እንዲህ እንድትሆን የሚያደርጋት ምንድን ነው? የወንጌል መልእክትን ስላልተቀበለች፡ እና እውነቱን ስለተቃወመች ነው። አስቃቂ ነች። ግድ የላችሁም፡ ተቃርባለች። የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና በራዕይ ውስጥ አይቼዋለሁ! እየመጣ ነው። ስለ ኃጢአቷ ትከፍላለች።

88 ድሮ አሜሪካ አሜሪካ በነበረችበት ጊዜ፡ ታላቅ ሀገር ነበረች። ከእስራኤል ዘመን ጀምሮ፡ በዓለም ላይ የምትታወቀው ታላቅ ሀገር አሜሪካ ነበረች፡ አሁን ግን በእርግጠኝነት እራሷን በክላለች። መልእክቱን ንቃለች። ተራ ነገር ተቀበለች... አሁን ራሷን አቅርባለች... አሁን የት እንደደረሰች ማየት ትችላላችሁ። ባለፈው ምርጫ ላይ መንፈሳዊ አቋሟ የት እንደደረሰ፡ ሁሉም ያውቃል። ኧሃ-እህ። እሷ አታውቅም።

89 እንግዲህ፡ እነዚህ ሽማግሌዎች በዙፋኑ ላይ ተቀምጠዋል። አሁን፡ 5ኛው ቁጥር፡ እንጀምራለን፦

> **ከዙፋኑም መብረቅና...** ነጐድጓድ... **ድምጽም ይወጣል፥ በዙፋኑም ፊት ሰባት የእሳት መብራቶች** ይበሩ ነበር፡ **እነርሱም ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት ናቸው።**

90 ኦህ፡ ይህን ወደድኩት! እናንተስ? ኦህ፡ ታውቃላችሁ፡ ኮቴ ልክ የሆነኝ ያህል ተሰማኝ። ማ... ማለቴ... ኦህ፡ ያው፡ ትረዱኛላችሁ፡ መንፈሳዊ ኮት ማለቴ ነው። በጣም ጥሩ።

91 “ከዙፋኑ ውስጥ።” እስቲ ስለዚህ ዙፋን አሁን ለጥቂት ደቂቃዎች እንነጋገር። ይህ ዙፋን የምሕረት ዙፋን አልነበረም። የምህረት ዙፋን አልቋል፥ ከዚህ በኋላ ምሕረት የለም፡ ከምህረት ውጭ ነው። እንዴት እየሄድን ነው... የፍርድ ወንበር የክርስቶስ የፍርድ ወንበር፡ ይህ የፍርድ ወንበር፡ የነጩ ዙፋን ፍርድ የሚሆነው እንዴት ነው? ታዲያ ምህረት ይኖራልን? የሚዘረጋ አንድም ምሕረት የለም። በፍርድ ዙፋን ላይ በመጨረሻው አቅማችሁ “ምሕረት” ብላችሁ ልትጮኹ ትችላላችሁ፡ እንዲህ ነው፡ የሆነ ቦታ በአየር ላይ እንደመጮኽ ነው፡ ምክንያቱ ከእንግዲህ ምሕረት የለም።

92 የምሕረት ቀን **አሁን** ነው! አሁን፡ ወደ ብሉይ ኪዳን እዚህ በጥቂቱ እንመለስና ምሕረት ምን እንደሆነ እንወቅ። ተመለሱ እና በዚህ ዙፋን ላይ ምን እንደተፈጠረ ተመልከቱ። ይህ ዙፋን፡ በእርግጥ—የፍርድ ወንበር፡ ነው። እና አሁን... ዛሬ ምሕረት የሆነበት ምክንያት፡ የስርየት መክደኛው በስርየት ስለተረጨ ነው። ደም! ደም በፍርድ ወንበር ላይ እስካለ ድረስ ፍርድ አይደለም፡ ምሕረት ነው፡ ምክንያቱም ፍርድን ለማቆየት የሆነ ነገር ሞቷል። ከገባችሁ፡ "ኣሜን" በሉ። [ጉባኤው "ኣሜን፡" አለ።—አርታዒ።] ደም በስርየት መክደኛው ላይ እስካለ ድረስ፡ ፍርድን ለማስቆም የሆነ ነገር እንደሞተ ያሳያል። ቤተክርስቲያን ስትነጠቅ ግን፡ የስርየት መክደኛው የፍርድ ወንበር ይሆናል!

93 እንደምታውቁት፡ እዚህ፡ በአዲስ ኪዳን ውስጥም፡ ያው ነው፡ "እና መቅደሱ።" ዳኛው—በዚያ... በመቅደስ ውስጥ ነው፡ ፍርድ ሰጪው በመቅደስ በወንበሩ ላይ ነው። አሁን፡ በመቅደሱ ውስጥ የነበረው የፍርድ ወንበር ጢስ ሞላ። ምን ነበር? እንደ ሲና ተራራ፡ ፍርድ! ምሕረት ከእግዚአብሔር ዙፋን—ለቆ ሄዶ ነበር። እግዚአብሔር አለምን ያለምህረት ይፈርዳል። ስንቶች ታውቃላችሁ?

94 በዚያ ቀን እሱ የሚያውቀው አንድ ነገር ብቻ ነው፡ እርሱ ምንድን ነው? ደም። የተቆጣውን አምላክ የሚያረጋጋው ይህ ብቻ ነው።

95 አዳምና ሔዋን ማንኛውም ሜቶዲስት፡ ባፕቲስት፡ ፕሪስባይቴሪያን፡ ወይም ጴንጤቆስጤ ሊሰራው የሚችል ያህል ጥሩ ቅጠል ሰፍተው ነበር፡ ራቁታቸውን ሸፈኑ። እግዚአብሔር ግን አልፎ ሊያየው ይችል ስለነበር፡ አንድ ነገር ገደለና የሞተውን ቆዳዎች ገፎ—በሞተ የእንስሳ ቆዳዎች ሸፈናቸው። ደም ስፍራውን መተካት ነበረበት። ቁጣውን የሚያበርደው እሱ ነው፡ ደሙን አይቶ ይመለሳል፡ ምክያቱ ህይወቱን የሰዋ ነገር ሰላለ ነው። አምላክ ሆይ!

96 አሰቡት! እግዚአብሔርን ሊያበርደው የሚችል አንድ ነገር ደም ነው። ቁጣውን ማብረድ የሚችል አንድ ደም አለ፡ እርሱም የገዛ ልጁ ነው። የገዛ ልጁ ደም መሆኑን ሲያይ፡ ወደ ኋላው ይመለሳል። ምክንያቱም ሰጦታው ያ ነው... እግዚአብሔር አሰቀድሞ ያወቃቸውን ይቤዣቸው ዘንድ፡ ለልጁ ሰጠ፡ እግዚአብሔርንም ከፍርዱ እንዲመለስ አደረገ። ነገር ግን ያ ደሙ ሲወገድ፡ አሰቀድመው የታወቁ ሁሉ ወደ ክቡር ሥጋ በተጠሩ ጊዜ፡ ቤተክርስቲያኑ ተዘጋጅታ በተወሰደች ጊዜ፡ የእግዚአብሔር ቁጣ በሰዎች ላይ ነው።

97 ኦህ፡ ወንድሜ ሆይ፡ በዚያ ፊት ለመቆም ፈጽመህ አትፈልግ! መትረየስ ፊት ልቁም፡ ልቆራረርጥ፡ ኢንች በኢንች በመጋዝ ልሰንጠቅ፡ (እንደ ኮሎምበስ ፈረሰኞቹ መሃላ) ምንም ይድረሰብኝ፡ ሆዴን ይክፈቱ በውስጤ ያለውን ስልፈር እና ሁሉ ያቃጥሉ፡ እጆቼና እግሮቼ ይቁረጡ፡ ምንም ይሁን ምን ያድርጉ፡ ነገር ግን በነጩ ዙፋን ፍርድ በእግዚአብሔር ፊት **ፈጽመህ** አታቁመኝ።

98 አቤቱ፡ በክርስቶስ ዙፋን ፊት ያለችውን **ይህች** ትንሿን ዙፋን ልውረስ ደሙንም ልቀበል እርዳኝ። ጌታ ሆይ፡ በእጄ ምንም አላመጣሁም።

ሌላ ምንጭ አላውቅም፡
የክርስቶስ ደም ብቻ ነው። (ሌላ አላውቅም።)
ተስፋዬም ኑሮዬ ይህ ነው፡

የክርስቶስ ደም ብቻ ነው።

99 ኤዲ ፔሮኔት በመዝሙሩ ውስጥ... እንዲህ ማለቱ አያስገርምም። ክርስቲያን፡ ጠንካራ ክርስቲያን በነበረ ጊዜ፡ መዝሙሮቹን መግዛት አልፈለጉም። አንድ ቀን እንዲህ አለ፡ "ሌላ እጽፋለሁ፡ እና አንድ ቀን... ይቀበሉታል።" (ሰዎቹም በሃይማኖታዊ መዝሙሮች ውስጥ የበለጠ ዘመናዊ ነገር ይፈልጉ ነበርና።) አንድ ቀን በዚያ መንፈስ ቅዱስ ያዘውና፡ ብዕሩን አንሥቶ እንዲህ ሲል ጻፈ፦

ሁሉም የኢየሱስን ስም ኃይል ያወድሱ!
መላእክትም ይሰገዱ፡
የክብር ዘውድ ይምጣ፡
የጌቶችም ጌታ ያንግሱ።

በጠንካራ ዓለት፡ በክርስቶስ፡ ቆምኩኝ፡
ሌላው ሁሉ የሚያሰምጥ አሸዋ ነው፡
ሌላው ሁሉ የሚያሰምጥ አሸዋ ነው።

100 ቤተ ክርስቲያን ይሁን፡ ወዳጅም፡ ጠላትም ይሁን፡ ብሔርም ይሁን፡ ሀብትም ቢሆን፡ ድህነትም ቢሆን፡ ጥሩም ቢሆን፡ ወይም ምንም ቢሆን፡ ሌሎች ምክንያቶች ሁሉ የሚያሰምጡ አሸዋዎች ናቸው! እንዲሁ ብቻ ናቸው፡ በመጨረሻም ይተፋሉ። ግን፦

... በጠንካራ ዓለት፡ በክርስቶስ፡ ቆምኩኝ፡
ሌላው ሁሉ የሚያሰምጥ አሸዋ ነው። (ይህን ልብ በሉ።)

101 ልብ በሉ! ወደ ዘሌዋውያን 16 እንሂድና፡ ከጀርባው እናንብብ፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጀርባ፡ በሌዋውያን ሕጎች ውስጥ፡ ዘሌዋውያን—ኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 16ን ተመልከቱ። ከ16ኛው ምዕራፍ 14ኛው ቁጥር ጀምሮ። ኦህ፡ በ—በእነዚህ ነገሮች ላይ ጊዜ ወሰጄ፡ ባስተምር ደስ ይለኛል። ዘሌዋውያን አራተኛ፦... ወይም ዘሌዋውያን 16:14።

**ከወይፈኑም ደም ወስዶ፡ በስርየቱ መክደኛ ላይ ወደ ምሥራቅ በጣቱ ይረጨዋል** (በምህረት መክደኛው ላይ! ተከታተሉ፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወደዚህ ጉዳይ እንገባለን።)... **ወደ ምስራቅ፥...**

102 "ወደ ምስራቅ" የሚለውን ቃል አትርሱ! ኢየሱስ የሚመጣው ከየት ነው? ከምሥራቅ፡ በክብር ደመና። ጸ-ሐ-ይ በየት በኩል ትወጣለች? በምስራቅ። ል-ጅ በየት በኩል ይወጣል? በምስራቅ። የምህረት መክደኛው የት ተቀምጦ ነበር? በምስራቅ። ሁላችሁንም **በዚህ** መንገድ ወደ ምሥራቅ ለምን ተቀመጣችሁ? ለምን? መሠዊያው ወደ ምስራቅ ስለሆነ። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ እናየዋለን፡ በሚያምር ሁኔታ፡ በስዕል መልኩ አስፍረዋለሁ። በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ እነዚህ ካርታዎች ማየት እንድንችል፡ የተቻለ ያህል ጋዜጣ እና ሌላ ነገሮች እንዲያመጡልኝ ጠይቄአለሁ። በጣም ጥሩ፦

**... ወደ ምሥራቅ... በጣቱ ይረጨዋል፥ ከደሙም በመክደኛው ፊት... በጣቱ ሰባት ጊዜ ይረጫል።**

103 ኦህ፡ አያምርም ወይ? "ወደ ምስራቅ ሰባት ጊዜ።" ምንድነው ይሄ? ሰባቱ የቤተክርስቲያን ዘመናት በደም ይሸፈናሉ። ሃሌ ሉያ! የኢየሱስ ክርስቶስ

ደም፡ ትናንትም፡ ዛሬም፡ እስከ ለዘላለምም ድረስ ብቁ ነው፡ ለዘመናት ሁሉ ጭምር፡ እያንዳንዱን ኃጢአተኛ ለማዳን፡ እያንዳንዱን የታመመ ሰው ለመፈወስ፡ እያንዳንዱን ተአምር ለማድረግ፡ እያንዳንዱን ምልክት ለመፈጸም ብቁ ነው። "ሰባት ጊዜ፡" ወደ ኋላ ወደ ብሉይ ኪዳን ተመልሰን፡ ከክርስቶስ መምጣት አሥራ አራት መቶ ዘጠና ዓመታት በፊት። አስቡት! ተምሣሌት፡ "ሰባት ጊዜ ይረጫል... "

**ስለ ሕዝቡም ኃጢአት-የሚሠዋውን መሥዋዕት፡ ፍየል ያርዳል... ደሙም** ወደ፡ **መጋረጃው ውስጥ... ያመጣዋል፡ በወይፈኑም ደም እንዳደረገ በፍየሉ ደም** ያደርጋል፡... **በመክደኛውም ላይና፡ በመክደኛውም ፊት ይረጨዋል፥**

**ስለ መቅደሱም ያስተስርይለታል፡ ከምን የተነሣ... ከ... ከእስራኤል ልጆች ርኩሰነት፡** ከመተላለፋቸውም **ከኃጢአታቸውም የተነሣ፥ እንዲሁም ለመገናኛውም ድንኳን ያደርጋል፡ በ—በርኩሰነታቸው መካከል ከእነርሱ ጋር** ለኖረች **ለመገናኛው ድንኳን ያደርጋል።**

104 ምኑ ላይ ነበር? "የምህረት መክደኛው።" አሁንስ የት አሉ? ታቦቱ ውስጥስ ምን ነበር? ሕጉ። ሕጉንም፡ ከትእዛዛት አንዲት መጣስ ማለት ያለ ምሕረት መሞት ነበር። ነገር ግን ምህረትን ማግኘት ስለምትችሉ፡ ደሙ በመሠዊያው ላይ ይቀመጥ ነበር። የምህረት መክደኛውን ይረጩታል። የስርየት መክደኛውም ተንበርክካችሁ ምሕረትን የምትለምኑበት መሠዊያ ነው። ሰዎች ተንበርክከው እግዚአብሔርን ምሕረት የሚጠሩበት፡ የጥንቱ-መሠዊያ ከቤተክርስቲያናችን እንዳይርቅ እግዚአብሔር ይጠብቀን። ምሕረትም፡ ከጌታ ከኢየሱስ ደም በነጻ የሚፈስ ባለጸጋ ነው። አሁን፡ ምህረት ማለት፡ ያ ነው። የምህረት መክደኛ ያ ነው።

105 እዚህ ላይ ግን የምህረት መክደኛው አለመሆኑን፡ ልብ በሉ፡ "መብረቆች እና ነጎድጓድ እና ድምፆች።" በምህረት ምንም መብረቅ እና ነጎድጓድ አይኖርምና። ይህ ፍርድ ነው።

106 ወደ ዘጸአት፡ ዘጸአት ምዕራፍ 19 እና 16ኛው ቁጥር እንሻገር። ኦሪት ዘጸአት፡ ዘጸአት ምዕራፍ 19 እና፡ በ16ኛው ቁጥር እንጀምር፦

**እንዲህም ሆነ...**

በደንብ አድምጡኝ... እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ በወረደ ጊዜ፥

**እንዲህም ሆነ በሦስተኛው ቀን በማለዳ ጊዜ፡ ነጐድጓድና**... መብረቅ፡ **ከባድም ደመና፡** እጅግም የበረታ **የቀንደ መለከት ድምጽ** በተራራው **ላይ ሆነ፥** (የመለከት ድምፅ ምንድን ነው? የመላእክት አለቃ ነው።) **ሕዝብ ሁሉ...** (አድምጡ!)... **በሰፈሩም የነበሩት ህዝብ ሁሉ... ተንቀጠቀጡ።**

107 "ፍርድ!" ዋው! ወደዚያ ተጉዘው ነበር እግዚአብሔርም እንዲጓዙ ጸጋ ሰጥቷቸው ነበር፡ ነገር ግን ህግ ተጠይቀዋል። እነሱን... እግዚአብሔር እርሱ በርሳቸው እንዲሆኑ ፈልጎ ነበር፡ እነርሱ ግን የእምነት ተቋም ሊሠሩ ፈለጉ፡ እግዚአብሔርን ከመከተል፡ እና በስልጣኑ ስር ከመኖር ይልቅ፡ በኃይሉ ችሎት

ስር ከመኖር ይልቅ ሊከራከሩበት የሚችሉት ነገር ተመኙ። ጸጋ ነብይን አቀረበላቸው፡ ጸጋ ስርየትን (በግን) ሰጣቸው፡ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ጸጋ አቀረበ፡ እነርሱ ግን ፍርድን ፈለጉ። ማድረግ የሚችሉትን ነገር ፈለጉ።

108 እግዚአብሔርም "እንድ ላይ ሰብስቧቸው፡ ምን እንደሆነ አሳውቃቸዋለሁ። ምን እንደሆነ አሳያቸዋለሁ፡" አለ። እንብቡ! ሰሙ! የመለከቱም ድምፅ ምድርን እስኪያናወጥ ድረስ እየበረታ ሄደ። ፍርድ ምን እንደሆነ ተመልከቱ። ያንን አልፈልግም። ምህረትን ስጠኝ!

109 [ወንድም ፍሬድ ሶትማን እንዲህ ተናገረ፡ "ወንድም ብራንሃም? "—እርታዒ።] እ... ["ወንድም ብራንሃም? "] ወዬ? ["መጨረሻውን ያነበብከው ቃል—ምን ነበር? "] ኦሪት ዘፀአት፡ እ—እ—19ኛው ምዕራፍ እና 16ኛው ቁጥር ነው፡ ወንድም ፍሬድ። ዘጸአት 19፡16።

110 አሁን 17ኛውን ቁጥር አስተውሉ፦

> **ሙሴም ሕዝቡን ከእግዚአብሔር... ጋር ለማገናኘት ከሰፈር አወጣቸው፥** (ኦህ፡ ማይ! በሰላም እንጂ፡ በዚያ መልኩ ከእርሱ ጋር መገናኘት አልፈልግም።) **ከተራራውም እግርጌ ቆሙ።** (ከኋላ።)

111 አስታውሱ፡ በተራራው ዙሪያ መስመሮች ተዘርግተው ነበር። ያንን ተራራ ላም ብትነካው እንኳ፡ እዚያው ትሞታለች፡ በእግዚአብሔር ፊት ልትመጣ አትችልም። እግዚአብሔርም... "ሙሴም ሕዝቡን አመጣቸው።"

112 አሁን፡ 18ኛው ቁጥር፡ ቀጣዩ ቁጥር፦

> **እግዚአብሔርም... በእሳት ስለ ወረደበት፡ የሲና ተራራ ሁሉ ይጤስ ነበር፥**... (እንደ ምድጃ እሳት ይነድ ነበር።)

113 በምን ወረደ? በእርያም ክብሩ ሳይሆን፡ በፍርዱ ቁጣ ነው።

> **... ከእርሱም እንደ እቶን ጢስ ያለ ጢስ ይወጣ ነበር፡** ተራራውም **ሁሉ እጅግ ይናወጥ ነበር።** (ወንድሜ ሆይ፡ በዚያ መገኘት አልፈልግም!)
>
> **የቀንደ መለከቱም** ድምፅ፡ **እጅግ በበረታና በጸና ጊዜ፡ ሙሴ** ተናገረ፡ **እግዚአብሔርም በድምፅ መለሰለት።** (ህዝቡ ሳይሆን፡ ሙሴ ተናገረ፡ እነርሱ'ማ እየተንቀጠቀጡ ነበር።)
>
> **እ—እግዚአብሔርም በሲና** ተራራ **ላይ፡ ወደ ተራራው ራስ ወረደ፥ እግዚአብሔርም ሙሴን ወደ** ተራራው **ራስ ጠራው፥ ሙሴም ወጣ።**
>
> **እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው፡ ውረድ፥ ሕዝቡንም አስጠንቅቃቸው፡ እግዚአብሔርን ለማየት ዳርቻውን እንዳያልፉ፡ ከእነርሱም ብዙ እንዳይጠፉ።**

114 [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—እርታዒ።] ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ጀርባ ተቀምጠው በልሳን በሚናገር ሰው፡ ወይም በመንፈስ በሚያሸበሽብ ሰው፡ ይሳለቃሉ፡ መንፈስ ቅዱስን ሰድበው፡ ለዘለአለም ይታተማሉ! "በመንፈስ ቅዱስ ላይ ቃል የሚናገር ሁሉ፡ በዚህ ዓለምም ሆነ በሚመጣው አይሰረይለትም።" አታፍጥጡበት! ተቀበሉት ወይም ራቁ!

115 ቅዱሱን ቃል ለቀቅ ብናደርገው ይሻላል። ቀሪውን፡ ራሳችሁ አንብቡት፡ እግዚአብሔር የተናገረውን ተመልከቱ። ሰዎቹም፡ "ሙሴ ሆይ፡ ከእንግዲህ፡ አንተ ተናገር። እግዚአብሔር እንዳይናገር! እንዲህ አይነቱ ጥያቄ ባናቀርብ ይሻለን ነበር።" አያችሁ? "ሙሴ ሆይ፡ አንተ ንገረን። እግዚአብሔር ከተናገረ እንሞታለን።" አያችሁ፡ እግዚአብሔር ማስተሰረያ አድርጓል።

116 አሁን፡ "የዙፋኑ ድምፅ።" በዚህ ዙፋን ላይ ልብ በሉ፡ "ከዙፋኑ ፊት ሰባቱ ከዋክብት ነበሩ፡" የከዋክብት ድምጽ። "ድምጾች፡" አያችሁ። እዚህ በራዕይ 4 ወይም፡ 5 ላይ፡ ተጨማሪ እናገኛለን፡ "ከዙፋኑም መብረቅ፡ ነጎድጓዶች፡ እና ድምጾች ወጣ።" **አንድ** ድምጽ ሳይሆን፡ ብዙ ቁጥር፡ **ድምጾች**። ምን ነበር? እግዚአብሔር በሰባቱ መናፍስት በኩል ራሱን እያንጸባረቀ፡ ለቤተክርስቲያን ሲናገር። እውነተኛው በእግዚአብሔር የተቀባ ሲናገር፡ የእግዚአብሔር ድምፅ ነው! አለመቀበል መቅረዙን ማስወገድ ነው። አያችሁ? "ድምጾች፡" የሰባቱ የቤተክርስቲያን ዘመን ድምጽ (ጥግ ላይ)፡ በነጎድጓድ እና በመብረቅ የሚናገሩ ድምፆች።

117 በአሁኑ ዘመንም እንዲሁ ናቸው፡ "አይ፡ እኛ ፑልፒት ላይ 'ሲኦል' ብሎ መናገር አናምንበትም።" አቤቱ፡ ማረን! እጅግ ያስለቻል! እምም! ወደ ኋላ የማይሉ፡ የእግዚአብሔር ሰዎች ያስፈልጉናል!

118 እንግዲህ፡ ሁሉም ሰው ሰባኪ መሆን አይችልም፡ ድምጽ ግን አላችሁ። ህዝቡን ሰብከት መሰበክ ካልቻልክ… ሰባኪ ከሆንክ፡ ለመሰበክ ወደ ፑልቢቱ ተጠርተሃል። ሰባኪ ባትሆንም፡ አሁንም ሰባኪ ነህ፡ ለህዝቡ በህያውነት **ኖረህ** ሰበካቸው። ስብከትህ ህያው **ኑሮ** ይሁን፡ ለማይቀበሉት ነቀፌታን የሚያመጣ የእግዚአብሔር ድምፅ ነው። እንዲህ ይበሉ፡ "በሱ ላይ ወይም በሷ ህይወት ላይ ማንም ጣቱን አይቀስርባትም። ደስ ይላሉ፡ ህያዋን… ናቸው… የእግዚአብሔር ሰው ከተባለ'ማ፡ ያ ሰው ወይም ያቺ ሴት ናት ይበሉ።" አያችሁ፡ ሰብከታችሁን ኑሩት። ሰባኪ ለመሆን ካልተጠራህ ለመሰበክ አትሞክር፥ እንዲሁ፡ ትቀላቅልባቸዋለህ፡ ታበላሽባቸዋለህ፡ ሳታውቀው፡ ሰዎች እንዲጠመዱ ታደርጋቸዋለህ… ይኸውልህ፡ አንተን ጨምሮ፡ እነርሱን እና ራስህን—ታፈርሳቸዋለህ። ዝም ብለህ ሰብከትህን ኑረው!

119 ሰባኪው እንዲሰብከው፡ እና እንዲኖረው ተጠርቷል። መኖር ካልቻላችሁ፡ መሰበካችሁን አቁሙ። ሰብከትህን እንድትኖረው ግን ይገባሃል።

120 እሺ፡ እዚህ ጋር "ድምጾች" ይላል። ኦህ፡ እዚህ ጀፈርሰንቪል ውስጥ ህያዋን ድምጾች እጅግ እንፈልጋለን፡ የእግዚአብሔር ነጐድጓድ በጣፋጭነትና በቅድስና፡ በንጽሕናም፡ ርኩሰ ባልሆነ ሕይወት፡ ዛሬ በምድር ላይ፡ ያለ ነውር የሚመላለሱ ያሻናል። አዎን፡ ዋዳጄ፡ እውነተኛ ክርስቲያን፡ ለጠላት እንደ ነጎድጓድ ነው። ዲያቢሎስ ምን ያህል ድምጽ ማሰማት እንደምትችል ግድ አይሰጠውም፥ ዲያቢሎስ ምን ያህል መዝለል ትችላለህ ወይም ምን ያህል **ይህን** ማድረግ ወይም መጮህ ትችላለህ አይጨንቀውም። ዲያብሎስን የሚጎስመው የተቀደሰ፡ ለእግዚአብሔር የተለየ ቅዱስ ህይወት ማየት ነው፥ በተቻላችሁ ኃይል መልካሞች በመሆን እየቀጠላችሁ፡ የወደዳችሁትን ነገር ተናገሩት፡ የሆነ ነገር በሉት። ኦህ፡ ማይ! የሚያሸቀነጥረው ያ ነው፡ ዲያብሎስን የሚያናውጠው ነጎድጓድ ያ ነው።

121 እንግዲህ፡ “መቼም፡” እንዲህ ትላላችሁ፡ “እንደ ቢሊ ግራሃም ወይም እንደ ኦራል ሮበርትስ፡ ወይም እንደ እከሌ፡ እንደ ተጽዕኖ ፈጣሪ መሰበክ ብችል ኖሮ፡ እንዲህ ይሆን ነበር... ” በጭራሽ፡ አይደለም! እንደውም አንዳንዴ ዲያብሎስ በዛ ላይ ይሰቃል። ከምንም በላይ አብልጦ ለዚያ ምንም ትኩረት አይሰጥም። ሁሉንም የሥነ መለኮት ዓይነት—የፈለከውን የሥነ መለኮት እና የሴሚናሪ ሥልጠና ቢኖራችሁም፡ ዲያቢሎስ ተቀምጦ ይስቅበታል። ህይወት ሲያይ ግን!

122 ደቀ መዛሙርቱን አስታውሷቸው፡ በሚጥል በሽታ ተይዞ የሚሰቃየውን ልጅ፡ እንዲህ አሉት፡ “አንተ ዲያብሎስ፡ ልቀቀው! ልቀቅ ከሱ፡ ዲያብሎስ! ልቀቅ ከሱ፡ ዲያብሎስ!”

123 ዲያብሎስ ተዝናንቶ ተቀምጦ፡ እንዲህ አላቸው፡ “አሁንስ፡ በራሳችሁ ላይ አታፍሩምን? ቆይ፡ የምታደርጉትን ታውቃላችሁን? ኢየሱስ አዘዛችሁ፡ ወጥታችሁ እንድትገስጹኝ፡ ተልዕኮ ሰጣችሁ። ማናችሁም ማድረግ ተሳናችሁ።”

124 ነገር ግን፡ ወንድሜ፡ ሲመጣ ባዩት ጊዜ ግን፡ አንደኛው ሰተት ብሎ ለቀቀ። ኧረ-ሃህ። ኦህ፡ ማይ! ምንም ማለት አላስፈለገውም። ዲያብሎስ ወድያውኑ ተንቀጠቀጠ። ህይወት ተገልጧልና፡ ወዲያው፡ መሄድ እንዳለበት ተረዳ፥ ስብከት ብቻ ሳይሆን፡ ሕይወትም ያስፈልጋል። “ከሱ ውጣ፡” አለው። ጉድ፡ ነው! ያደረገው ያ ነው! ወዲያውኑ፥ የሚናገረውን የሚያውቅ ነው፡ የሚሰራውንም ያውቃል።

125 “ድምጾች፡” ማለት፡ የሰባት ቀንደ መለከቶች ድምፅ፡ የሰባት ከዋክብት፡ የሰባቱ መልእክተኞች ድምፅ ነው። አሁን ግን እዚህ ተመልከቱ፦

… **በዙፋኑ… ም… .ፊት ሰባት የእሳት መብራቶች ይበሩ ነበር፡ እነርሱም ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት ናቸው።**

126 “ሰባት መብራቶች።” እስቲ አሁን ዙፋኑን፡ ቅድስት ሰፍራ፡ ጉባኤውን፡ ለመሳል እንሞክር። እና **እዚህ** ጋር (አንድ፡ ሁለት፡ ሶስት፡ አራት፡ አምስት፡ ስድስት፡ ሰባት) ሰባት ከዋክብት፡ ሰባት መብራቶች፡ ሰባት መልእክተኞች፡ ሰባት መናፍስት ነበሩ፥ በአጠቃላይ እግዚአብሔር ሰባት መናፍስት ነው ማለት አይደለም፡ ነገር ግን “ሰባት የአንድ መንፈስ ቅዱስ መገለጫዎች።”

127 መንፈስ ቅዱስ የት አለ? እዚህ በዙፋኑ ላይ፡ በእያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን ዘመን እየበራ ነው። **ይህ** የቤተ ክርስቲያን ዘመን **በዚህ** መንገድ እያንጸባረቀ ነው፡ የእግዚአብሔር ድምጽ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትም፡ ዛሬም፡ እና ለዘላለም ያው ነው። አያችሁ፡ ሰባት፡ “ድምጾች” ነበሩ። “ሰባት መብራቶችም ይበሩ ነበር፡” ሰባት መናፍስት፡ “እነዚህም ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት ናቸው።”

128 ከሁለት ሳምንታት በፊት፡ ስለ ትልቁ አልማዝ የተነጋገርነውን ታስታውሳላችሁ? ነገር ግን እሳቱን እና መብራቶቹን ለማንፀባረቅ በተለያየ መንገድ ይመታል ብለናል። መንገዱ ያ ነው፡ “ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ፍጥረት መጀመሪያ ነው፡” ራዕይ 1። ልክ ነው? ታዲያ አምላክ መቼ ተፈጠረ? እርሱ የእግዚአብሔር ፍጥረት መጀመሪያ ነው። እግዚአብሔርም ዘላለማዊ ነው። ልክ ነው? እግዚአብሔር ሲፈጠር ግን... በእናት ማኅፀን ውስጥ፡ በድንግልና የተፀነሰ ሕፃን በሆነ ጊዜ ነው። እናም ይህን ትንሽ ልጅ ለመውለድ እነዚህን ሴሎች በውስጧ ማዳበር ጀመረች፡ የእግዚአብሔር የፍጥረት

መጀመሪያ ያ ነበር፡ “እግዚአብሔር ሥጋ ሆነ በእኛም አደረ **አማኑኤልም** ተባለ፡ ‘እግዚአብሔር ከእኛ ጋር፡’ የእግዚአብሔር ፍጥረት መጀመሪያ።”

129 ከዚያም ከአፈር መካከል በወጣው በዚያ ታላቅ ዕንቍ ውስጥ… እሱ ከአፈር ሆኗልና። ልክ ነው? እንደ እኔ ምግብ በላ፡ እንደ እናንተም ምግብ ተመገበ። የትኛውም፡ የሰውነት አፈር፡ ካልሲየም፡ ፖታሽ፡ ፔትሮሊየም፡ ኮስሚክ ላይት ሆነ፡ በውስጡ ግን ዘላለማዊ ብርሃን አደረበት። ሰብአ ሰገሎች ኮከቡን “ወደ ፍጹም ብርሃንህ ምራን፡” ማለታቸው አያስገርምም።

130 እነሱም የሚያንጸባርቁት ብርሃን ፍጹም ከሆነው ብርሃን ነበርና። በዚያም እርሱ፡ የእግዚአብሔር ፍጥረት መጀመሪያ ሆኖ፡ ፍጹም የሆነ የእግዚአብሔር ብርሃን ነበረ። አሁን፡ እርሱ በዚያ ነበረ…

131 ሰብአ ሰገል በሰማይ ካዩት በኋላ፡ በዚህ ምድር ላይ የሚያገለግሉ መናፍስት ከሆኑ በኋላ፡ ራሱን ወደ ምድር ከዋክብቱ እንዴት ማንጸባረቅ ቻለ? “እርሱ ቆሰለ (ትልቁ አልማዝ፡ ተቆረጠ) ሰለ መተላለፋችን፡ ሰለ በደላችን ደቀቀ፡ የሰላማችን ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፡ በእርሱ ቍሰል እኛ ተፈወስን።” ምን እየሰራ ነበር? እያንጸባረቀ!

132 የእግዚአብሔር አገልጋይ ነኝ የሚል፡ መለኮታዊ ፈውስንና ኃይሉን የሚክድ ሰው፡ ብርሃኑን ከዚያ አልማዝ አይደለም፡ ብርሃኑን ከዚያ ዙፋን አይደለም። ምክንያቱም ትናንት፡ ዛሬ፡ እና ለዘላለም በሰባቱ ከዋክብት እና በሰባቱ የቤተ ክርስቲያን ዘመናት ውስጥ እያንጸባረቀ ነው።

133 ኧረ፡ እግዚአብሔር ይመስገን! አንድ አገልጋይ እግዚአብሄርን ከመድረክ ላይ ሆኖ በምስጋና፡ እና በምስጋና በክብር እና በኃይል ማምለክ ተገቢ እንደሆነ እወቁ። ኦህ፡ እንዴት ያለ እውነት ነው፡ በፊት ከነበርኩበት በውስጤ እኔን የለወጠኝ ነገር አለና፡ ጩኸ ጩኸ የሚል ነገር በነፍሴ ውስጥ ይሰማኛል፡ የቻልከውን ያህል ከፍ ብለህ ዝለል ሩጥም ይለኛል። መሆን በሚገባኝ፡ እና መሆን በምፈልገውን አልደረስኩም፡ ከነበርኩበት ሁኔታ እንደተለወጥኩ ግን አውቃለሁ። የሆነ ነገር ተከስቷል፡ የሆነ ነገር ሆኗል!

134 ቁሙ እና እያንዳንዱን ማዕበል የሚበግረውን ዘላለማዊውን ቃል እዩ! መጽሐፍ ቅዱሶችን እና ሁሉንም ነገር ለማቃጠል ሲሞክሩ፡ እንደ ወትሮው ሳይናወጥ ጸና፡ ምክንያቱ እንዲህ ተብሎ እንደተጻፈ፡ “ሰማይና ምድር ያልፋሉ፡ ቃሌ ግን አያልፍም።”

135 እዚህ ቺካጎ አቅራቢያ፡ በቤተ ክርስቲያን ፑልቢት ላይ የተቀመጠች መ—መጽሐፍ ቅዱስ አለች። ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በፊት፡ አንድ ሚሰዮናዊ ይዟት ነበርና አንድ ወዳጁ ጌታን ተቀበለ፡ ሚሰዮናዊውም መጽሐፍ ቅዱስ እንዲሰጠው ፈልጎ፡ እንዲህ አለው፡ “ይህንን እናቴ የሰጠችኝ ስለሆነ፡ ለአንተ ልሰጥህ አልችልም።” “ወደ ቤት በተመለስሁ፡ ጊዜ፡ አንድ እልክልሃለሁ፡” አለው።

136 በባሕር ማዶ መመለስ ጀመረ እና አንድ የጀርመን ሰርጓጅ መርከብ መጣና—መርከባቸውን አጋየው። ስብርባሪውን እንኳ ማግኘት አልተቻለም። እና ከሁለት አመት በኋላ፡ በባህር ዳርቻው ላይ፡ አንድ ሳጥን ሲንሳፈፍ አዩ። አንዳንዶቹ የሰመጠው ነገር ሊሆን ይችላል ብለው አሰቡ፡ በዚያም ሲያልፉ የነበሩ ሁለት ጓደኛሞች፡ ሳጥኑን ይዘው ከፈቱት። እና በዚያ ውስጥ፡ የተረፈው

ብቸኛው ነገር፡ ወደ ሚሰዮናዊው መልሶ የላከው መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነበር። ዛሬ እዚህ ቺካጎ አቅራቢያ በሚገኝ አንድ የሜቶዲስት ቤተክርስቲያን ውስጥ፡ መድረክ ላይ ተቀምጧል። "ሰማይና ምድር ያልፋሉ፡ ቃሌ ግን አያልፍም።"

137 በ1937፡ በነበረው በጎርፉ መጥለቅለቅ ወቅት፡ ይህች ምስኪን ቤተ ክርስቲያን፡ ወለሏ ሁሉ በጭቃ እና በሌላ በተጥለቀለቀ ጊዜ፡ በጀልባ እየቀዘፍን—በላይዋ ስንመላለስ ነበር። ጎርፉ ከፍ ብሎ ነበርና። እና፡ ታዲያ፡ ያን ቀን ማታ ላይ ወንጌል ከሰበክኩ በኋላ መጽሐፍ ቅዱሴን እንደተከፈተች ፑልፒቱ ላይ ትቼ ጎርፍ እንደሚመጣ ትንቢት ተናግሬ፡ ወደ ቤት ሄድኩኝ፡ "ስፕሪንግ ስትሪት ጎዳና አካባቢ ላይ ሀያ-ሁለት ጫማ ሲለካ አይቻለሁ፡" አልኳቸው።

138 ሽማግሌው ወንድም ጂም ዋይዝሃርት እና ሌሎቹ ሳቁብኝ። ያንን ታስታውሳለህ፡ ወንድም ጆርጅ? እንዲህ ሰል... እንዲህ—አለኝ፡ "ኦህ፡ ቢሊ፡ በ 84 ስፕሪንግ ስትሪት እንኳ የተመዘገበው ስድስት ኢንች ብቻ ነበር።"

139 እንዲህ አልኳቸው፡ "አንድ ሰው ከሰማይ ሲወርድ አየሁ፡ እና መስፈሪያ ዘንግ ይዞ በስፕሪንግ ስትሪት ላይ እንዲህ አጋድሞ፡ ሀያ-ሁለት ጫማ አለ።"

"አይ እንዲሁ ደስ ደስ ይሆናል፡" አለኝ።

እኔም፡ "ደስ ስላለኝ አይደለም! የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ነው!"

140 በስፕሪንግ ስትሪት ላይ ስንት ጫማ እንደነበረ ጠይቋቸው። ሃያ-ሁለት ጫማ በ—ኢንች! በትክክል።

141 በዚያች ሌሊትም የተሰበከባት ያች ያረጀች መጽሐፍ ቅዱስ... መዝነብ ጀመረ፡ ጎርፉ ጎረፈ ሌላም ሆነ፡ እና ይህች ቤተ ክርስቲያን... ወንበሮቹ በቀጥታ ወደ ጣሪያው ወጡ፡ መጽሐፍ ቅዱስ በቀጥታ ወደ ጣሪያው ወጣ፡ ከፍ እያለ የሚሄደውን ውኃ እየጠራረገው ወጣ። ፑልቢቱም በቀጥታ ወደ ላይ ተንሳፈፈ። እና ወደ ታች ወረዱ፡ እና እያንዳንዱ ወንበር በቦታው ተቀመጠ፡ መጽሐፍ ቅዱሱም በቦታው ተቀመጠ፡ በዚያ ሁሉ ውኃ፡ በነበረበት ምዕራፍ እና ስፍራ፡ እንደተከፈተ ተገኘ።

142 "ሰማይና ምድር ያልፋሉ፡ ቃሌ ግን አያልፍም።"

143 ያ መጽሐፍ ቅዱስ በጨዋማው ውኃ ውስጥ ለሁለት ዓመታት ያህል በውስጡ ያሉትን ቃላት እንኳ ሳያቆሽሽ እንዴት ተንሳፈፈ! የእግዚአብሔር ቃላት እውነተኞች ናቸው። ኣሜን።

144 አስታውሳለሁ ከዚያ በኋላ፡ ሽማግሌው ወንድም ጂም ዋይዝኸርት በዚህ በጣም ተደሰተ፡ እጁ ላይ ህመም በተሰማው ቁጥር... ሰባ-አምስት አመት ሲሞላው ችግር ገጥሞት ነበር፡ የሩዩማቲዝም በሽታ ያዘው። ህመሙ **እዚህ** ጋር ሲሰማው፡ ሮጦ መጽሐፍ ቅዱስን ይይዝና፡ ገልጦ፡ በሚያመው ቦታ ላይ ያደርገዋል፡ **እዚህ** ጋርም ደግሞ ያመዋል። አንድ ቀን ወደሱ ሄድኩና ብዙ መጽሐፍ ቅዱስ ላዩ ላይ አድርጓል እና ወንድም ጂምን ማየት አልቻልኩም፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ተሸፍኖ አገኘሁት! በቃ፡ "የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ነው!" አለኝ።

145 "ሰማይና ምድር ያልፋሉ፡ ቃሌ ግን አያልፍም።"

146 እየመጣ ሲጎበኘኝ የነበረ ሰው ነው ታስታውሱታላችሁ። ከቤተሰቡ መካከል እዚህ ማንም የለም። እኔም ትንሽ እረዳው ነበር፡ ታውቃላችሁ፡ ምክንያቱም ሽምግሎ ነበር፡ ገንዘብ ስለሚያስፈልገው ይመጣል። እናም... አንድ ቀን ወደ ካናዳ ለመሄድ፡ ከበር ገና ሰወጣ፡ ዞር አልኩና፡ እንዲህ አለኝ፡ “ቢሊ፡ ልጄ፡ በነዚህ ቀናት ውስጥ ተመልሰህ ስትመጣ አጎትህ ጂም ከአሁን በኋላ እዚህ መንገድ ላይ መምጣት አይችልም።” ለመጨረሻ ጊዜ ያኔ ነበር። ካናዳ በነበርኩበት ጊዜ፡ በቴሌግራም ሰማሁ፥ በእህት ሞርጋን እቅፍ ውስጥ ያን ጊዜ ሞተ። የልብ ድካም ነበረበት፡ እና ሮጠው ወደ ሆስፒታል ወሰዱት፡ ቀና ብሎ ካያት በኋላ ህይወቱ አለፈ።

147 እህት ማርጂ፡ ዛሬ ጠዋት እዚህ ናት? ብዙውን ጊዜ ትገባለች። ሁላችሁም ታውቃላችሁ። ከአስራ ሰባት ዓመታት በፊት በባፕቲስት ሆስፒታል ውስጥ በካንሰር በሽታ በሞት መዝገብ ከነበሩ ታላላቅ ኬዞች አንዷ ነበረች፡ የዛሬ አስራ ሰባት አመት፡ “በካንሰር ሞት አፋፍ፡” እንደነበረች የሚገልጽ ማሕደር በዚያ ሜዲካል ክሊኒክ ውስጥ አለ። በኖቢሎሽ አቬኑ 412፡ በዚያ ባለው ሆስፒታል በነርስነት እየሰራች ትገኛለች። ድንቅ ጸጋ፡ ሆይ፡ አስደናቂ!

148 የሉዊስቪል ጠበቃ፡ ጂም ቶም ሮበርትሰን፡ ጂም ቶምን ሁላችንም እናውቀዋለን። በዚህ መልእክት እንዲያምን ያደረገው ያ ነበር፡ እና ወደዚያም ሄደ። አባቱም በሆስፒታሉ ውስጥ ካሉት የስራ ኃላፊዎች አንዱ ነው። በካንሰር ለሞት ቀርባ እንደነበረች ለማረጋገጥ፡ ወደዚያ ሄደና ጥናት አደረገ፡ ተስፋ ተቆርጦባት ወደ ቤት እንደተመለሰች፡ እና ይሄኔ አብቅቶላት እደሞተች መሞቷን ተስፋ እንደሚያደርጉ ነገሩት። አባቱም እንዲሁ አረጋገጠለት፡ እውነትም ነውና። ጂም ቶምም እንዲህ አላቸው፡ “ውሸት ነው፡ ወደ እሷ ልወስዳችሁ እችላለሁ፡ አሁን እዚህ ተቀምጣለች” አላቸው።

149 ኦህ፡ ኦህ፡ እሱ—እውነተኛ አምላክ ነው፡ አይደለም ወይ? ስህተቶቻችንን ይቅር የሚል አምላክ ስለሆነ ደስ ይለኛል፡ እናንተስ? በፍጹም ልባችን እንድንወደው ያደርገናል።

150 ዙፋኖች፡ መብረቆች... ምንድን? “ሰባት መብራቶች፡” መብራቶች፡ ወይም ሰባት ከዋክብት “ሰባት መናፍስት፡” ይባላሉ፡ ማለት ሰ-... በሰባት የቤተክርስቲያን ዘመናት ስለ ሕዝቡ በሰባቱ የምሕረት መክደኛዎች ሰባት የመንፈስ ቅዱስ መገለጫዎች። እነሆ፡ ሰባት የምሕረት መክደኛዎች፡ ሰባት መክደኛዎች፡ ሰባት አብያተ ክርስቲያናት፡ ሰባት ኮከቦች፡ ሰባት መገለጫዎች፡ ሰባት መናፍስት፡ ሰባት መብራቶች። ኦህ፡ ማይ! እግዚአብሔር እንዴት ፍጹም ነው! በሁሉም...

151 በዚያ በመጽሐፍ ቅዱስ የቁጥር ቀመሮች ውስጥ ተቀምጧል፥ የመጽሐፍ ቅዱስ የቁጥር ቀመሮች በምድር ካለ ሁሉ ፍፁም ነገሮች ናቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ የቁጥር ቀመር ውስጥ፡ ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ ድረስ አንድ ጉድለት ልታገኙ አትችሉም። ሦስት ጥቅሶችን ከማንበባችሁ በፊት ስሕተት የማታገኙበት መጽሑፍ የለም፥ መጽሐፍ ቅዱስ ግን እንደዚያ አይደለም-...

152 በጌታ ጸሎት ላይ አንድ ሀረግ ለመጨመር ወይም አንዷን ለመቀነስ፡ ከሁለት መቶ ለሚበልጡ ዓመታት ሲሞክሩ ቆይተዋል። ፍጹም ነው! ተጨማሪ ማከል ወይም መቀነስ አይቻልም። ጸሎቱን ትንሽ የተሻለ እንደሚያደርጉ

እያሰቡ ነበር። አበጥረው **ይህን** ሊከቱበት፡ **ያም** እንዲጨምሩበት፡ ወይም **ይህ** ሊቀንሱበት ይሞክራሉ፡ ልክ አይመጣም። እያችሁ፡ ፍጹም ነው! የእግዚአብሔር አሰራሮች ሁሉ ፍጹም ናቸው።

153 ስለዚህ እኛ ደካሞች ሰንሆን፡ እንዲህ አለን፡ "እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ።" እንዴት መሆን እንችላለን? በክቡር በኢየሱስ ክርስቶስ ደም፡ እራሳችንን ረስተን በእርሱ ብቻ እንድንኖር ነው። ይኸው ነው። እንዴት ግሩም ድንቅ ነው!

154 እሺ 6ኛው ቁጥር አሁን፡ ከገባንበት። "ሰባት መብራቶች።"

> **በዙፋኑም ፊት... ብርሌ የሚመስል የብርጭቆ ባሕር ነበረ፥ በዙፋኑም መካከል፡ በዙፋኑም** ዙሪያ፡ **በፊትና በኋላ ዓይኖች የሞሉአቸው አራት እንስሶች ነበሩ።** (ድንቅ፡ ነው! ተመልከቱት!)... **በፊትና በኋላ ዓይኖች የሞሉአቸው—ዓይኖች የሞሉአቸው እንስሶች-...** (አሁን፡ ቆይ።)... **በዙፋኑም ፊት... ብርሌ የሚመስል የብርጭቆ ባሕር ነበረ፥ በዙፋኑም መካከል፡** አራት ነበሩ... **በዙፋኑ**... ዙሪያ፡ **በፊትና በኋላ ዓይኖች የሞሉአቸው አራት እንስሶች ነበሩ።**

155 አሁን፡ የ "ብርጭቆ ባህር።" እንግዲህ እናንተም... እኔም... ይህ እዚህ ጋር እንደ ተምሣሌት አይደለም፡ ብቻ ለአፍታ ያህል ላጥፋው። አሁን፡ አሁን እዚህ ጋር በጥቂቱ ጥናት ማድረግ እንፈልጋለን። የብርጭቆ ባሕር በጥንታዊው ቤተ መቅደስ ተመስሎ ይገኛል፡ ምክንያቱም ሙሴ በሰማያት እንዳየው አድርጎ በምድር ላይ ቤተ መቅደሱን እንዲሠራ በእግዚአብሔር ታዝዟል። ይህ ሁላችንም እናውቀዋለን። በጣም ጥሩ።

156 እስኪ አሁን አንዲት አነስ ያለች ነገር ልሳል፡ እንዲህ ልበል፡ ብሉይ ኪዳን ላይ ታቦቱ **እዚህ** ነበር፡ በጣም ጥሩ፡ ቀጣዩ ነገር፡ "ቅድስተ ቅዱሳን" ይባላል። እዚህ ጋር ቀጣዩ ሰፍራ ጋር መሰዊያ ነበር፡ "ቅድስት" ይባላል። **ከዚህ** ሰፍራ በፊት የሚገኘው ደግሞ "የናስ ባሕር፡" ይባላል። በሌላ አነጋገር፡ ይህ ቦታ መሰዋዕት... መሰዋዕቱ የሚታጠብበት ቦታ ነው—ገና በመሰዊያው ከመቀመጡ በፊት... እዚህ ጋር ታጥቦ፡ በናሱ መሰዊያ ላይ፡ ወይም መሰዋዕቱ በሚቀርብበት ከናስ በተሰራው መሰዊያ ላይ ይቀርባል።

157 አሁን፡ ይህ የት እንደሆነ ማየት... የት እንደሆነ ማየት እንፈልጋለን። እና፡ አሁን—አሁን፡ በዚህ የብርጭቆ ባህር... ከዙፋኑ እና ከቅድስት ፊት ነበር። ልክ... አሁን አስታውሱ፡ ሰባቱ የወርቅ መቅረዞች በዚህ በኩል **እንዲህ** ይቀመጣሉ፡ ከዚያም የመታጠቢያ ገንዳ ነበረ። እያችሁ? አሁን፡ ከቅድሰት **ወደዚህ** ወደ ውጪ ብርሃን የሚያንጸባርቀው ይህ ነው። እንግዲህ፡ ካልተሰማችሁ... ተዉት፡ ካልፈለጋችሁ በቀር መጻፍ አይጠበቅባችሁም፡ ይህ ግን... እኔ ራሴ የሳልኩት እናንተም እንድትረዱት የምፈልገው፡ የራሴ ሰዕል ይዣለሁ። አሁን ግን፡ እያችሁ፡ **ይህ** የናስ ባሕር ተብሎ ይጠራ ነበር፥ ያን ያህል ትልቅ አልነበረም፡ ይብዛም ይነስ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ባለው ሰፍራ ላይ ይቀመጣል። **በዚህ** በኩል ተቀምጦ የነበረው፡ የናስ ባሕር ነበር፡ መሥዋዕቱን የሚያጥቡበት ከናስ የተሠራ የመታጠቢያ ገንዳ ነበረ። መሥዋዕቱ ከመቃጠሉ ወይም ከመቅረቡ በፊት፡ መታጠብ ይኖርባቸዋል።

158 ኦህ፡ አሁን ከዚህ ውስጥ ሰብከት አይወጣውም ወይ፡ ዶክተር? ኦህ፡ ማይ! አይወጣውም ወይ—አይወጣውም ወይ… “መታጠባቸው፡” በጣም ነክቶኛል። ማንኛውም መሰዋዕት ወደ እግዚአብሔር ከመቅረቡ በፊት፡ መታጠብ አለበት። እንዴት? በስሜት ሳይሆን፡ በቃሉ ይታጠባል። አሁን፡ ወደ ኋላ ወደ አይሁዳዊው ራባይ መመለስ እንችላለን… ስለ መለየት ውኃ የሰበክኩ ጊዜ፡ ስለ ቀይ ጊደር፡ እሷን ስለሚጠብቃት ውኃ፡ የሚያዘጋጁት የመለየት ውኃ ነበረ። ስለዚህ በእውነተኛ እምነት ወደ እግዚአብሔር ከመቅረባችን በፊት፡ በመለየት ውሃ ማለፍ አለብን። አዎን፡ ወዳጄ። በምን ማለፍ አለባችሁ? በቃሉ።

159 ኦህ፡ እስኪ ምናልባት… ሁሉም ሰው እንዲረዳው በሚያስችል መንገድ ልናገር እሰቲ። አሁን፡ መንፈሳዊ አስተሳሰባችሁን ልበሱ። እዚህ ጋር አንዳች ነገር እያመጣን ስለሆነ፡ የጦርነት አሳባችሁን አውልቁና መንፈሳዊ አስተሳሰብ ልበሱ። “በመሠዊያው ላይ ተቀባይነት ከማግኘቱ በፊት ይታጠባል፡” አስቀድሞ መለየት ውኃ መታጠብ አለበት።

160 አሁን፡ በፍጥነት ከእኔ ጋር ወደ ኤፌሶን 5 ክፈቱ፡ ያላችሁበት ሳትለቁ፡ ወደ ኋላ ጥቂት ገጾች ተመለሱ፡ ወደ ኤፌሶን 5ኛው ምዕራፍ 26ኛው ቁጥር፦

> **በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት…** (የሚናገረው፡ ስለ ቤተክርስቲያን ነው።)

161 አሁን፡ አያችሁ፡ ከዚያ አለፍ ብዬ ወደ ኋላ ልመለስ። እየፈለጋችሁ ሳላችሁ፡ ወደ 21ኛው ቁጥር ተመለሱ፦

> **ለእያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሃት** የተገዛችሁ ሁኑ።

162 “የተገዛችሁ ሁኑ።” ጉባኤ ሆይ፡ ለፓስተራችሁ የተገዛችሁ ሁኑ። ፓስተር ሆይ፡ ለጉባኤህ የተገዛህ ሁን። ቡድን መሆን ከተጀመረ፡ በሁለቱም በኩል አትወግኑ፡ እራሳችሁን ለጉባኤው ሁሉ የተገዛችሁ ሁኑ። ጉባኤ ሆይ፡ ብዱናዊነት ከጀመራችሁ፡ በእግዚአብሔር ፍርሃት ለፓስተራችሁ የተገዛችሁ ሁኑ። አያችሁ? ኦህ፡ ወንድሜ ሆይ! እህም!

> **ሚስቶች ሆይ፡ ለጌታ እንደምትገዙ፡** ለባሎቻችሁ **ተገዙ፡** (እርሱ ጌታችሁ ነውና።)

163 እናንተ ሴቶች፡ ይህን ስንቶቻችሁ ታውቃላችሁ? ትክክል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያ እንዲሁ ይላልና። አሁንም ተመሳሳይ ነው።

> **ሚስቶች ሆይ፡ ለጌታ እንደምትገዙ፡** ለባሎቻችሁ ተገዙ።
>
> **ክርስቶስ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደ ሆነ፡ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደ ሆነ፥ ባል የሚስት ራስ ነውና።**

164 ባልም እንዲሁ። ያገባችሁ ሰዎች እና ጎልማሶች፡ ወይም የህይወት መንገድን ለማወቅ የደረሳችሁ ልጆች፡ ሁላችሁም ይህን እውቁ። መልካም።

> **… ለጌታ እንደምትገዙ።**
>
> **ክርስቶስ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደ ሆነ፡ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደ ሆነ፥ ባል የሚስት ራስ ነውና።**

**እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ፡ እንዲሁ ሚስቶች ደግሞ በሁሉ ለባሎቻቸው ይገዙ።**

**ባሎች ሆይ፡ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት፡ ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ እንደ ሰጠ፡ ሚስቶቻችሁን ውደዱ፥** (አታንገላታት! እንዲህ ካደረግህ፡ ባል ለመሆን አትበቃም። ልክ ነው!)

**እንዲቀድሳት...**

አሁን፡ ልብ በሉ! ተረዱት፥

**በውኃ መታጠብና** ከምኑ **ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት...** [ጉባኤው "**ከቃሉ**፡" አለ።—አርታዒ።] እህም!

165 ስለዚህ፡ መሰዋዕቱን ይዞ ውደዚህ ለመግባት ዕድል ያገኘ **ሁሉ** በቃሉ በኩል ማለፍ አለበት። በሌላ መንገድ ለመግባት የሞከሩ ብዙዎች ነበሩ። እኔም በአጫጭር ታሪኮች እና መሰል ነገሮች የማምን ሰው ነኝ፡ ለምሳሌ "ከብዙ ዓመታት በፊት የሞተች እናትህ በገነት ውስጥ አንተን እየጠበቀች ናት፡" እንዲህ አይነቱ ነገር ቃሉን ከታዘዙ **በኋላ** ከሆነ ልክ ነው። ብዙ ሰዎች እናታቸውን በገነት ማግኘት ፈልገው ወደ መሰውያው ይመጣሉ። ያም ይሁን፡ ችግር የለው፡ ነገር ግን ወደ መሠዊያው የምትመጡበት ምክንያት ይህ አይደለም። ክርስቶስ ለእናንተ ስለ ሞተላችሁ፡ ኃጢአቶቻችሁ እየተናዘዛችሁ ወደ መሠዊያው ትመጣላችሁ!

166 ስለዚህ፡ በቃሉ መሰረት የማይመጣ ማንኛውም መሰዋዕትነት ተቀባይነት የለውም። ልክ ነው? (ኦህ፡ ወንድሜ ሆይ፡ ይህን ማለቴ አዝናለሁ። ኦህ፡ ማለቴ ያሳዝነኛል። እንዲህ ማለቴ ይቅርታ አርጉልኝ።) ለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ በሐዋርያት ሥራ 19 እንዲህ የሚለው፡ "ካመናችሁ ወዲህ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን? "

እነርሱም አሉ፡ "እኛስ... መኖሩን እንኳ አልሰማንም... "

አላቸውም፡ "እንኪያስ፡ በምን ተጠመቃችሁ? ወደዚህ እንዴት አልገባችሁም? "

167 ከቃሉ ውጪ በሌላ መንገድ መጡ! "ኦህ፡ በፎርሙላው በኩል አልፈን፡ በዮሐንስ... ተጠመቅን፡" አሉት።

"ያ አይሰራም። ዮሐንስ ያጠመቀው ለንስሐ ብቻ ነው፡ ለኃጢአት ሥርየት አይደለም፡" አላቸው።

168 ይህንም በሰሙ ጊዜ፡ ዳግመኛ ተጠመቁ። እንዴት? በቃሉ! "በቃሉ ውሃ ታጠቡ።" ቃሉ ሲናገር፡ "ከኢየሱስ ክርስቶስ ስም!" በቀር የሚጨመር ማንኛውም ነገር ውሸት ነው!

169 አሁን፡ ውድ ወንድሜ ሆይ፡ ይህ ካሴት እንደሆነ አውቃለሁ። አሁን፡ አትደነቅ። በአምላካዊ ፍቅር ይህን እላለሁና፡ ከእንግዲህ ወዲህ እነዚህን ነገሮች ማካሄድ የማልችልባት ሰዓት ደርሳለች፡ መምጣቱ በደጅ ነው። እየህ? የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል! "ሥላሴአዊነት ከዲያብሎስ ነው!" ከየት እንደመጣ ልብ በሉ። ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መሪ ከነበረችበት ከኒቂያው ጉባኤ የመጣ ነው። "ሥላሴ" የሚለው ቃል በራሱ በመላው የመጽሐፍ ቅዱስ

መጽሐፍት ውስጥ እንኳን አልተጠቀሰም። ስለ **ሦስት** አማልክት ካላችሁም፡ ከገሀነም ነው። አንድ አምላክ ብቻ አለና። ይህ ትክክል ነው።

170 ታዲያ፡ እንዲህ እያልክ ነውን፡ "የሥላሴ እምነት ተከታዮች ሁሉ——የገሀነም ናቸውን? " አይደሉም፡ ወዳጄ። ክርስቲያኖች መሆናቸውን አምናለሁ። ይሁን እንጂ፡ ወንድሜ ሆይ፡ በቅንነት የሚሰቱባት ሰዓት አሁን ቀርባለች።

171 በዚህ ርዕሰ ጉዳዩ ላይ፡ ለመነጋገር የሚፈልግ ማንኛውም ሰው፡ ማንኛውም አገልጋይ፡ ቢሾፕ ይሁን፡ አርክ ቢሾፕ፥ ምንም ሁን ማንም፡ በየትኛውም ቦታ፡ በማንኛውም ጊዜ፡ ወደ እኔ ይምጣና ይነጋገር። ይህም በካሴት እየተቀዳ ነው፡ በዓለም ዙርያ ሁሉ ይሰራጫል። በአለም ዙሪያ በዚህ ካሴት ላይ ለሚሰማኝ ሰው ሁሉ፡ በወንድማማች ፍቅር እጠይቃለሁ፡ ወደ እኔ ይመጣና ከቅዱሳት መጻሕፍት ወይም በማንኛውም ታሪክ ውስጥ (ከትክክለኛው የታሪክ መዝገብ) ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጋር ድርጅት እስከሆኑባት ቀን ድረስ በ "አብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስ" ስም የተጠመቀ አንድም ሰው ካለ አንድ አንቀጽ ያሳየኝ፡ ትምህርቴን እቀይራለሁ። ሰው ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቀ! ውድ ወንድሞቼ ሆይ፡ ዓይኖቻችሁ ለእነዚያ ነገሮች ታውረዋል። እግዚአብሔር ብርሃን እንዲሰጣችሁ ጸልዩ!

172 እንግዲህ፡ ይህን የሚደግፉ ቅዱሳት መጻሕፍት ካላችሁ፡ ስልክ ጠሪአችሁን ለመስማት እጠባበቃለሁ። እናንተ... እናንተ... ከዚህ ቅጂ ውጪ የምትኖሩ ሁላችሁ፡ በዚህ ነገር ላይ እኔን መሞገት ካልቻላችሁ በገዛ ፈቃዳችሁ በመንፈሳዊ ድንቁርና ስር እየኖራችሁ ነው። ብርሃን እና ጨለማ ምን እንደሆነ ለማወቅ ከፈለጋችሁ፡ እግዚአብሔርን እንጠይቅ። የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር ይላል ማለቴን፡ አስታውሱ! የእርሱ አገልጋይ እንደሆንኩ ካመናችሁ... እና ያ በቃሉ መሰረት ባይሆን፡ ስህተት ይሆን ነበር። እንግዲህ እንደ ቃሉ ካልሆነ፡ እኔን የማቃናት የእናንተ ግዴታ ነው፡ ኧሃ-ሃህ፡ ምን እንደሆነ እዩ። ኡኧሃ-ሃህ። ስህተት ነው!

173 በሶስት አማልክት የሚያምኑ ብዙ ሺህ የሥላሴ አማኞች ድነዋል ብዬ አምናለሁ፡ ምክንያቱም ልዩነቱን አያውቁትምና። በመልእክቱ ውስጥ ወደዚያ እንሄዳለን።

174 አሁን፡ እናንተ ይሥላሴ እምነት ተከታዮች ወንድሞቼ ሆይ፡ ካሴታችሁን ዘግታችሁ እንዳትወጡ፡ ይህን ሰሙኝ። ለጥቂት ደቂቃዎች አርፋችሁ ተቀመጡ። ለራሳችሁ ዕዳ አለባችሁ። ለጉባኤያችሁ ዕዳ አለባችሁ። እሺ? ካሴቶቹን መቅዳታችሁን አታቁሙ፡ ያዟቸው። በቃሉ ላይ መርምራችሁ እውነት እንደሆነ ተረዱ። መጽሐፍ ቅዱስ "ሁሉን ፈትኑ፡" ይላልና።

175 በብዙ እንደሚነቀፍ አውቃለሁ፡ ኢየሱስም እንዲሁ ነበርና፡ መልእክቱም፡ ሁሌ እንዲሁ ይሆናል። መጥቼ በመካከላችሁ ያሉትን ድውያንንና የተጨነቁትን ስፈውስ ወደዳችሁኝ፡ እንዴት ድንቅ ነው ብላችሁ አሰባችሁ፡ ታላቅ ጉባኤ እና ቤተ ክርስቲያን አቆማችሁ። ይኸውላችሁ፡ ኢየሱስም አንድ ቀን እውነቱን ማፍረጥ እስኪጀምር ድረስ ተመሣሣይ ነገር አደረገ። ባፈረጠው ጊዜ ግን፡ ሰባዎቹ ተለዩት። ወደ ሌሎቹም፡ ወደ አሥራ ሁለቱ ዘወር ብሎ፡ "እናንተስ መሄድ ትፈልጋላችሁን፡" አላቸው?

ጴጥሮስም ይህን ድንቅ ቃል ተናገረ፡ “ጌታ ሆይ፡ ቃልህ ብቻ ዘላለማዊ ነውና፡ ወደ ማን እንሄዳለን? ”

176 የእግዚአብሔር ቃል ብቻውን ዘላለማዊ ነው! ስለዚህ እግዚአብሔር በ “አባት፡ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ” ስም ያስጠመቀበት እንዲት ስፍራ አሳዩኝ።

177 ማቴዎስ 28:19 ክፈቱ፡ “አባት፡ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ፡” ማቴዎስ የተናገረው፡ “እንግዲህ ሂዱና፡ ሕዝቦችን ሁሉ፡ በአባት፡ በልጅ፡ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው”? “አባት፡ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ” ስም ነው ብሎ የሚያስብ ማንም ሰው ካለ፡ በትምህርቱ ላይ የሆነ ችግር እንዳለ ያሳያል። (እንግዲህ፡ **ይህን** እያዳመጡ ላሉ ጳጳሳት እየተናገረ ያለው ሰው ሰባተኛ-ክፍል ተማሪ ነው።) **አባት** ስም አይደለም፡ **ልጅ** ስም አይደለም፡ **መንፈስ ቅዱስም** ስም አይደለም። “የአባት፡ የልጅና፡ የመንፈስ ቅዱስ) ለሆነው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ለተባለው **ስም** እንደ **መገለጫዎች** ናቸው።

178 በፍቅር፡ እና በአምላካዊ አክብሮት እናገራለሁ እንጂ፡ በቁጣ አለመናገሬን አትርሱ፡ በሥላሴ አማኞች ወንድሞቼ መካከል ወደሚጠሩኝ ሁሉ ግምት ውስጥ በማስገባት ለክርስቶስ አካል በሙሉ በፍቅር መጥቼ በጉባኤያቸው እንድሰብክላቸው ለሚጠሩኝ (በመላው ዓለም ላሉ ሁሉ) ነው። መካከላችሁ ሳለሁ በፍጹም አልጠቅሰውም። እኔ የምፈልገው... እራሳችሁ ካልጠየቃችሁኝ በስተቀር፡ አብሬአችሁ ወደ ሰብከት እሄዳለሁ ከእናንተም ጋር እነጋገራለሁ። በጉባኤያችሁ ፊት ግን፡ ያናውጣቸዋል። መገለጡን ተቀብላችሁ መንጋችሁን የማስተማር ኃላፊነት የራሳችሁ ነው፡ የመንጋው እረኞች እናንተ ናችሁ። አገልጋዮች ለሆናችሁ እናገራለሁ። ካልገባችሁ፡ ኑና፡ ተቀምጠን እንወያይ። መጽሐፍ ቅዱስ “ሁሉን ፈትኑ፡ መልካሙንም ያዙ፡” ይላልና።

179 “የብርጭቆው ባሕር፡” መሰዋዕቱ የሚታጠብበት ስፍራ... እኛም ታጥበናል... ኦህ፡ ከአፍታ በኋላ እንመለሰበታለንና፡ ይህን አትርሱ፡ “በቃሉ ውኃ ታጥበን።” ከዚያ ከመግባታችሁ በፊት ቃሉን መሰማት አለባችሁ፡ ምክንያቱም ወደ እግዚአብሔር መቅረብ የሚቻልበት ብቸኛው መንገድ፡ በእምነት ነው። ልክ ነው? “እምነት ከመሰማት ነው፡ የቃሉን መሰማት፡” ሕሊናችንን በማጠብ። ሰው ለማግኘት አይደለም፡ አባትን ለማግኘት አይደለም፡ እናትን ለማግኘትም አይደለም፡ ቤቢን ለማግኘት አይደለም (በርግጥ ልክ ነው፡ እነዚህም ሁሉ እናደርጋቸዋለን)፡ ነገር ግን ከሁሉ በፊት የምንመጣው የእግዚአብሔር መገኛ ወደሆነው አጸድ ነው፥ የእግዚአብሔርን ቃል ሰንሰማ እንታጠባለን።

180 በእምነት እንጓዛለን። “እግዚአብሔር ያደረገላችሁ፡” **ጸጋ** ነው። ይህ ትክክል ነው። እግዚአብሔርን እመኑ፡ በእግዚአብሔር ታመኑ፥ በተጸጸታችሁ ቅጽበት፡ ይቅርታን አግኝታችኋል።

181 ትናንት ከአንድ ወንድም ጋር ሰንነጋገር፡ ነገሩን ቀላቀለውና፡ እንዲህ አልኩት፡ “ተመልከት፡ ወንድሜ፡ የሚሰትህን ስሜት የሚጎዳ ነገር ከተናገርክ፡ ወዲያው ታዝንላታለህ፡ ያን በማድረግህ ትጸጸታለህ፡ ያን ጊዜ በልብህ ንስሓ ገብተሃል። ትክክል ነው። ግን ሄደህ ስለጉዳዩ ልታናግራት ይገባሃል። ሄደህ እንዲህ ማለት አለብ፡ ‘ማር፡ ይህን በማለቴ ይቅርታ አ—አርጊልኝ።’ ያን ጊዜ ሙሉ በሙሉ ንስሐ ገብተሃል።” እንግዲህ፡ በእግዚአብሔር ዘንድ እንደዛ ነው።

182 ሄዶ እንዲህ የሚናገር ሰው፡ “ስሜቷን ጎድቻታለሁ፡ ምንም ለውጥ አለው፡ ይቅርታ እላታለሁ፡ ከውስጤ ግን ምንም አይመስለኝም የሚል ሰው፡” ግብዝ ነው። እያችሁ? ትክክል ነው። ያ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የለውም።

183 ስለ ኃጢአትህ ከልብህ ሊሰማህ ይገባል። ስለ ኃጢአትህ ይቅርታ ማለትህ ስታውቅ፡ ያን ጊዜ “ንስሓ ግቡ፡ ስለ ኃጢአቶቻችሁ ስርየት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፡ ይቅርታን ትቀበላላችሁ፡ መንፈስ ቅዱስን ትቀበላላችሁ።” እያችሁ፡ እጅግ ቀላል ነው፡ እግዚአብሔር ቀላል አድርጎታል።

184 እዚህ ጋር... እዚህ “ብርጭቆው ባሕር” ውስጥ፡ በብርሌ ተምሣሌት ሲመስል አይተነዋል። ስለዚህ፡ ይህ የብርጭቆው ባህር በናስ ባህር ተመስሎ፡ ተምሣሌታዊ ነው። ይህም በገነት ውስጥ ያለው፡ የብርጭቆ ባህር ነው። ሙሴ እንደ ብርጭቆ ባህር ሆኖ አየው “የናስ ባሕር” አድርጎ ሰራው፡ የነሐስ መሠዊያ፡ የነሐስ መሥዋዕት... የነሐስ መሠዊያ፡ ማለቴ ነው።

185 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ናስ የምን ተምሣሌት እንደሆነ ታውቃላችሁ? የፍርድ። የናሱን እባብ ሠራ። **እባብ** ማለት ምን ማለት ነው? **የእባብ** ምልክት ትርጉሙ “ኃጢአት አስቀድሞ ተፈርዶበታል ነው፡” በኤደን ገነት ውስጥ፡ “እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፥ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ፡” በተባለ ጊዜ ተፈረደበት።

186 ከነሐስ የተሰራው፡ መሰዋዕቱ የሚቃጠልበት **ናስም** “የመለኮታዊ ፍርድ፡” ተምሣሌት ነው፥ ከነሐስ የተሰራ መታጠቢያ ገንዳ፡ ማለት በቃሉ ውኃ የሚታጠቡበት ነው። እያችሁ? ኤ-... ኤልያስ፡ በዘመኑ፡ ወጥቶ ወደ ሰማይ አይቶ፡ “ሰማዩ ናስ መስሏል፡” አለ። (በተጣለ ህዝብ ላይ የወረደ መለኮታዊ ፍርድ።) ኦህ፡ ማይ! ናስ፡ ነሐስ!

187 አሁን “መታጠቢያ ገንዳ” ላይ ነን። እና ይህ መታጠቢያ ገንዳ ባዶ እና ንጹሕ እንደ ብርሌ እንደነበረ አይተናል። ለምን? ቤተክርስቲያኑ ቀድሞውኑ ተዋጅታ ነበርና!

188 አሁን፡ አሁን፡ ከጥቂት ቆይታ በኋላ፡ ከመከራ የሚወጡ ቅዱሳን ሲመጡ ግን፡ የሆነ ነገር እናስተውላለን፡ እንደገና በእሳት ተሞልቶ እናገኘዋለን። ታውቃላችሁ... ያንን ማንበብ ትፈልጋላችሁ? አሁን ወደ ራዕይ፡ 15ኛው ምዕራፍ፡ 2ኛው ቁጥር እንሂድ፡ እና ይህን የነሐስ እሳት እንደገና የምናይበትን እናነባለን። እሺ፦

> **ሌላም ታላቅና ድንቅ** ምልክት... **በሰማይ አየሁ፡** (ልክ ነው።) **የእግዚአብሔር ቍጣ፡ በእነርሱ ስለሚፈጸም... ኋለኛዎቹን ሰባት መቅሠፍቶች** የያዙ፥ **ሰባት መላእክት ታዩ።**

አሁን የእግዚአብሔር “ቁጣ።” ተከታተሉ፦

> **በእሳትም የተቀላቀለውን የብርጭቆ ባሕር** የሚመስለውን **አየሁ፥** (አሁን፡ ተከታተሉ።) **በአውሬውና፡** በ**ምስሉም፡ በሰሙም ቍጥር ላይ ድል ነሥተው** የነበሩት፡ **የእግዚአብሔርን በገና ይዘው... በብርጭቆ ባሕር ላይ፡** ሲቆሙ **አየሁ።**
>
> **የእግዚአብሔር ባሪያ የሙሴንም ቅኔ...** ዘመሩ፡

189 ኦህ፡ አያችሁት? “የመከራ ዘመን።” ኦህ፡ ቸኩላችኋል እንዴ? [ጉባኤው “አልቸኮልንም፡” ብለው መለሱ።—አርታዒ።] በጣም ጥሩ፡ ሰሙኝ፡ እዚህ ጋር አንድ ነገር ልብ እንበል።

190 እንዴት እንቀርባለን? እኛ (ይህች የአህዛብ ቤተክርስቲያን) የምንቀርበው በዚህ ቃል፡ ብርጭቆ ባሕር፡ ውኃ፡ የቃሉ ውኃ (ልክ ነው?)፡ ቃሉን እና የተጻፈበትን እንድምታ ማወቅ። ያን ጊዜ በዘመኑ ብርሃን እያንጸባረቀ፡ መሰዋዕቱ ከውስጥ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሆኖ ተቀባይነት ያገኛል። ከዚህም... ከዚህ ከቅድሰት ሰፍራ **ወደዚህ** ይወጣል፡ ከኮከቡ **ወደዚህ** ይወጣል። ገባችሁ?

191 ልብ በሉ፡ አሁን፡ በዚህ ዘመን መጨረሻ፡ ዮሐንስ፡ የናሱን ባሕር ባየ ጊዜ፡ “እንደ ብርሌ ግልጽ” ነበረ። ምን ነበር? ቃሉ ከምድር ተወሰደ፡ በቤተክርስቲያን ተነጠቀ፡ “እንደ ብርሌም ንጹሕ” ነበረ፡ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ሰላበቃ፡ ከእንግዲህ ደም አልነበረበትም።

192 አሁን፡ በራዕይ 15 ላይ፡ የሴቲቱ ዘር ቅሪት እናያለን፡ እነዚህም በመከራ ያለፉትን የመከራው ቅዱሳን ናቸው፡ የት ነበሩ (ተመልከቱ!) በባሕሩ ላይ ቆመው ነበር። በእሳት፡ በደም፡ በሚንበለበል በእግዚአብሔር ቀይ እሳት፡ የተሞላ ነበር። በአውሬው (በሮም) ላይ፡ በቁጥሩ ላይ፡ በሰሙ ፊደል ላይ ድልን ነሰተው ነበር፡ እንዲሁም በምስሉ (ኢብያተ ክርስቲያናት ካውንስን)፡ ድል ነሰተው የወጡ ናቸው። እነርሱን ለማውጣት ወደ እሰራኤል በሚገለጡ በሁለቱ ነብያት፡ በሙሴ እና በኤልያስ ሰብከት... እነዚህ ወገኖች፡ ማለት ከመከራው ዘመን የወጡ ቅዱሳን፡ በዚያ ዘመን እንዲገቡ የሚደረጉ፡ እነዚህ...

193 እዩ፡ ቤተክርስቲያኑ አሁን ተነጠቀች፡ ሚስት ግን በዙፋኑ ላይ እንዳለች አስታውሱ። በመከራው ዘመን... በመንግሥታት ውስጥ የሚኖሩ ሁሉ፡ እየወጡ፡ ንጉሣቻቸውን ሁሉ ክብራቸውንና ግርማቸው ወደ ከተማይቱ ያመጣሉ። ወደ ራዕይ 22 ሰንደርሰ፡ ታዩታላችሁ። ማስታወሻ እየጻፋችሁ ከሆናችሁ፡ ወደዚያ ሰንደርሰ ምን ማለታችን እንደሆነ ታያላችሁ። እያንዳንዷን ጥቃቅን ነገር ለማየት እና ወደ ላይ ወደ ታች እየተመላለሰን ለመተንተን ጊዜ ያጥርብናል፡ ከፍ ከፍ ያሉትን ግን እንዳሰሳለን። ከዚያ በኋላ፡ ምናልባት አንድ ቀን፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ ስለእሱ ለመነጋገር ብዙ ጊዜ ይኖረናል።

194 እንግዲህ፡ እነዚህ ከመከራው ዘመን የመጡ ቅዱሳን፡ በታላቅ መከራዎች ውስጥ አልፈዋል። (ቤተ ክርስቲያን በመከራ ውስጥ አታልፍም! አስቀድመው ወደ ክብር መወሰዳቸውን አይታችኋል?) እና እነዚህ ከመከራው የሚመጡ፡ ተቀድሰው የሚወጡ ቅዱሳን... በእኔ እና በእናንተ ጥፋት ቃሉን ሰምተው አያውቁም ነበር። ሰምተውት ቢሆን ቢክዱት፡ ወደ ገሃነም ይሄዳሉ፥ ቃሉን ጠልተዋልና በውጭ ወዳለው ጨለማ በተጣሉ ነበር። ፈጽሞ ባይሰሙት ግን፡ የመከራ ጊዜ ስለደረሰባቸው ነውና፡ እግዚአብሔር ጻድቅ ነው።

195 አሁን፡ አንድ ደቂቃ ብቻ አስተውሉ። በአንዱ ቃል የታጠቡ ቅዱሳን ናቸው፡ ምክንያቱ መሰውያውም ያው ነው፡ ተመሳሳይ የብርጭቆ ባህር እና ተመሳሳይ ቃል ነው። ራእይ 2፡5፣ ራእይ 15፥ (ማለቴ) ፥ከ 2 እስከ ፥5። አንዴ፡ ልብ በሉ። አሁን፡ እነርሱ እነዚያ እንዲሆኑ የቻለበት ምክንያት፡ ቃሉን ወደ እነርሱ—አድርሰንላቸው ሰለማናውቅ ነው። ቃሉን ፈጽመን ወደ እነርሱ አድርሰንላቸው እናውቅምና፡ ስለዚህም ተጠያቂ እንሆናለን። ስለዚህ ሁሉንም ህዝቦች መድረሰ

አንችልም፡ (በዚህ ዘመን) እውነቱን የያዘች ቤተ ክርስቲያን አትችልም። ምክንያቱም እነርሱም በመከራው ውስጥ ያልፋሉ፡ እነዚህ በቤተ ክርስቲያን ዘመናት የሞቱት ቅዱሳን አይደሉም፡ ምክንያቱ “ከታላቁ መከራ የወጡ ናቸው፡” ይላቸዋልና፡ ታላቁ መከራም ቤተ ክርስቲያን ወደ ቤት ከተወሰደች በኋላ፡ ወደፊት የሚመጣ ዘመን ነው።

196 ኦህ፡ ይኸውላችሁ እንግዲህ! ኦህ፡ ደስ ይለኛል! ሰሙ! ትንሽ ወደ ፊት እንቀጥል፡ ምን ዓይነት ቃል እንደሰሙ ማየት እፈልጋለሁ። አሁን፡ በ15ኛው ምዕራፍ 2ኛ ቁጥር ላይ እንደገና እንጀምር።

> **በእሳትም የተቀላቀለውን የብርጭቆ ባሕር** የሚመስለውን **አየሁ፥ በአውሬውና:... በምስሉም:... በስሙም ቊጥር ላይ:... ድል ነሥተው የነበሩት፡ የእግዚአብሔርን በገና፡ ይዘው... በብርጭቆ ባሕር ላይ** ሲቆሙ **አየሁ።**

197 አሁን፡ ተመልከቱ፡ ቃሉን ሰምተው ነበር እንጂ፡ ገና አልገቡም ነበር። ቃሉን ግን ሰምተዋል። አሁን፡ ሰሙኝ፡ ምን አይነት አስተምህሮ ሰምተው እንደነበር ተመልከቱ፡ አሁን ካለችው ቤተ ክርቲያን የሚነጻጸር ከሆነ እስኪ እንየው።

> **የእግዚአብሔር ባሪያ የሙሴንም** ቅኔ፡ (ይህም፡ ሙሴ ከተሻገረ በኋላ ነው።) **ሁሉን የምትገዛ ጌታ አምላክ ሆይ፥ ሥራህ ታላቅና ድንቅ ነው፡ እያሉ፡ የበጉ ቅኔ ዘመሩ፥** (በጉ ማን ነው? ) **ሁሉን ቻይ የሆንከው፥ የቅዱሳን ንጉሥ ሆይ፡ መንገድህ ጻድቅና እውነተኛ ነው።**

198 ምን እንደሆነ ሲያውቁት አያችሁ? የሥላሴ ሦስተኛው አካል ሳይሆን፡ “ሁሉን ቻይ ጌታ፡ የቅዱሳን ንጉሥ!” ሰሙት! ዝግጁ ናችሁ? 4ኛው ቁጥር፦

> **ጌታ ሆይ፡ የማይፈራህና፡** (በትልቁ ፊደል ኤል-ኦ-አር-ዲ፡ ኤሎሂም) **የማያከብርስ...** የማይፈራህስ **ማን:... ስምህን የማያከብር ማን ነው?...**

199 አሁን እናንተ ቃሉን እየሰማችሁ፡ እና ኢየሱስ ክርስቶስ እሱ ሁሉን ቻይ መሆኑን እያመናችሁ፡ በምትታጠቡበት ተመሳሳይ ውኃ እነርሱም ታጠቡ። ገና ከጅምሩ ሙሉውን በመገለጥ ነው። ነገሩ ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ማን እንደ ሆነ በተገለጠው መገለጥ የተጠቀለለ ነው፡ “እግዚአብሔር በመካከላችን ሥጋ ሆነ!”

> ... :ሰምህ **ታላቅና ድንቅ ነው...**
>
> **የማይፈራህ... ስምህን** የማያከብር ማን **ነው?... አንተ ብቻ... ብቻህን... ቅዱስ ነህና፥ የጽድቅም ሥራህ ሰለ ተገለጠ፥ አሕዛብ ሁሉ ይመጣሉ በፊትህም ይሰግዳሉ።**

200 በሌላ አነጋገር፡ አለመቀበል ማለት ምን ማለት እንደሆነ እናያለን፡ ፍርዶችህ እየተገለጡ ናቸው። ሰለዚህ እነሆ ቆመናል፡ አሁን ታጥበናል፡ በመከራ ጊዜ ውስጥ ካለፍን በኋላ በውሃ ታጥበናል። ለአንተ ቆመናል እንተንም አምነናል፡ እናም አሁን በብርጭቆ ባህር ላይ ቆመናል፡ እንደ መንፈስ ቅዱስህ ነጸብራቅ እናከብርሃለን ውዳሴም እናቀርባለን። መቅረዞችህ እውነት ፍርዶችህም ጽድቅ ናቸውና።

201 ኦህ፡ ማይ! በዚህ ላይ አንድ ሳምንት መቆየት እንችላለን። "የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡" አንድ ነገር አሁን እዚህ እንሳል፡ አንድ ደቂቃ ብቻ፡ መሳል የምፈልገው ነገር አለ። አሁን፡ እስቲ፡ ባለንበት እዚህ ጋር ያለውን ለምን አንጠቀምም።

202 አሁን፡ ካስተዋልን፡ እዚህ በጣም ጥሩ ስዕል አለን። አሁን፡ ቅድስተ ቅዱሳን **ይህ** ነው። በጣም ጥሩ። ቅድስት የሚባለው ስፍራም **ይህ** ነው። **ይህ** ደግሞ ወደዚህ ከመግባት በፊት፡ የሚገኝ ስፍራ፡ ባ—ባሕሩ ነው።

203 በጣም ጥሩ፡ አሁን ልብ በሉ። ወደ እግዚአብሔር የምንቀርበው እንዴት ነው? "እምነት ከመስማት ነው፡ የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት፡" ከቅድስተ ቅዱሳን ወደ ዘመኑ መልእክተኛ እየተንፀባረቀ ነው።

204 ይህ በድሮው፡ በ... በሰለሞን ቤተ መቅደስ፡ ያንጸባርቃሉ፡ እነዚያ የመቅረዝ መብራቶች ወደ ነሐስ መታጠቢያው ገንዳ ያንጸባርቃሉ። ስለዚህ፡ ይህ **እዚህ** ጋር ያለው፡ የቤተ ክርስቲያን መልአክ ይህ **እዚህ** ወዳለው ሰው ወደ ውኃው ዘንድ ያንጸባርቅበታል፡ ምሕረቱን፡ ቃሉን፡ ፍርዱን፡ ሰሙን ያንጸባርቅበታል። ሁሉም የሚንፀባረቀው በማመን በምትለዩበት በዚህ ስፍራ ውስጥ ነው። ገብቷችኋል?

205 ምን ያህል ደስ እንደሚል ልብ በሉ፡ በቀደም ስለዚህ ነገር እየተነጋገርን ነበር። እዚህ ጋር እዩት፡ **እዚህ** ጋር፡ "እንግዲህ የምትጸድቁት፡ በእምነት ትጸድቃላችሁ።" በጣም ጥሩ፡ **በሁለተኛው ስፍራ**፡ ከታጠባችሁ በኋላ፡ "ትቀደሳላችሁ።" **ከዚያ**፡ በመቀጠል፡ "መንፈስ ቅዱስ ትሞላላችሁ።" ጽድቅ፡ ቅድስና፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት! አያችሁት? መልእክቱ እንዴት ነበር? ጽድቅ በመስማት ሲሆን፥ ቅድስና እናንተ በትምትሰሩት ነው፥ ከዚያ በኋላ የሰራችሁትን ስራ በማድነቅ እንደ ሽልማት፡ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ያትማችኋል።

206 አሁን፡ አንተ፡ የባፕቲስት ወንድሜ ሆይ፡ አንድ ጥያቄ እጠይቅሃለሁ። "አብርሃም እግዚአብሔርን ከማመን በቀር ምን ሊያደርግ ይችላል? እግዚአብሔርም ጽድቅ አድርጎ ቈጠረለት፡" ትላለህ።

207 **እዚህ** ስፍራ ላይ፡ ማድረግ የሚችለው ብቸኛው ነገር፡ እግዚአብሔርን ማመን ነው። እግዚአብሔር ግን፡ እምነቱን ይቀበላት ዘንድ፡ የመገረዝን ማኅተም ሰጠው፡ ይህም የሚያሳየው-... እግዚአብሔር እምነቱን ይቀበላት ዘንድ እንደሚገባ ነው። እና በእግዚአብሔር ላይ እምነት እንዳለህ ተናግረህ፡ በመንፈስ ቅዱስ ካልታተምህ... ኤፌሶን 4:30፡ ማስታወሻ መያዝ ከፈለጋችሁ፡ ወደ ኤፌሶን ሰዎች 4:30 ላይ፡ "የታተማችሁበትን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ!" የታተማችሁት መንፈስ ቅዱስ እስክትቀበሉ ድረስ አይደለም።

208 ለምን ያህል ጊዜ ይቆያል? እስከሚቀጥለው ሪቫይቫል ድረስ ነውን? "እስከ ቤዛችን ድረስ፡ እስከ የመቤዠት ቀን ድረስ ነው።" ከሱ የምትለዩበት መንገድ የለም። እሱ ከእናንተ አይለይም፡ ከሱ የምትለዩበት መንገድ የላችሁም። አያችሁ? "እስከ ቤዛችሁ ቀን ድረስ ታትማችኋልና።" "ያለውም፡ የሚመጣውም፡ አደጋ፡ ረሃብ፡ ጥማት፡ ሞት፡ ሌላም ቢሆን፡ በክርስቶስ ካለው ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን አይችልም።" ጳውሎስ እንዲህ አለ፡ "ሙሉ በሙሉ አምኛለሁ!" ይኸውላችሁ እንግዲህ! ይኸውላችሁ፡ እስከ ቤዛነት ቀን ድረስ ታትማችኋል።

209 ልብ በሉ፡ አሁንም ይህ ወደ ባለፈው—ወደ እሁድ ይመልሰናል። ጊዜ ይኖረኝ ይሆን? እስኪ... ተከታተሉ፡ ይሄን ተከታተሉ፡ መንፈስ... መንፈስ፡ ነፍስ፡ እና ስጋ። በጣም ጥሩ፡ እዩ፥ ስጋ፡ ነፍስ፡ መንፈስ።

210 አሁን፡ ያንን ላጥፋ እና አንድ ነገር ላስተካክልላችሁ። አሁን፡ እዚህ የሆነ ነገር እስላለሁ፡ ባለፈው እሁድ ለመሳል እድል አላገኘሁም ነበር ስለዚህ እኔ ራሴ በዚህ ቢጫ ወረቀት ላይ ሰዬዋለሁ። እሱን ምልክት እንድታደርጉበት እና ምን ማለቴ እንደሆነ እንድታዩት፡ አሁን፡ ብዕራችሁን ይዛችሁ ጻፉት። አሁን፡ **ይህ** ስጋ ነው፥ **ይህም** ነፍስ ነው፥ **ይህ** ደግሞ (በትልቁ ፊደል S-p-i-r-i-t) መንፈስ፡ መንፈስ ቅዱስ ነው። በጣም ጥሩ። አሁን፡ የተፈጠርነው በዚህ መልኩ ነው።

211 በተጨማሪ **እዚህ** ጋር ልብ በሉ፡ ቅድስት፡ ቅድስተ ቅዱሳን፥ **እዚህ** ጋር መሰዊያ፡ ቅድስት፥ **እዚህ** ጋር ደግሞ ባህር—ባህር አለ፡ ቃሉንም የምትሰሙት እዚያ ነው፡ "እምነት ከመስማት ነው፡ ቃሉን መስማት፡" መለየት፡ የመለየት ባሕር፡ ባሕረ መለየት። አሁን፡ እዚህ ጋር ልብ በሉ። አሁን፡ **ወደዚህ** ለመግባት አንዲት መግቢያ ብቻ አለች፡ እናንተም መጀመሪያ **ወደዚህ** መምጣት አለባችሁ። ልክ ነው?

212 አሁን፡ ጊዜ ቢኖረኝ ጥሩ ነበር፡ **እዚህ** ጋር አንድ ተጨማሪ ነገር፡ "የ—ደናግሉ።" የ... የ "የሰርጉ እራት፡" አስቀምጥበት ነበር። ይህ ሰው **ወደዚህ** የሰርግ እራት እንደገባ፡ የገባው ግን በሌላ መንገድ እንደሆነ አይታችኋል? በሩ **እዚህ** ነበርና። ኢየሱስም "በሩ እኔ ነኝ፡" አለ። ይህ የሰርግ ጠረጴዛ **እዚህ** ተዘርግቷል ሰዎችም ሁሉ በዙሪያው ተቀምጠዋል፡ እና የሰርግን ልብስ ያልለበሰ አንድ ሰው በመካከላቸው ተቀመጠ። ንጉሡም በገባ ጊዜ፡ "ወዳጄ ሆይ፡ ወደዚህ እንዴት ገባህ? እንዴትስ መግባት ቻልክ፡" ብሎ ጠየቀው? በዚህ በር እንዳልገባ ያሳያልና። በመስኮት ወይም በኋለኛው መንገድ መጣ፡ ወይም በአንዳንድ የሐይማኖት ስርዓት ወይም በቤተ እምነት ተቋማት። በበሩ በኩል አልመጣም!

213 ምክንያቱም በድሮ አባቶች ዘመንም ተመሳሳይ ስነ ስርዓት ነበራቸው፡ የሚያገባው ሙሽራ፡ የጥሪ ወረቀትን ይልካል ለጋበዛቸው ሰዎችም ለሁሉም ልብስ ያዘጋጅላቸዋል።

214 ኦህ፡ ሳስበው ልቤ ይዘላል ደጋግሞ ይዘላል! "አባቴ አስቀድሞ ካልጠራው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም፡ አብም የሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል።" የተጠራነው እንዴት ነው? ዓለም ሳይፈጠር በፊት ስማችን በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ላይ ተጽፏል፡ ብርሃን ለማየት፡ መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል፡ በእርሱ ዘንድ ለመላለስ ተመድበናል። ስሞቻችን (በጉ በታረደ ጊዜ) የበጉ ስም በተጻፈ በተመሳሳይ ጊዜ ስማችንም በመጽሐፉ ላይ ተጻፈ። መጽሐፍ ቅዱስ፡ የሚናገረውን፡ ከአፍታ በኋላ እንረዳዋለን፡ "ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ስሞቻቸው በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ውስጥ ያልተጻፉ በምድር ያሉ ሁሉ ያስታቸዋል።"

215 አስቡት፡ እሱ ራሱ... ሙሽራው ራሱ፡ በበሩ ይቆማል። ባልደረባውም የጥሪ ወረቀቱን ያመጣና፡ "ይኸው፡" ይለዋል።

216 "አመሰግናለሁ።" የጥሪ ወረቀቱን ይቀበላል፡ እዚህ ጋር ያስቀምጠዋል፡ ታዳሚዎቹ ሁሉ አንድ አይነት እንዲመስሉ መጎናጸፊያ ይሰጠዋል። ይህን በጣም ወደድኩት! አያችሁ? በእግዚአብሔር ስልጣን ፊት፡ በሕያው በእግዚአብሔር

ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፡ ሀብታም፡ ድሃ፡ እስረኛ፡ ነጻ፡ ጥቁር፡ ነጭ፡ ቡኒ፡ ቢጫ፡ ሁሉም አንድ አይነት የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይለብሳሉና አንድ ናቸው። አያችሁ?

ስለዚህ፡ ይህ በበር በኩል እንዳልመጣ ያስታውቅበታል።

217 አሁን፡ እዚህ ጋር ልብ በሉ። እነሆ፡ አንድ ሰው ወደ ቅድስተ ቅዱሳን መግባት ቢሞክር (አንድ፡ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ የነገረኝ)፡ አንድ ሰው **በዚህ** በኩል ሳያልፍ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ለመግባት ቢሞክር፡ ይሞታል። የአሮን ልጅ አንድ ቀን እንግዳ እሳት ወሰዱ፡ (የሐይማኖት ተቋም እሳት ባልነበረበት ጊዜ) የሐይማኖት ተቋም እሳት በወሰዱ ጊዜ፡ በዚያው በሩ ሞቱ። ልክ ነው? የኤሊ ልጆችም፡ ይመስለኛል። ኤሊ ካህን ሆኖ የአሮን ልጆች በሚወክል ጊዜ፡ ልጆቹ ይዘው ገቡ።

218 አሁን፡ አሁን፡ ወደ አካሉ መግቢያ አንድ መንገድ ብቻ አለ። ይህ አካል የሚቆጣጠረው እንዴት ነው? አሁን፡ ብዕራችሁን ይዛችሁ በትክክል ተከታተሉኝ። ወደ አካሉ መግቢያ የሚሆነው በር **ይህ** ነው፥ አንድ፡ ሁለት፡ ሦስት፡ አራት፡ አምስት። አሁን፡ ይህን ስላችሁ ይዛችኋል? አሁን፡ **ይህ** የመጀመሪያው በር፥ ማየት፡ ማሽተት፡ መስማት፡ እና መቅመስ፡ እና መዳሰስ ወይም ስሜት ነው (ከሁለቱ አንዱ ብትወስዱ፡ ለውጥ የለውም)። አሁን፡ እነዚህ የስጋ ውስጥ ስሜቶች ናቸው። ልክ ነው? ስንቶች ይህን ታውቃላችሁ? ስጋን ስድስት ስሜቶች ይቆጣጠሩታል። አሁን፡ **ይህን** ካለፋችሁ በኋላ ነፍስ አለን። የስሜት ህዋሳቱ ከውጭ ናቸው፡ ይህ ውጫዊ ስርዓት ነው።

219 አሁን፡ **እዚህ** በነፍስ ውስጥ አንድ፡ ሁለት፡ ሶስት፡ አራት፡ አምስት፡ አምስት ባህሪያት አሉ። አሁን፡ እነዚያን መጻፍ ትፈልጋላችሁ? አንደኛው ምናብ፡ ምናብ ነው። ሁለተኛው ህሊና። ሶስተኛው ትዝታ ነው። አራተኛው ምክንያት ነው። አምስተኛው ፍቅር።

220 እሺ፡ ጽፋችሁ ይዛችኋል? ካልጻፋችሁ፡ አሁን ንገሩኝ። ሁሉንም ጽፋችኋቸዋል? ማየት፡ መቅመስ፡ መዳሰስ፡ ማሽተት፡ እና መስማት፥ የስጋ፡ የስጋ መክፈቻዎች ናቸው።

221 ነፍስ ደግሞ ምናብ፡ ህሊና፡ ትዝታ፡ ምክንያት፡ እና ፍቅር፡ እነዚህ የነፍስ፡ ስሜቶች ወይም ባህሪያቶች ናቸው። ነፍስም ከውስጥ ያለው የመንፈስ ተፈጥሮ ናት፡ ምክንያቱም ነፍስ የምታወጣው በውስጣችሁ ያለውን ሁኔታ ብቻ ነው። ነፍስ፡ የመቀደስ ቦታ ይወስዳል፡ እዚያው ተመሳሳይ ምድብ ውስጥ ይቀመጣል። በጣም ጥሩ፡ አሁን፡ ሁላችሁ… ሁላችሁ ጽፋችሁታል? በጣም ጥሩ።

222 አሁን፡ **ለዚህኛው** አንድ በር ብቻ አለች፡ አንድ በር፡ "የራስ-ፈቃድ" ትባላለች። በዚያ ውስጥ ለሚከናወን ነገር ሁሉ እናንተ ራሳችሁ አለቃ ናችሁ። እና ምን ያደርጋል? ምንድነው? **ስጋው፡** በመታጠቢያ ገንዳ፡ ይታጠባል፡ **እዚህ** ጋር ይቀደሳል፥ **እዚህ** ጋር፡ በመንፈስ ቅዱስ ይሞላል፡ እና ይህ እንደገና እግዚአብሔር በልባችሁ ውስጥ የሚቀመጥበት፡ የእግዚአብሔር የፍርድ ዙፋን ይሆናል፡ አንድ ስሕተት ስትሰሩ፡ "ወይ፡ 'ኔ፡ ተሳሳትኩኝ፡" ትላላችሁ።

223 አንዳንድ ሰዎች፡ ሴቶች፡ "ጸጉሬን ማሳጠር—አይኮንነኝም" ይላሉ። "ማኒኩር መስራት ወይም ሜካፕ መልበስ፡ ወይም ምንም ይሁን ምን አይኮንነኝም። ጭፈራ ቤት መግባት አይኮንነኝም። ጉዳት የሌለው ውሸት መናገር አይኮንነኝም። የካርታ ቁማር በሚጨወትበት ፓርቲ የካርታ ጨዋታ

መጫወት አይኮንነኝም።” ለምን እንደሆነ ታውቂያለሽ? የሚኮንን ነገር ስለሌለሽ ነው። “ይህ ህሊናዬን አይጎዳኝም።” የእባብ ዳሌ ያህል እንኳን ህሊና የለሽም። እንዲሁ… በውስጥሽ የሚከስ ነገር የሌለሽ፡ ህሊና አልባ ነሽ። ከዚህ ዓለም ነሽ!

224 ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ **ወደዚህ** አስገባውና እንዴ ይህን ለማድረግ ሞክር! ወንድሜ፡ በጣም ትኮነናለህ እኔ እዚህ መቆሜ እርግጠኛ እንደሆነ ሁሉ በርግጠኝነት እያንገሸገሽህ ጭንቅላትህን ነቅንቀህ ትወጣለህ፡ እርሱ ቅዱስ ነውና። ሰሙኝ፡ ከቃሉ ዘንድ እጠቅሳለሁና፡ “በዓለም ያሉትን፡ እና የዓለም ነገሮችን ከወደዳችሁ፡ የእግዚአብሔር ፍቅር በእናንተ ውስጥ ስለሌለ ነው።”

225 ይህ እንዴት ይደረጋል? የራስ-ፈቃድ። “ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ ይህ እንዴት ‘የራስ-ፈቃድ’ ትለዋለህ? ” ምክንያቱም ሴቱም ሆነ ወንዱ በኤደን ገነት እንደነበሩት እንደ አዳምና ሔዋን እንዲያደርጉ ያስችላቸዋል። በምን ላይ? ሁለቱ ዛፎች! **ይሄኛው** የራስ-ፈቃድ፡ ሞት ነው። **ይሄኛው** የራስን-ፈቃድ፡ ህይወት ነው። ሰነ ምግባራዊ… የመምረጥ ነፃነት! አምላክ የመጀመሪያዎቹን ሰዎች፡ ማለት አዳምና ሔዋን፡ የመምረጥ ነፃነት እንዲኖራቸው አድርጎ በዚህ ሰፍራ አስቀመጣቸው። እናንተንም በተመሳሳይ ሰፍራ አስቀመጣችሁ። እና **እዚህ** ውስጥ መግባት የምትችሉበት ብቸኛው መንገድ በራሳችሁ የራስ-ፈቃድ ነው። ሃሌሉያ! ያራሳችሁ የራስ-ፈቃድ! የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመቀበል እናንተ ራሳችሁ መፍቀድ አለባችሁ። የእግዚአብሄር ፈቃድ እንዲመጣ የራስ ፈቃድ ማስወገድ አለባችሁ፡ ወደ ልብ የሚመራው መግቢያ መንገድ ይህ ብቻ ነውና።

226 እናንተ ባፕቲስቶች እና ፕሪስባይቴሪያኖች፡ ሆይ፡ ቤተ ክርስቲያን መቀላቀል ትችላላችሁ። እናንተ ሜቶዲስቶች እና ፒልግሪም ሆሊነሶችም ወደ መቀደስ መድረስ ትችላላችሁ። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመቀበል መንፈስ ቅዱስ **ወደዚህ** እንዲገባ፡ እንዲቀርብ ለማድረግ ግን፡ እናንተ ራሳችሁ የራስ-ፈቃድ፡ መፍቀድ አለባችሁ። “ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል። በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ። በአዲስ ቋንቋ **ይናገራሉ**። እጃቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ ወይም የሚገድል ነገርን ቢጠጡም፡ ወዘተ። ፈቃዶቻቸው ፈቃዴ እንዲሆን የፈቀዱትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፡ እኔም የማደርገውን ሥራ እነርሱ ደግሞ ያደርጋሉ።” እንደማያልፋችሁ ተስፋ አደርጋለሁ። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ፈቃድ አለ። ምን ለማለት እንደፈለኩ አያችሁ?

227 እዚህ ጋር ተመልከቱ፡ ስለ ቅድስት ሰፍራ፡ ስለ መታጠቢያው ገንዳ እየተነጋገርን ነው። መብራቶቹ **እነዚህ** ናቸው፡ መቅረዞቹ (አንድ፡ ሁለት፡ ሶስት፡ አራት፡ አምስት፡ ሰድስት፡ ሰባት)፡ እያንዳንዳቸው ብርሃን አላቸው። ብርሃናቸውን ከየት ነው የሚያገኙት? ብርሃናቸው የሚያንፀባርቀው የት ነው፡ የሚያንፀባርቀው ወደ የት ነው? እዚህ ጥግ ወዳሉት ወደ አንዳንድ ሐይማኖት ተቋሞች አያንጸባርቅም። የሚያንጸባርቀው ወደ ቃሉ ነው! የመለየት ውኃ ነው። ዋው!

228 “ንስሐ እና የኃጢያት ስርየት” (ሉቃስ 24:49) “ከኢየሩሳሌም ጀምሮ፡ ለአሕዛብ ሁሉ በስሙ መስበክ አለበት።” በኢየሩሳሌም ንስሐና የኃጢአት ስርየት እንዴት ተማሩ? ምን ያክል ርቀት ተጓዘ? ወደ ዓለም ሁሉ ሄደ። “ንስሐ

ግቡ፡" አለ ጴጥሮስ፡ በሐዋርያት ሥራ 2፡38 ላይ፡ "ለኃጢአታችሁም ስርየት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ።" መልእክቱ ወደ ዓለም ሁሉ ይሄዳል፡ ያን ጊዜ መጨረሻው ይመጣል። ስለዚህ መጨረሻ የሚሆነው፡ **ይህ** መልእክት ወደ ዓለውም ሁሉ ከሄደ በኋላ ይሆናል።

229 እንዴት፡ እነዚህ እዚህ ላይ ብርሃን የሚያንፀባርቁ መቅረዞች በአንዳንድ የሜቶዲስት፡ የፕሬስባይቴሪያን፡ ወይም የጴንጤቆስጤ ቤተ እምነት ያንጸባርቃሉን? መልካም፡ በፍጹም አይደለም!

230 **እዚህ** ላይ እንደ "እኔ ነኝ" ያንጸባርቃል እንጂ፡ እንደ "እኔ ነበርኩ" አይደለም። ሦስት ወይም አራት የተለያዩ ሰዎች ሳይሆኑ፡ ብቻውን እግዚአብሔር በዚያ ውስጥ አስገብቶ ለእያንዳንዳቸው ለእነዚያ አብያተ ክርስቲያናት ራሱን ያሳያል። መለስ ብላችሁ ምን እንዳደረጉ ተመልከቱ (በታሪክ ውስጥ አይተነዋል)፡ እርሱን እንደነበረ፡ እንዳለ፡ እና ወደፊትም እንደሚኖር አንጸባረቁት።

231 "የነበረው... " ዮሐንስ የመጀመሪያውን በከፊል ባየ ጊዜ፡ እንዲህ አለ፡ "የነበረው፡ ያለውና፡ የሚመጣው፡ ሁሉን ቻይ አምላክ፡ የእግዚአብሔር ፍጥረት፡ አልፋ፡ ኦሜጋ፡ መጀመሪያና መጨረሻ።" ሊንጸባረቅ የሚገባው እውነተኛው ብርሃን ይህ ነው። አያችሁት? አሜን! ዋው!

232 ከአስራ ሁለት ሰአት በኋላ፡ እኔ—የያዝኩትን... ሰሙኝ፡ በደንብ መጻፍ እንድትችሉ ቶሎ ቶሎ እንበል። ብዙ ስላቆየኋችሁ አዝናለሁ፡ ይሁን እንጂ ደግሜ መቼ እንደማያችሁ አላውቅም። አያችሁ? ወዳጆች ሆይ፡ ህይወት ነውና፡ ይህን እንድታውቁት እፈልጋለሁ። እንግዲህ፡ ይኸውላችሁ፡ እኔ ስለተናገርኩት ሆንኩት አይደለም። እንደዚያ አይነቱ ነገር—ካንጸባረቅኩ... እንግዲያውስ... ልቤን—በተሳሳተ መንገድ ተረድታችሁታል። ለመንጸባረቅ እየሞከርኩ አይደለም፡ "ኦህ፡ ያን ብታደርግ... ተራ ነህ።" ያን ለማድረግ እየሞከርኩ አይደለም። ብርሃኑን ያላገኛችሁ ከሆናችሁ፡ የምታገኙበትን እያሳየኋችሁ ነው። እዚህ ፑልቢት ላይ የቆመውን ሳይሆን፡ በዚያ በዙፋኑ ላይ ያለውን። ያ ዙፋንም በልባችሁ መሆን አለበት፡ ያን ጊዜ እዚህ እንደሚንጸባረቅ እንዲሁ በትክክል ታዩታላችሁ።

233 **እዚህ** ያለው ማን ነው? **ይህንን** የሚያንፀባርቅ ነው። **ይህ** ደግሞ ይህ ነው፡ ቃሉ ነው። በቃሉ ውሃ፡ የታጠበ፡ በቃሉ የታጠበ (በመለየት ውኃዎች) ከዓለም—በቃሉ፡ ከዓለም ነገሮች የተለየ። ቃሉ ትናንት እና ለዘላለምም ያው ነው ይላል። "በጴንጤቆስጤ ዘመን፡ እና በደቀ መዛሙርት ዘመን ያው ነው፡ ከዚያ በኋላ ባለው ዘመን ግን ተለወጠ፡" አይልም። አይልም፡ እርሱ ያው ነው! አያችሁ? ያላለውን ነገር አለ ማለት አትችሉም። በአንዱ ላይ ለሰዓታት መቆየት እንችላለን፡ ነገር ግን አሁን እንደምትረዱት ተስፋ አደርጋለሁ። እግዚአብሔር የጠራችሁ ስለሆናችሁ፡ ትረዱታላችሁ። እኔ የማምነው እነደዚያ ነው። በጣም ጥሩ፡ ወዳጄ።

234 አሁንስ፡ ምንድን ነው? ጽድቅ፡ ቅድስና፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡ ነፍስ፡ ስጋ፡ መንፈስ፡ ሁሉም አንድ ናቸው። አሁን፡ መቅረዙ የሚያንጸባርቀው ቃል ነው። እውነተኛው ቃልስ ምንን ያንጸባርቃል? እንግዲያውስ የሚንጸባረቅ ብርሃን የሚያገኘው ከአርያም ክብር ከነበረ፡ ይህ መቅረዝ ምንድነው? የአርያምን ክብር ያንጸባርቅ ነበር። አይደል?

235 ሴሚናሪ ውስጥ ስትገቡ፡ የምታንጸባርቁት ብርሃን፡ የሰሚናሪው ይሆናል። በሜቶዲስት ሴሚናሪ ውስጥ ከገባችሁ፡ ሜቶዲስዝምን ታንፀባርቃላችሁ። ታንጸባርቃላችሁ! በጴንጤቆስጤ ሴሚናሪ ውስጥ ከገባችሁ፡ ጴንጤቆስጤነትን ታንጸባርቃላችሁ። በቁጥቋጦ አጠገብ ወደ ነበረው፡ ወደ እግዚአብሔር ክብር ከገባችሁ ግን...

236 ታዲያስ፡ ሙሴ'ኮ ከመገኘቱ በመጣ ጊዜ፡ ፊቱ ላይ መሸፈኛ ማድረግ ነበረበት፡ ምክንያቱም፡ ሰዎች እሱን ማየት ስለተሳናቸው ነው። ልክ ነው? በእግዚአብሔር ኃይል ተሞልቶ ነበር።

237 እስጢፋኖስ፡ መንፈስ ቅዱስ የሞላበት ሰው። ይኸውላችሁ፡ እሱን ማስቆም ማለት፡ በከባድ ንፋስ መካከል በእሳት የሚጋየውን ቤት፡ እሳቱን ማጥፋት መሞከር ነው፡ ቤቱ ከባድ ንፋስ ባለበት ቀን በእሳት እየነደደ... ለማጥፋት መሞከር ማለት ነው። ኦህ፡ አብዝተው—በሞከሩ ቁጥር፡ እየባሰ ይሄዳል። ለምን፡ እሱን ማስቆም አትችሉም። በቀጥታ፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር፡ በሳንሄድሪን ሸንጎ ፊት ባቀረቡት ጊዜ እንዲህ ይላል፡ "በዚያ ቆሞ፡ መልአክ ይመስል ነበር።"

238 አሁን፡ "መልአክ" ሲል እዚያ የቆመ አንድ ፍጡር ነበር ማለት አይመስለኝም፥ ነገር ግን፡ መልአክ የሚናገረውን ነገር በትክክል የሚያውቅ ነው። ስለዚህ የትኛውም መልእክም፡ የቤተክርስቲያን ዘመን መልእክተኛም እንዲሁ ነው፡ ሴሚናሪው ምን ያሰባል ብሎ ወደ ኋላ አያይም። እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ የተናገረውን፡ እና ትናንትናና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለም ድረስ ያው መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያንጸባርቀው ኃይሉንም ያውቀዋል። አይፈራም፡ በትክክል እውነት መሆኑን የሚያውቀውን ነገር ይናገራል። እግዚአብሔርም በዚያ ቆሞ በተመሳሳይ ምልክትና ድንቅ እንዲሁም በተመሳሳይ ቃል፡ እርሱን ያጸናለታል። መልአክ ማለት ያ ነው!

239 እስጢፋኖስ በዚያ ቆሞ፡ "የምናገረውን አውቃለሁ፡" አለ። እንዲህ አላቸው፡ "እናንተ አንገተ ደንዳኖች እና ልባችሁ እና ጆሮዎቻችሁ ያልተገረዘ፡ እናንተ ሁልጊዜ መንፈስ ቅዱስን ትቃወማላችሁ። አባቶቻችሁ እንዳደረጉት፡ እናንተም እንዲሁ ታደርጋላችሁ!" አላቸውም፡ "ከአባቶቻችሁ ነቢያትን ገድሎ መቃብራቸውን ያልሠራ ማን ነው? "

240 እናንተ የሐይማኖት ተቋማት ሆይ፡ ከእናንተስ እንዲህ ያላረገ ማን ነው? አያችሁ? በነጭ-ግድግዳ ያጌጡ ትልልቅ ግንቦችን እና የሬሳ ቤቶችን እና ሌሎች ትገነባላችሁ፡ ከዚያም ስለ እግዚአብሔር ትናገራላችሁ! ወደ ሬሳው ቤት ያስገባችሁት እናንተ ራሳችሁ ናችሁ፡ ወደ መቃብር ውስጥ ያስገባችሁት እናንተው ራሳችሁ ናችሁ። እርሱን ወደዚያ ወደ ማቃብር ያወረደው፡ ትልቁ በነጭ-ግድግዳ ያጌጤ ቤተ ክርስቲያን፡ የሐይማኖት ተቋም ነበር፡ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ወደዚያ አወረዱት ከዚያም መታሰቢያ ሊሰሩለት ይሞክራሉ።

241 ክርስቶስ ሕያው ፍጡር መሆኑን ልንገራችሁ። ሞቶ የቀረ ነገር አይደለም፡ እንደገና "**ከሞት** ተነስቶ ለዘለአለም ህያው ሆኖ የሚኖር" እንጂ። አዎን፡ ወንድሜ! በትክክል! ምን ያደርጋል አልን? ምን ያንጸባርቃል? **ከዚህ** የተነሣ ያንጸባርቃል፡ ምን ይሆናል? እንዲህ ይሆናል-... የእሱ እውነተኛው ነጸብራቅ ምንድን ነው? ከሁሉ በፊት ቀድሞ የሚያንጸባርቀው፡ ስሙ ይሆናል። ልክ

ነው? ሰሙን ያንፀባርቃል። በመቀጠል፡ ኃይሉን ያንጸባርቃል። ምን ለማለት እንደፈለግኩ ተመልከቱ? ያለውን ሁሉ ያንፀባርቃል።

242 ስለዚህ **ይህ** ከዚህ በፊት የነበረው ነገሩን ሁሉ፡ **ወደዚህ** ወደ አሁኑ ዘመን የሚያንጸባርቅ ከሆነ፡ እንግዲያውስ እርሱ ያው ነዋ! ዋው፡ ክብር! ክብር ይሁን! ይህ ምንድነው? እርሱን እንደ የነበረ፡ ያለ፡ እና ዘወትር እንደሚኖር ያንጸባርቀዋል፡ ምክንያቱ ከእግዚአብሔር ዙፋን በቀጥታ ስለሚመጣ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትናም፡ ዛሬም፡ እስከ ለዘላለምም ያው ነው፥ አንዱ አምላክ፡ አንዱ ኃይል፡ አንዱ ክብር፡ ሁሉም ነገር ያው ነው። ትናንትናም፡ ዛሬም፡ እና ለዘላለም ያው ነው። ወንድሜ፡ ሆይ!

243 እስኪ ትንሽ ዘልቀን እንሂድ። አሁን፡ የቀረውን የዚህን 4ኛ ምዕራፍ፡ 6ኛው ቁጥር እንየው። በዚህ ላይ አንዳንድ አስተያየቶች ተጽፈውልኛል፡ እና ከቻልኩ በፍጥነት መግባት እፈልጋለሁ። እንግዲህ፡ ቀ—ቀሪው፡ ይህን ምዕራፍ ከፈጸምን በኋላ-... ይህን ቁጥር ካለፍነው በኋላ፡ ከዚህ በፊት ያደረጉትን በመናገር፡ የሚሸከረከር ነገር ብቻ ነው። እስኪ ያንን ማለፍ እንችል እንደሆን እንየው።

> ... **ብርጭቆ... የብርጭቆ ባሕር...** (እንግዲህ፡ ያ ምን እንደነበረ ተረድተናል።) **በዙፋኑም መካከል፡... አራት**፡ ህያው ፍጡራን **ነበሩ...**

244 አሁን፡ አሁን፡ አዲሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ዕትም ያላችሁ ሰንቶች ናችሁ? በአዲሱ እትም ላይ፡ "ህያው ፍጡራን" ይላቸዋል። እንጃ፡ እዚህ ጋር፡ ኪንግ ጄምስ፡ ህያዋን ማለቱ፡ ወይም፡ አራት "**እንስሶች**" ነበሩ ማለቱ ገረመኝ። እና፡ የግሪክ—መዝገበ ቃላት አመጣሁ፡ እና ወደ መጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ገብቼ ትርጉሙን አገኘሁት። እንግዲህ፡ ነገሩ ይህ ነው። አሁን፡ በደንብ ተከታተሉኝ። እዚህ ጋር ቃሉ ሲተረጎም፡ እና ሄዳችሁ በደንብ እንድትፈትሹት፡ እርግጠኞችም እንድትሆኑ፡ ይህን ማስታወሻ ያዙ። እያችሁ። ከቻላችሁ እና ከፈለጋችሁ፡ የምናገራቸውን ነገሮች... ማስታወሻ እንድትይዙ እፈልጋለሁ። እሺ፡ በዚህ ውስጥ፡ አዲሱ ቅጂ "ህያው ፍጡራን፡" ይላቸዋል። አሁን፡ ተከታተሉ፥

> **በፊትና በኋላ ዓይኖች የሞሉአቸው አራት አውሬዎች** ነበሩ።

245 ወደ ፊት ይሄድና "አውሬዎቹን" ይተነትናቸዋል፡ እኛም ከእፍታ በኋላ ወደዚያ እንገባለን። አሁን፡ እዚህ ጋር **አውሬ** ተምሣሌት ነው። በመጽሐፍ ቅዱሳችሁ ስር፡ ስለ—ስለ **አውሬዎቹ** ማጣቀሻ ንባብ አለው? ካለው፡ ወደ ማጣቀሻው ንባብ ሂዱ። እዚህኛው ላይ ዶክተር ስኮፊልድ በእሱ ውስጥ ምልክት ማድረጉን አስተውያለሁ። እዚህ ጋር፡ **አውሬዎች** ማለት፡ "ህያው ፍጡራን፡" ማለት ነው ይላል። ኦህ፡ ማይ! አሁን፡ ተከታተሉ። በግሪክኛ ቃሉ እንዲህ ነው፡ "Z፡ ደብል o፡ m፡" ወይም "Z፡ ደብል o፡ n፡" እንዲህ ነው፡ "Z፡ ደብል o፡ n፡" አሁን፡ በ—በግሪክኛ ዙን ይባላል፡ ትርጓሜውም "ፍጡር" ማለት ነው።

246 አሁን፡ እንደዚያ አይደለም... አሁን ማንበብ ከፈለጋችሁ። ጊዜ የለንም። ላነብ ነበር፡ ግን አላነበውም። ራእይ 11ን፣ 13ን፣ እና 17ን አንብቡ። አሁን፡ በዚያ **አውሬ** ይለዋል፡ በራእይ 11፣ 13፣ እና 17 ላይ፣ ያሉት ምዕራፎች በተመሳሳይ መልኩ **አውሬዎች** ይላቸዋል፥ በዚያ ውስጥ ያሉትን **አውሬዎች**

ግን፡ ሲተረጎሙ “t-h-e-r-i-o-n፡” ቴሪዮን ነው። ቃሉ፡ የግሪክ ቃል **ቴሪዮን** ነው፡ ትርጉሙም “የዱር፡ ያልተገራ አውሬ።” **ቴሪዮን፡** ማለት “የዱር፡ ያልተገራ አውሬ” ማለት ነው።

247 ዞን ማለት ግን “ፍጡር” ማለት ነው፡ አያችሁ፡ “አራት ሕያዋን (ዞን) ፍጥረታት።” **ቴሪዮን**፡ የተባሉ “የዱር” **አውሬዎች** አይደሉም፡ ነገር ግን፡ “ዞን፡ ህያው ፍጡራን።”

248 እና **ቴሪዮን** ግን “ያልተገራ፡ የዱር አረመኔ ነው።” በሌላ አነጋገር፡ 11ኛውን ምዕራፍ የምትመለከቱ ከሆነ “የሮም አውሬ” ነው። 13ኛው ምዕራፍ፡ “አሜሪካ” ናት። 17ኛው ምዕራፍ ደግሞ፡ “ሁለቱም አሜሪካ እና ሮም” ናቸው፡ ከእነዚያም ከካቶሊካዊነት ጋር የተዋሃዱ የሐይማኖት ተቋማት የሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ያልተለወጡ፡ ለወንጌል ያልተገሩ ያደርጋቸዋል። ዋው! ያልተገሩ!

249 “እግዚአብሄር ይባረክ፡ ከትልቁ የሜቶዲስት ቤተክርስቲያን፡ ከባፕቲስት፡ ከፕሪስባይቴሪያን፡ ከጴንጤቆስጤ የሐይማኖት ተቋም እምልጠናል። የምንናገረውን እናውቃለን! ማንም አይመራንም... አይነግረንም!” ይኸው። ያልተገሩ! ያልተለወጡ! ተፈጥሮአዊ ፍቅር የሌላቸው! ውል አፍራሾች! የውሸት ከሳሾች! ራሳቸውን የማይገዙ! መልካም የሆነውን የሚጠሉ! የአምልኮት መልክ ያላቸው...

250 [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።]... አሁን ይሄን አደርጋለሁ። እና ያንን ነገር አሁኑኑ መቆራረስ እፈልጋለሁ፡ ማለት... ምክንያቱ፡ ወደዚህ ካሴት ቅጂ ውስጥ እንዲገባ ነው። ያንን ለማድረግ ግን ጊዜ አይኖረንም። አሁን፡ ይገባችኋል። ሰንቶች ገብቷችኋል? እስኪ “አሜን” በሉ። [ጉባኤው “ኣሜን፡” አለ።] አያችሁ፡ እነዚህ ሁሉ...

251 **ዞን** ምንድነው፡ Z፡ ደብል o-n? ህያው ፍጡራን። ሲነበብ **ዞን** ይመስለኛል፡ Z፡ ደብል o፡ n። ስታነቡት ምን ትላላችሁ፡ “ዞን”? እኔ “ዞን፡” እለዋለሁ።

252 እና **ቴሪዮን** ደግሞ t-h-e-r-i-o-n፡ **ቴሪዮን**፡ አያችሁ። ስለዚህ ትርጉሙም “ያልተገራ አራዊት፡ የዱር፡ አረመኔ።” እነዚያ አውሬዎች... የያዛችሁትን... የግሪክ መዝገበ ቃላት ክፈቱ እና ተመሳሳይ ቃል ካልሆነ እዩ። ገልጣችሁ እዩ እና እወቁ። የግሪክ መጽ—መጽሐፋችሁን፡ ኢምፋቲክ ዲያግሎትን ክፈቱት። ስለዚህ፡ ይህ ትክክል ካልሆነ እዩ፡ ይህ እውነት ነው፡ ትርጉሙም “ያልተገራ አራዊት” ማለት ነው፡ በራዕይ 11፣ 13፣ እ—እና 17 ላይ።

253 እና እዚህ የራዕይ 4 ላይ፡ ትርጉሙ “ሕያው ፍጡር” ማለት ነው። **አውሬ** አይደለም፡ “አውሬ” ተባሉ እንጂ አይደለም። በሕዝቅኤል 1:8፣ 1 እስከ :28 ላይም ተመሳሳይ ነገር ነው። ምናልባት በአንድ ደቂቃ ውስጥ እንገባበታለን።

እሺ፡ “ያልተገራ፡ ያልተለወጠ፡ የዱር አራዊት።” ያልተገራ!

254 **እነዚህ** ግን “ህያው ፍጡራን” ናቸው። ምንድን ናቸው? መላእክት አይደሉም። ልንገራችሁ፡ በዚያው ገጽ፡ ራእይ ምዕራፍ 5 ላይ እናንብብ። ራእይ 5፣ ከ ቁጥር 11፦

**እየሁም፡ እና... የብዙ መላእክትን ድምፅ ሰማሁ** (“መላእክት፡” ብዙዎች) በ**ዙፋኑ ዙሪያ** (“እና” የቃላት አያያዥ ነው።) **በአውሬዎቹ እና... በሽማግሌዎቹ መካከል፥...**

255 አያችሁ፡ “እና፡” አያያዥ ነው። አያችሁ? መላእክት አልነበሩም፡ ሽማግሌዎችም አልነበሩም፡ እነዚህ በዙፋኑ ላይ የነበሩ “ሕያው ፍጡራን” ናቸው። ኦህ፡ ይህ አይላችሁም? ህያው ፍጡራን! መላእክት አይደሉም፡ ምክንያቱ ይህ ያጸናዋል፡ አያችሁ፦

**... እኔም አየሁ፡ እና... በዙፋኑም በእንስሶቹም በሽማግሌዎቹም** ዙሪያ **የብዙ መላእክትን ድምፅ ሰማሁ፥...**

256 አሁን እዚህ ሶስት የተለያዩ ምድቦች አሉ። ሁላችሁም ይህንን ስርዓት አሁን እንደተረዳችሁት ተሰፋ አደርጋለሁ። አሁን፡ ላሳያችሁ። በውስጡ ሦስት የተለያዩ ምድቦች አሉ፡ ሦስት የተለያዩ ዝርያዎች (አሁን፡ ተመልከቱ።) በዙፋኑ ዙሪያ።

257 ዙፋኑ **ይህ** ነው። አሁን፡ በዚህ ዙፋን ላይ የመጀመሪያዎቹ አራት ሕያዋን ፍጥረታት ይገኛሉ። ከዚያ ወጣ ሰንል ሃያ-አራት (ልክ **እንደዛ**) ሽማግሌዎች በዙፋን ላይ የተቀመጡ ናቸው፡ በዙፋን—በዙፋኖቻቸው ላይ፡ ትናንሽ ዙፋኖች ስር። በዚህ ዙሪያም፡ በዙፋኑ ዙሪያ የብዙ መላእክት ሰራዊት አሉ። ምን ለማለት እንደፈለግኩ ገባችሁ? እያንዳንዳቸው አንዱ ከሌላው፡ የተለያዩ ናቸው። **እነዚህ** መላእክት፡ **እዚህ** ጋር ሽማግሌዎች ናቸው፥ **እዚህ** ጋር ደግሞ ሕያዋን ፍጥረታት አሉ።

258 እስቲ ለአንድ ደቂቃ ከዚህ እንውጣ። ለአፍታ ያህል በዚህ እንቆያለን፡ “ህያው ፍጡራን።” መላእክት ካልሆኑ፡ የተዋጁ ሰዎች ካልሆኑ ምንድናቸው? ምንድን ናቸው? ማወቅ ትፈልጋላችሁ? የእኔ ትርጓሜ እንደሚከተለው ነው። ትክክል እንደሆነ ተሰፋ አደርጋለሁ፥ እንደሆነም አምናለሁ። የእግዚአብሔር የዙፋኑ ጠባቂዎች ናቸው። አሁን፡ ይህን ቶሎ ብለን እንደምሰሰዋለን። ስለዚህ፡ እንደምታዩት፡ ሰዎች ወይም—ወይም መላእክት አይደሉም። የዱር አውሬዎች አይደሉም። ፍጡራን፡ “ህያዋን ፍጡራን” ናቸው።

259 ስለዚህ፡ **ይህ** የእግዚአብሔር ዙፋን ነው። **እነዚህ** ደግሞ ጠባቂዎች ናቸው። እስቲ በጥቂቱ ከዚያ እናንብብ እና በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ እናውቀዋለን። አያችሁ፡ የእግዚአብሔር መላእክት ወይም የእግዚአብሔር የዙፋኑ ጠባቂዎች ናቸው፡ እና... አሁን እንለፍ... አ—አሁንም አንድ ደቂቃ፡ ወደ ሕዝቅኤል እንለፍ። እነዚህ ነገሮች እዚህ ጋር ጽፌ ይዣቸዋለሁና፡ ዝም ብዬ ላልፋቸው አልተሰማኝም፡ በርግጥ ይህ እንዲህ እንደሆነ ይገባኛል... [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።] ወደ ሕዝቅኤል ምዕራፍ 1 እንመለስ፡ እና ከ12ኛው እስከ 17ኛው ቁጥር፡ አንድ ደቂቃ ብቻ እንየው።

**እያንዳንዱም ወደ ፊት ቀጥ ብሎ ይሄድ ነበር፥...**

260 አሁን፡ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ እንመለከታለን... እና እዚህ ጋር፡ 7ኛው ቁጥር ታስታውሳላችሁ፡ በዚያው በራዕይ ምዕራፍ ላይ 7ኛው ቁጥር እዚህ ላይ “አራቱ፡” ምን እንደሚመስሉ ተመልከቱ።

**ፊተኛውም አውሬ እንደ አንበሳ ነበረ፡... ሁለተኛውም አውሬ ጥጃን** ይመስላል፡... **ሦስተኛው አውሬ ፊቱ...** እንደ **ሰው... ፊት**

ነበረው፡ አራቱም አው**ሬዎች... አራተኛው አውሬ... እንደ የሚበር** ንስር... **እንደሚበር ንስር ይመስል ነበር።**

261 እንግዲህ፡ ሕዝቅኤል የእግዚአብሔርን ክብር ባየ ጊዜ፡ ዮሐንስ ያየውን ተመሳሳይ ነገር አየ። ባለፈው እሁድ "የእግዚአብሔር ክብር" እንዴት እንዳገኘን፡ ከእኛ ጋር የተነሳውንም ፎቶውን እንዴት እንዳየነው ታስታውሳላችሁ? ታስታውሱታላችሁ? "የእግዚአብሔር ክብር፡" ሕዝቅኤል ያየውን፡ ዮሐንስም ያየውን፡ ዛሬም ይኸው አለ። በሕዝቅኤል ዘመንም ያው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስን፡ በምድር ላይ የነበረውም ያው ነበረ፡ ዛሬ ከእኛ ጋር ያለው ያው አምላክ፡ ትላንትናም፡ ዛሬም፡ ለዘላለምም፡ ያው የሆነው፡ የነበረና፡ ያለው የሚመጣውም፥ እርሱ ወደ ነፍስ፡ ስጋ፡ መንፈስ መግቢያ፥ የናስ ባህር (ቃል)፡ የነፍሳችን ቀዳሽ፡ መንፈስ ቅዱስን የሚሞላን። ያው ነው፡ አያችሁ፡ ያው ራሱ ነው!

262 አሁን፡ ይህን ተመልከቱ። በጣም ጥሩ፦

... እና **መንፈሱ**... ሁሉ **እነርሱ ሲሄዱ፥**... አሁን... **በሄዱበት፡ ይሄዳሉ፥ ሲሄዱም አይገላመጡም ነበር።**

263 ወደ ኋላ አይመለሱም። **በዚህ** መንገድ ሲሄዱ፡ እንደ ሰው ይሄዱ ነበር፥ **በዚህ** በኩል ሲሄዱ፡ እንደ ንስር ይሄዱ ነበር፥ **በዚህ** በኩል ሲሄዱ፡ እንደ በሬ ይሄዱ ነበር፥ **በዚህ** በኩል ሲሄዱ፡ እንደ አንበሳ ይሄዱ ነበር። ወደ ኋላ አይመለሱም! አውሬዎቹ በሚሄዱበት፡ በሁሉ ወደፊት ይሄዱ ነበር። አሁን፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ **አውሬ** ማለት ምን ማለት ነው? ስልጣን። እሺ "ስልጣን፡" ማለት ነው።

264 አሁን፦

**በሕያዋን ፍጡራን መካከል እንደሚነድድ የእሳት ፍም ያለ ምሰያ ነበረ፡** በእንስሶች **መካከል፡ ወዲህና ወዲያ የሚሄድ፥ እንደ... ፋና... ያለ ምሰያ ነበረ፥ ለእሳቱም ፀዳል ነበረው፡ ከእሳቱም** ብርሃን **ይወጣ ነበር።**

እግዚአብሔር ነው። ከእሳቱ ውስጥ ብርሃን ይወጣል፥ የጠፈር ብርሃን አይደለም፡ ይህ፡ ዘላለማዊው ብርሃን ነው።

**ህያዋን ፍጡራንም ምሰያ ይሮጡና** ይመለሱ (እስኪ እንየው... ) **እንሰሶቹም እንደ መብረቅ ምሰያ፡ ይሮጡና ይመለሱ ነበር።**

**ህያው ፍጡራንን ሰመለከት፡ እነሆ በህያዋን ፍጡራን አጠገብ በምድር ላይ አንድ አንድ መንኰራኵር አየሁ፡ አራት ፊትም ነበረው።**

**የመንኰራኵሩም መልክ እንደ ቢረሌ ነበረ... አራቱም አንድ አምሳያ ነበሩ... ሥራቸውም... በመንኰራኵር ውስጥ እንዳለ፥ መንኰራኵር ነበረ፥ መልካቸው እና ሥራቸውም... በመንኰራኵር ውስጥ እንዳለ መንኰራኵር** ነበረ።

265 "ይህ ተምሣሌት፡ የምን ምልክት ነው ወንድም ብራንሃም? ምንድነው ይሄ? " እነዚህ ጠባቂዎች ናቸው—እነዚህ የእግዚአብሔር ታቦት ጠባቂዎች ነበሩ... ሕዝቅኤል ባያቸው ጊዜ፡ በመንኰራኵሮች እየተንከባለሉ የሚጓዙ ነበሩ፥ ዮሐንስ ባያቸው ጊዜ ግን፡ በሰማይ ወደነበረው ወደ ትክክለኛው ቦታቸው

መጥተው ነበር። በመንኰራኲሮች እየተንከባለለ፡ ከቦታ ቦታ ሲወሰዱት በጉዞ ላይ ነበር፡ ማለት የእግዚአብሔር ታቦት፡ በምድር ላይ ነበር ማለት ነው፡ ከዚያ ከምድረበዳ ጀምሮ እስከ ቤተ መቅደስ ድረስ እና በዚያ ሁሉ አሳለፋት፥ አሁን ግን የቤተ ክርስቲያን ዘመን ስላበቃ፡ ወደ ሰማይ ተወሰደ ወደ ክብርም ተወሰደ። እያችሁ? አሁን በመንግሥተ ሰማያት፡ ከመላእክቱ እና በዙሪያው ካሉ ነገሮች ጋር፡ ቋሚ ሆነ። አክሊላቸውን አውልቀው በግምባራቸው ወድቀው ለእርሱ ክብር ሲሰጡ እናገኛቸዋለን። እያችሁ? የቤተ መቅደሱ፡ የታቦቱ የእግዚአብሔር ጠባቂዎች ነበሩ።

266 አሁን፡ የእግዚአብሔርን የታቦት ጠባቂዎች፡ ወይም የሰርየት መክደኛውን አስታውሱ። አሁን፡ አስታውሱ። ለሰንቱ፡ ዮሐንስ፡ ሰንቶች አየ? አራት። **እሱ** ሰንቶቹን አ—አየ? እርሱም፡ አራት፡ ህያው ፍጡራን አይቷል። አሁን፡ ተመልከቱ፡ ሁለቱም አንድ አይነት ራእይ አይተዋል።

267 አራት ደግሞ የምድር ቁጥር ነው። ይህን ታውቃላችሁ? ወደዚያ ከመግባታችን በፊት፡ **አራት** ምድራዊ ቁጥር መሆኑን ሰንቶች ታውቃላችሁ? በእርግጠኝነት! እንደ አራቱ ዕብራውያን... ምድር ነው-... የምድር ቁጥር ነው፡ የ "ነጻ መውጣት፡ ነጻ መውጣት።" አሁን፡ ያንን "ነጻ መውጣት፡" የሚለውን በአሳባችሁ ያዙ፡ ከጥቂት ደቂቃ በኋላ፡ በደንብ አድርጌ፡ እዳሰሰዋለሁ። እያችሁ፡ "ነጻ መውጣጥ!" እንግዲህ፡ በእቶኑ ውስጥ ሦስት ዕብራውያን ልጆች ነበሩ፡ አራተኛው ሲመጣ ግን፡ ነጻ መውጣት ሆነ። አልዓዛር በመቃብር ሦስት ቀን ኖረ፡ አራተኛውም በመጣ ጊዜ ነጻ ወጣ። **አራት** የእግዚአብሔር "የነጻ መውጣት" ቁጥር ነው፡ ስለዚህ እነዚህ ፍጡራን ስለ ምድር የሆነ ነገር መሆን እንዳለባቸው ያሳያል።

268 አሁን እጅግ እንዳልራባችሁ ተስፋ አደርጋለሁ። መንፈሳዊ የምግብ ፍላጎታችሁ ከተፈጥሮአዊው ይልቅ—ትንሽ ከፍ እንዳለ ተስፋ አደርጋለሁ። እያችሁ? በጣም ጥሩ።

269 አሁን፡ ልብ በሉ፡ "ከፊት ከኋላ እና ከውስጥ" (እዚህ ሕዝቅኤል ላይ) "ዓይኖች አሏቸው።" እስኪ እናንብበው። ተመልከቱት፡ እሺ። እዚህ ጋር እዩት፡ እዚህ ጋር ስለ "አውሬዎቹ፡" የሚናገር ይመስለኛል፡ እንደ ንስር የመሰሉ፡ አራት ፊቶች፡ ክንፎች ያሏቸው፡ በውጭ እና በውስጥ፡ አይኖች የተሞሉ ናቸው። እዚህ ጋር እዩ፦

> **ለአራቱም እንስሶች ለእያንዳንዳቸውም ስድስት ስድስት ክንፎች ነበሯቸው፥...**

270 "ይበሩም ነበር፡" ወዘተ፡ "ከውጪም፡ ከውስጥም፡ ከኋላም ዓይኖች ነበራቸው።" ስለ እውቀታቸው ይናገራል። የነበረውን፡ ያለውን፡ እና የሚመጣውን ያውቃሉ፥ ምክንያቱ ሰው እስከማይሆኑ ድረስ፡ ወደ ዙፋኑ እጅግ ቀርበው ስለተቀመጡ ነው። የቤተመቅደስ ጠባቂዎች፡ ወይም፡ የቤተመቅደስ ጠባቂዎች ሳይሆኑ (የመቅደሱ ጠባቂዎች፡ መቶ አርባ-አራት ሺህ ናቸው።)፡ እነዚህ የምሕረት-መክደኛውን ጠባቂዎች፡ የዙፋኑ ጠባቂዎች ናቸው፡ ወደ እግዚአብሔር እጅግ ቀርበው፡ ዙፋኑን የሚጠብቁ፡ "ህያዋን ፍጥረታት፡" ከእግዚአብሔር ቀጥለው፡ የቆሙ ናቸው። በዕውቀታቸው፡ የነበረውን፡ ያለውን፡ የሚመጣውን ሁሉ ያውቃሉ። "ውጫዊ ዓይኖች" መኖራቸው፡

ወደፊት የሚመጣውን፡ የማየት ችሎታቸው ነው፥ “የውስጥ ዓይኖች፡” አሁን ያለውን ሁሉ ስለ ማወቃቸው ነው፥ “የኋላ ዓይኖቻቸው” ደግሞ፡ የነበረውን ስለማወቃቸው ያሳያል። የነበረው፡ ያለው፡ የሚመጣው፡ በሁሉ የቤተ ክርስቲያን ዘመናት የሚንጸባረቀው “የነበረ፡ ያለው፡ የሚመጣውም፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትም፡ ዛሬም፡ እስከ ለዘላለምም ያው ነው።”

271 አሁን እነሱን ያዙልኝ። በመቀጠል በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ እነዚህ ምን እንደሆኑ ብላክ ቦርዱ ላይ ከፋፍለን እናያቸዋለን። አሁን አስተውሉ። አንድ ደቂቃ፡ ስጡኝ።

272 የዕውቀት ክህሎታቸውን የሚያስረዳ ነው፡ ዕውቀት፡ እንደሚያውቁ ያሳያል። የወደፊቱን እና የአሁኑን እና ያለፈውን፡ እና ስለ እሱ ሁሉንም ያውቃሉ!

273 እነዚህም... የማይደክሙ ነበሩ። ደከመኝ አያውቁም። ደከመኝ ከሚል ሰው ጋር፡ የሚያገናኝ አንዳች ነገር የላቸውም። ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ፡ ቅኔ ይቀኛሉ “ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅዱስ! ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅዱስ! ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ሁሉን የሚገዛ ጌታ አምላክ! ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅዱስ!” ቀን እና ሌሊቱን ሁሉ ሳያርፉ በእያንዳንዱ ዘመን። “ቅዱስ!”

274 አንድ ደቂቃ ብቻ ወደ ኋላ እንመለስ። ወደ ኋላ እንመለስ፡ አንድ ጥቅስ በልቤ አለ፡ ኢሳያስ 6፣ ቶሎ እንበል። እዩት! ኢሳያስም ተመሳሳይ ነገር አየ።

275 የጌታ ራእይ ሁሉ... ያልኩትም ይህንኑ ነው። ዛሬ የምናያቸው ራእዮች በትክክል የመጽሐፍ ቅዱስ ራእዮች ካልሆኑ፡ ተሳስተዋል። እግዚአብሔርን ድሮም እንደነበረ ከሚያሳየው መገለጥ፡ በቀር፡ ሌላ ነገር የሚያንጸባርቁ ከሆነ፡ የተሳሳተ መገለጥ ነው። መላዋ ቤተ ክርስቲያን የተገነባችው በዚያ ላይ ናት፡ ማቴዎስ 17።

276 ኢሳይያስ፡ ምዕራፍ 6ን፡ እንመልከት። ይህ ወጣት ነቢይ በመልካሙ ንጉስ እቅፍ ላይ ተደግፎ ነበር፡ ሁሉንም አይነት መልከ መልካም ልብሶችም ይገዛለት ነበር። ነብይም ነበር፡ በሁሉም ቦታ ተቀባይነት አግኝቷል... አንድ ቀን ግን ንጉሱ ሞተ፡ ያን ጊዜ እራሱን ማትጋት ነ—ነበረበት። ስለዚህ ሊጸልይ ወደ ቤተ መቅደስ ወረደ። ምክንያቱም የንጉሥ ሰፍራ ከነበረበት መውጣት ጀምሮ ነበርና፡ እና፡ ወጣ... ንጉሡ ደግ እና መልካም ቅዱስ ሰው ነበረ። እርሱ ግን ወጥቶ የሕዝቡን ኑሮ አይቶ፡ ወደ ቤተ መቅደሱ ወረደ። አሁን፡ አዳምጡ።

> **ንጉሡ ዖዝያን በሞተበት ዓመት እግዚአብሔርን በዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁት፡ በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ አየሁት፡ የልብሱም ዘርፍ መቅደሱን ሞልቶት ነበር።**

277 ክብር ይሁን! “የልብሱ ዘርፍ” ምንድነው? ይኸውላችሁ፡ የሚከተለው የልብስ ዘርፍ “መላእክት፡ ፍጥረታት፡” ናቸው። የልብስ ዘርፍ ማለት ከኋላ የሚከተል ነው፡ አያችሁ?

> **... የልብሱም ዘርፍ መቅደሱን ሞልቶት ነበር።**

> **ሱራፌልም በላዩ ቆመው ነበር፥** ለእያንዳንዳቸውም **ስድስት ክንፍ ነበረው፥ በሁለት ክንፍ ፊቱን ይሸፍን ነበር፡... በሁለቱም ክንፍ እግሮቹን ይሸፍን ነበር፡ በሁለቱም ክንፍ ይበር ነበር።**

**እንዱም ለአንዱ፡ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፤ ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች፡ እያለ... ይጮኽ ነበር።**

**የመድረኩም መሠረት ከጭዋኺው ድምፅ የተነሣ ተናወጠ፡ ቤቱንም ጢስ ሞላበት።**

278 ማይ! ኦህ፡ ማይ! የሚያሳየው ራእዮቹ እነዚያ ሰዎች በየግላቸው ተመሳሳይ ነገር ማየታቸው ነው። "ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ!" ቀንና ሌሊት፡ ደከመኝ ስለቸኝ ሳይሉ፡ "ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስና፡ ለእግዚአብሔር!"

279 አሁን እነዚህ ሰዎች በትክክል እንደተርዳናቸው ለማየት፡ ውደኋላ መለስ እንበል። እነዚህ ጠባቂዎች ለመጀመሪያ ጊዜ የተገለጹት፡ በዘፍጥረት ውስጥ ነው። አሁን፡ የምንሰብከው ነገር ሁሉ ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ ድረስ መምጣት እንዳለበት፡ አስታውሱ። በማንኛውም ጊዜ መጠየቅ በፈለጋችሁ ጊዜ፡ ኑና ጠይቁኝ። እያችሁ? አንዱን ክፍል ብቻ ሳይሆን፡ መላው መጽሐፍ ቅዱስ ማዳረስ አለበት፡ እግዚአብሔር አይቀያየርምና! በዘፍጥረት ውስጥ የነበረው፡ በመካከለኛው ዘመንም እርሱ ነበር፡ ዛሬም እርሱ ነው። ሁል ጊዜ አንድ ነው! እያችሁ? አሁን፡ በዘፍጥረት ውስጥ፡ እነዚህ ኪሩቤል ሲሆኑ... እነሱን መረዳት የቻልኩት በዚህ ነው፡ መጀመሪያ ላይ ምን እንደነበሩ ለማወቅ ወደ ኋላ መመለስ ነበረብኝ።

280 ወደ ዘፍጥረት 3፡24 እንሂድ፡ ለአፍታ ያህል። ኦሪት ዘፍጥረት፡ ምዕራፍ 3 እና 24 ኛ ቁጥር። ወደዳችሁት? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—አርታዒ።] በጣም ጥሩ። አሁን፡ ከ 22ኛው ቁጥር እንጀምር። እ—እኔ ወድጄዋለሁ! ይሔኛው እዚህ ጋር ለማካተት ያህል ያመጣሁት፡ ተጨማሪ ነገር ነው፡ ቢሆንም አንድ ቀን እጅግ ይረዳችኋል።

**ጌታም... እንዲህ አለ፡ እነሆ፡ ሰው እንደ... እንደ እኛ ሆነ፡...**

281 አሁን፡ እናንተ የተወደዳችሁ እና ፍቅር የተሞላችሁ ውድ እህቶች ሆይ (እንዲህ ላስቀምጠው።)፡ እባካችሁ የሴትነትን ውድ ክብር፡ ታማኝነትዋ እና ርህራሄዋ—ላይ መጥፎ ነገር ለመጫር ፈልጌ እንዳይመስላችሁ። ስለ ሴት ለማሳየት የፈለግኩት... እባካችሁ! እናንተም፡ በዚህ ቴፕ ውስጥ ይህን ካሴት ለምታዳምጡ ሴቶች፡ እናንተን መናቄ አይደለም፡ እኔ ብርሃን ለማምጣት የእግዚአብሔር ባርያ ብቻ ነኝ። ክፉ ስትሆን በምድር ላይ እጅግ የዘቀጠች እና እጅግ የቆሸሸ ስነ ምግባር የጎደላት ማለት ክፉ ሴት ናት። መልካም ስትሆንም ለሰው ከነፍስ መዳን ቀጥሎ፡ በጎኑ ያለች እጅግ ውድ ድንቅ ነገር ማለት፡ መልካም ሴት ናት። እኔ አሁን የምናገረው፡ ለዚያች ወራዳ፡ ስነ ምግባር ለጎደላት ሴት እናገራለሁ። ከዚህ ሳንወጣ እዚሁ እንዳለን አሳያችኋለሁ፡ ምናልባት ከዚያ በተጨማሪም ይህን አሳያችኋለሁ... መጽሐፍ ቅዱስ ሴቶች ሰባኪ እንዳይሆኑ ያስተምራል፡ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ፓስተር፡ አስተማሪ፡ ወይም ሌላም እንዳይሆኑ ያስተምራል። አሁን፡ ይህን ብቻ ስሙ፡-

**ጌታም... እንዲህ አለ፡ እነሆ፡ ሰው እንደ... እንደ እኛ ሆነ፡** (አሁን፡ ሴቷ እንደ እኛ ሆነች አላለም፡ "ሰውየው አንድ ሆኗል።")... **መልካሙንና ክፉውን** አውቋል።... (ሴትየዋ አላወቀችም፥ ተታላለች። እያችሁት? )

282 አሁን፡ ጳውሎስ እንዲህ አለ፡ “ሴት እንድታስተምር ወይም ሥልጣን እንድትወስድ አልፈቅድም፡ ግን... አዳም አስቀድሞ ተፈጠረ በኋላም ሔዋን ተፈጠረች። አዳምም አልተታለለም፡ ሴቲቱ ግን ተታለለች።” ስለዚህ እንደ እግዚአብሔር አልሆነችም። ተታለለች እንጂ፡ የተለየ ነገር አላወቀችም። ገብቷችኋል? ከገባችሁ፡ “አሜን” በሉ፡” እኔም... [ጉባኤው “አሜን፡” አለ።—አርታዒ።]

> **... እግዚአብሔር አምላክም... አለ፡ እነሆ፡ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ... ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ፥** አሁንም... **እጁን እንዳይዘረጋ፡ ደግሞም፡ ከሕይወት ዛፍ ወስዶ እንዳይበላ፡ ለዘላለምም፡ ሕያው ሆኖ እንዳይኖር፥**
>
> **ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክ... የተገኘባትን መሬት ያርስ ዘንድ፡ ከዔድን ገነት አሰወጣው።**
>
> **አዳምንም አሰወጣው፥ ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውንም መንገድ ለመጠበቅ ኪሩቤልንና፡ በሁሉም በኩል...** የምትገለባበጥ የነበልባል **ሰይፍን በዔድን ገነት ምሥራቅ አስቀመጠ፡** (አራቱን አውሬዎች አያችኋቸው? መሄድ የሚቻልባቸው አራት መንገዶች ብቻ አሉ፡ እነሱም፡ ምሰራቅ፡ ሰሜን፡ ምዕራብ፡ እና ደቡብ። እነዚህ ኪሩቤል በገነት ደጃፍ ላይ የሚንበለበል ሰይፍ ይዘው ነበር... ) **ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወሰደውን መንገድ ለመጠበቅ።**

283 ምክንያቱም የሰው ልጅ የሕይወትን ዛፍ ከያዘ፡ ለዘላለም መኖር ይችላል።

284 እነዚያም ኪሩቤሎች፡ በመጀመሪያ የተገለጹት፡ በኤደን ገነት ደጅ በምስራቅ በኩል ነው፡ በአራቱ አቅጣጫ። እኔ ከዚያ ትንሽ በተለየ ማድረግ ብችል ጥሩ ነበር፥ በእግዚአብሔር ትዕዛዛትና እና በሰራዎቹ ሁሉ ማመቻመች አልችልም፡ ይሁን እንጂ ም—ምን... ለማለት እንደፈለግኩ እንዲገባችሁ ነው። የኤደን ገነት **ይህ ነው**። **እዚህ** ጋር ደግሞ በሩ አለ፡ እንዲህ ወደ ውጭ በመወዛወዝ፡ ይከፈታል፡ በበሩም ዘንድ ኪሩቤሎች ነበሩ። ኪሩቤሎች! እና፡ ያስታውሱ፡ “ኪሩቤሎች” አለ እንጂ፡ “ኪሩቤል” አይልም። ኪሩቤሎች ምንን ለመጠበቅ እዚያ ነበሩ? የሕይወትን ዛፍ። ሊጠብቁት የነበረው ያ ነው፡ ወደ ህይወት ዛፍ የሚወሰደውን መንገድ። መንገድ፡ መንገዱ ማን ነው? [አንድ ወንድም “ኢየሱስ ነው፡” አለ።—አርታዒ።] የሚንፀባረቀው ከየት ነው? ቅድሰት ሰፍራ **ይህች** ናት፡ ኪሩቤሎች **እነዚህ** ናቸው።

285 አሁን፡ ተመልከቱ፡ እነዚህ ሁሉ አንድ ላይ አሰሯቸው። ቅዱስ—ቅዱስ... ይህ ቅድሰተ ቅዱሳን ነው፡ ቅድሰተ ቅዱሳን **እዚህ** ጋር አለ፡ **ይሄኛው** ቅድሰት ሰፍራ ነው፡ **ይሄኛው** ባሕር ነው፡ ብርሃንን የሚያበሩ **እነዚህ** ናቸው፡ **ከዚህ**፡ **ወደዚህ**፡ **ወደዚህ**፡ **ወደዚህ**፡ **ወደዚህ**፡ **ወደዚህ**፡ **ወደዚህ**፡ ብርሃንን የሚያንጸባርቁ ሰባቱ መቅረዞች እነዚህ ናቸው። አያችሁ? የሚያንጸባርቁት ምንድነው? ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወሰደውን መንገድ በእግዚአብሔር እሳት እየጠበቁ እና እያንጸባርቁ ናቸው። አያችሁ፡ **እዚህ** ካሉት ነገሮች፡ ከፕሬሰባይቴሪያን ሰሚናሪ ወይም ከጴንጤቆስጤ ሰሚናሪ አይመጣም፡ ብርሃኑን በማንፀባረቅ፡ **ከዚህ** መምጣት አለበት። በጣም ጥሩ።

286 ልብ በሉ፡ እነዚህ ዮሐንስ እዚህ ጋር ያያቸው ኪሩቤሎች—የሕይወትን ዛፍ የመጠበቅ ፍላጎት ነበራቸው፡ ስለዚህ የሰዎችን ልጆች የሚወዱ ነበሩ። ወይም ዘፍጥረትን እንደገና አንብቡ፡ ወደ ዘፍጥረት መለስ ስንል፡ “የህይወትን ዛፍ ይጠብቁ፡ የሕይወትን መንገድ፡ ይጋርዱ ነበር።” የሕይወት መንገድ! መንገዱ እንዴት ነው? ኢየሱስም፡ “እኔ መንገድ ነኝ። ከእግዚአብሔር ከሰማይ የመጣ እንጀራ እኔ ነኝ። ሰው ይህን እንጀራ ቢበላ፡ ለዘላለም ይኖራል።” አሁን ወደ ሕይወት ዛፍ መመለሻ መንገድ ወጥቷል። ገባችሁ?

287 አሁን፡ እዚህ ጋር፡ ይህን ማሳየት እና ማረጋገጥ እፈልጋለሁ፥ መሠዊያ ነው። ስለዚህ፡ ይህ በኤደን ገነት የነበረ መሠዊያ መሆን አለበት። ለምን እንደሆነ እነግራችኋለሁ። ቃየንና አቤል ሁለቱም የመሰዋዕት አምልኮ ለማድረግ ወደዚህ እንደመጡ ታስታውሳላችሁ? ስለዚህ ይህ የሚያሳየው የአምላክ መሠዊያ ተንቀሳቅሶ እዚህ በኤደን ገነት እንደተቀመጠ፡ እና ወደ ኤደን የሚወስደው ብቸኛው መንገድ በመሠዊያው አጠገብ ነው። አያችሁ፡ እነሆ አሁንም፡ በመሠዊያው በኩል ወደ ኤደን ተመለስን። እነርሱ ግን መሠዊያው፡ በደም እስኪሸፈን ድረስ፡ እነርሱ መጥተው እንዳይገቡባት ይጠብቋት እና ይጋርዷት ነበር።

288 እምላክ ሆይ፡ ይህ ህዝብ አያይምን? አያችሁ፡ በደሙ ብቻ ነው! በዚያ ውስጥ ማስተሰሪያ፡ የምሕረት መክደኛ አስፈለገ፡ ይህ የፍርድ መሥዊያ የምሕረት መክደኛ መሆን አስፈለገው፥ ስለዚህ ከዚህ መሰዊያ፡ ደሙ ከተነሣ፡ በዚያም የፍርድ ቀን የእግዚአብሔር ቁጣ እሳት ያን ዛፍ እንደገና ለመጠበቅ በዚያ ይቆማል። እንደገና ወደዚህ ወደ ኤደን በር የሚገባው በአንድ ነገር ብቻ ነው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም። አይታችኋል?

289 አሁን፡ አስተውሉ፡ አዎን፡ አሁን ቃየን... ይኸው፡ **ይህ** ቃየን ነው፥ አቤልም፡ አቤል **ይህ** ነው። በጣም ጥሩ። አሁን፡ ሁለቱም ወንዶች ልጆች አምልኮን ለማቅረብ ወደዚህ በር ወጡ። ልክ ነው? ስለዚህ የእግዚአብሔር መሠዊያ መሆን አለበት። ልክ ነው? እና ከዚህ መሠዊያ ፊት፡ እሱን ለመተካት ሌላ መሠዊያ ሠሩ። የእግዚአብሔር እውነተኛው መሠዊያ **ይህ** ነው፡ በሰው ልብ ውስጥ ነው። ከዚያም **እዚህ** ጋር ሌላ መሠዊያ አለ፡ እርሱም በቅድስት ሰፍራ ውስጥ ቅድስተ ቅዱሳን የሚወክል ነበር።

290 ኦህ! ኦህ! በልሳን ተናገር ተናገር አለኝ። ኦህ፡ ማይ፡ እጅግ ፍጹም ነው... የእግዚአብሄር ክብር አይታያችሁምን? ልብ በሉ! ኦህ፡ ይህን የተናገርኩበት ምክንያት፡ ሰሜቴን ለመግለጽ በራሴ የእንግሊዝኛ ዘዬ በቂ ቃላት ማግኘት ስለማልችል ነው። አያችሁ፡ የሆነ ነገር መባል አለበት።

291 እንደ ወንድም ሮው፡ የፕሬዝዳንቱ... የአራት ወይም የአምስት የተለያዩ ፕሬዚዳንቶች ዲፕሎማት፡ እንዲህ አለ፡ “ኦህ፡ ወንድም ብራንሃም፡ አንድ ቀን ማታ ወደ ስብሰባው መጣሁ።” እንዲህ አለ፡ “ምን ማድረግ እንደነበረብኝ አላውቅም፡” “በዚያም ቆምኩኝ፡” አለ። እና “ኦህ፡” አለ፡ “ጌታን በዘመኔ ሁሉ እወደዋለሁ፡” አለ። እንዲህ አለ፡ “ድሮ እንዲህ ነበርኩ” “ኤጲስቆጶሳዊ” ነበርኩ (መሰለኝ)። እና “ጌታን የማውቀው ይመስለኛ ነበር፡” አለ። እንዲህ አለ፡ “እና አንድ ቀን ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም ነበርና፡ ዙርያዬን ተመለከትኩ።” “ቶሎ—የሚነካ አይነት ሰው አይደለሁም፡ ግን” አለ፡ “ቃሉ

ሲሰበክ ሰማሁ። ኦህ፡ ወደ ውስጤ መግባት ጀመረ፡" አለ። እንዲህ አለ፡ "ከድንኳኑ በስተውጭ ወደ ላይ እና ወደ ታች ተመላለስኩ፡ ወደ ኋላ እና ወደ ፊት ሄድኩ፡" ከዚያ "ወዲያው ወደ በሩ ቸኮልኩ፡ የመሠዊያውም ጥሪ በተጠራ ጊዜ ከሥር ገባሁ፡ ወደ መሠዊያውም ሮጩ ተደፋሁ፡ 'ጌታ ሆይ፡ እኔ ኃጢአተኛ ሰው ነኝ!' አልኩኝ፡" ያን ጊዜ "በመንፈስ ቅዱሱ ሞላኝ፡" ብሎ መሰከረ።

292 አለም፡ "ሰምንት የተለያዩ ቋንቋዎችን መናገር እችላለሁ፡" ምክንያቱ ዲፕሎማት ስለሆነ ነው። አያችሁ? እርሱም፡ ከውድሮ ዊልሰን... ወደ ታች ያሉትን... የ... የ—እሱ የ—የፕሬዚዳንት ዲፕሎማት ነው። ለእያንዳንዳቸው ፕሪዚዳንቶቻችን፡ የውጭ ዲፕሎማታችን ነው፡ ማንኛውንም የውጭ ቋንቋ መናገር ይችላል። "በአለም ውስጥ የሚታወቁትን ሁሉንም የጽሁፍ ቋንቋዎች በተግባር አውቃለሁ፡" አለ። ይሁን እንጂ፡ "ከክብሩ ብዛት የተነሣ በእነዚህ ቋንቋዎች እርሱን ማመስገን አልተቻለኝም፡ ስለዚህ ጌታ እሱን የማመሰግንበት ከሰማይ አዲስ ቋንቋ-ሰጠኝ።" ኦህ! ኦሃ! ይኸውላችሁ።

293 "መግቢያውን ጋርደውታል።" ቃየን እና አቤልም አምልኮ ለማድረግ ወደዚህ መሰዊያ መጡ። እነዚያ ወደሚጠብቁት መሰዊያ ሳይሆን አይቀርም። ልክ ነው፡ ኪሩቤሎቹ?

294 ሌላው ደግሞ፡ እዚህ ጋር ሌላ ማስረጃ አለ። ቃየን... መጽሐፍ ቅዱሱን አሁን እዩት! ሄዳችሁ ብትከፍቱ በወደድኩ ነበር፡ ይሁን እንጂ... ችግር የለውም፡ በዘፍጥረት ታገኙታላችሁ። መልካም፡ ተከታተሉ። ቃየንም ወጣ፡ ቃየንም በገነት ካለው በር ከእግዚአብሔር ፊት ወጣ። ስለዚህ የጌታ መገኘት በመሠዊያው ላይ ነበር ማለት ነው፡ መሠዊያውም በበሩ አጠገብ ነበር። ክብር ይሁን! ኦህ! መልካም። የእግዚአብሔር ማደሪያ፡ በመሠዊያው ላይ ነው። እንግዲህ፡ ቃየን ከእግዚአብሔር ፊት፡ ከዚህ ቦታ ወጣ። ማስታወሻ መጻፍ ትፈልጋላችሁ? ስለዚህ አሁን፡ መጻፍ ከፈለጋችሁ። አሁን፡ ዘፍጥረት 4፡16 ላይ አለ፡ ሙሉውን ታገኙታላችሁ፡ ጽፋችሁ፡ ይዛችኋል?

295 አሁን፡ ለአንድ ደቂቃ ብቻ እዚህ መሳል የምፈልገው ሌላ ነገር አለኝ። ባቄላችሁ፡ ወይም የሆነ ነገራችሁ እንደማይጎረና ተሰፋ አደርጋለሁ... አሁን፡ ልብ በሉ... ቢፈልግም ይጎርና፡ ምንም ችግር የለውም፡ ጠፊ ነውና። እውነተኛው ነገር—ይህ ስለሆነ፡ አትኩሮታችንን—ወደዚህ—ወደዚህ እናድርግ።

296 ሙሴ ወደ ሰማይ ተወሰደ፡ ሙሴ፡ ከምድር ወደ ሰማይ ተወሰደ እና የእግዚአብሔርን መሠዊያ አየ። ልክ ነው? አሳቤን ለማጠናከር እየሞከርኩ ነው። ለማድረግ የፈለግኩት ነገር አውቃችኋል፡ አይደል? መልካም። ወደ ሰማይ ወደ እግዚአብሔር ፊት ወጣ። በእግዚአብሔር ፊት በቀረበ ጊዜ፡ እግዚአብሔር-... ሙሴን፡ እንዲህ አለው፡ "በሰማይ እንዳየኸው ምስል በምድርም እንዲሁ እንድታደርግ ተጠንቀቅ።" ልክ ነው? መልካም።

297 ከዚያም፡ ያንን በሠራ ጊዜ፡ የቃል ኪዳኑን ታቦት በሠራ ጊዜ፡ ታቦቱን የሚጠብቁ ሁለት ኪሩቤሎችን አደረገ። ምን እንደሆነ አያችሁ? ቤተ መቅደስ... ዙፋኑን የሚጋርደው፡ መሠዊያው ነበር፡ ሁለቱ ኪሩቤሎች፡ "የሁለቱም ክንፎች እርስ በርስ **እንዲህ** እንዲነካካ አድርገህ ከናስ የተሰሩ ይሁኑ፡" አለው፡ ምክንያቱም በገነት ያየው ያ ነው።

298 ዮሐንስ በገነት ያየውም፡ በገነት በዙፋኑ ታቦት በአራቱም ወገን እነዚህ አራቱ ኪሩቤሎች ናቸው። የታቦቱ ጠባቂዎች ነበሩ። ኪሩቤሎች፡ በስርየት መክደኛው ላይ ጠባቂዎች ናቸው።

299 ጥቅሱን ማንበብ ከፈለጋችሁ (ወደሱ ለመግባት ጊዜ የለንም)፡ ዘጸአት 25፡10 እስከ 22 ጸፉ።

300 ስለዚህ፡ እግዚአብሔር በእርያም ክብሩ ውስጥ እያለ የምህረት መክደኛውን የሚጠብቁ ናቸው። የእርያም ክብር የት ነው? በምሕረት መክደኛው ነው። ልክ ነው? የእርያምን ክብር ይጋርዳሉ። እህም! ዋው! ወዳጆች ሆይ፡ ስሙኝ! ይህ የሚያሳየው የማንም እሰስ ገሰስ መጥቶ ከዚያ መካፈል እንደማይችል ያሰረዳል። ወደ ህልውናው ከመድረሳችሁ በፊት መዘጋጀት አለባችሁ።

301 አሮንን፡ በተምሣሌት ተመልከቱት። አስቀድሞ... አሁን፡ ልንገራችሁ፡ በዚያ ዘመን ጉባኤው ወደዚያ መጠጋት እንደማይቻለው አስታውሱ። አሮን ሲገባ ግን... በየሰንት ጊዜ ወደዚያ ይገባል? በአመት አንድ ጊዜ። ምን ምን ያደርጋል... ? በልዩ ሁኔታ፡ በተመረጡ እጆች የተሰራ ልዩ ልብስ፡ መልበስ ይኖርበታል። በተመረጠ መንገድ በልዩ ሁኔታ ይለብሰዋል። "ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅድስና ለእግዚአብሄር፡" እያለ በተንቀሳቀሰ ቁጥር፡ ድምጽ የሚያሰሙ ሮማኖች ነበሩት። ደም ይዞ፡ በምሕረት መክደኛው ፊት ይቀርብ ነበር።

302 ከሳሮን ጽጌረዳ የተሠራ ሽቱ፡ እና የተቀመመ ዘይት ተቀብቶ ይገባ ነበር። ያ የሳሮን ጽጌረዳም ኢየሱስ ነበር። እና፡ ልብ በሉ፡ ጽጌረዳ ቆንጆ ነገር ነው፡ በውስጡም ሽቶ አለው። ሽቶው ከመውጣቱ በፊት ግን፡ ጽጌረዳው መፈጨት ይኖርበታል፡ ከዚያም ሽቶው ከጽጌረዳው ላይ ይጨመቃል። ኢየሱስ፡ በሕይወቱ፡ በምድር ከኖሩ ሁሉ ይልቅ የሚያምር ነበር፡ ቤተ ክርስቲያኑን መቀባት ካለበት ግን፡ እንደዚያው ሆኖ መቅረት የለበትም (ቅድስናው ላይ ለመግባት)፡ ህይወቱ መጨመቅ ነበረበት። በእርሱ የነበረው ያው መንፈስ ቅዱስም በቤተ ክርስቲያን ላይ ወረደ፡ ይህም እርሱ ትናንትናና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘለአለም ድረስ ያው የሆነ፡ የሳሮን ጽጌሬዳ፡ መልካሙ መዓዛ እንዲሆን ያስችለዋል። ወደዚህ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የሚቀርብ ማንኛውም ሰው በተመሳሳይ መንፈስ ቅዱስ መቀባት አለበት። "ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅድስና፡ ለ... " እያለ ሲንቀሳቀስ፡ (አፉ ውስጥ ሲጋራ ሰክቶ አይደለም።) "ቅዱስ!" (ኮሌታው አዙሮ አይደለም።) "ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅዱስ፡" የኢየሱስ ክርስቶስን ቅድስና ለብሶ። እህም! አቤቱ ድንቅ ነህ! ኦህ!

303 አሁን፡ "የምህረት መክደኛ።" የምህረት መክደኛው፡ በልብ ውስጥ ነው፡ ከዚህም ከዙፋኑ ከክብሩ—በሰው ልብ ውስጥ ካለው ከእርያም ክብሩ የሚወጣውን፡ ወደ ልጆቹ ሁሉ ላይ ያንጸባርቃል። የሰው ልብ **እዚህ** አለ። ልክ ነው? የምህረት መክደኛውስ እሱ ነው? በእነዚህ የተለያዩ ሰርዓቶች በኩል ወደዚያ እንዴት ልትገቡ ትችላላችሁ? በራስ-ፈቃድ፡ በራስ-ፈቃድ። **በዚያ** በኩል፡ **ወደዚህ** መምጣት፡ **ምን** ያስገኛል? የእርያም ክብር። የእርያም ክብር—ምንድነው? የእግዚአብሄር ህልውና። ያን ጊዜ ወንዱ ወይም ሴቷ፡ ሲመላለሱ፡ የእርያምን ክብር ያንጸባርቃሉ። ወደ ቁማር ቤቶች አይሄዱም—አይገቡም፡ ወጥተውም የእግዚአብሔርን ቃል አይክዱም። ሰዎች ምንም

ቢናገሩ፡ ልባቸው በአንድ ነገር ላይ የጸና ይሆናል፥ በእግዚአብሔር። በእውነትም በእግዚአብሔር የተጠራ ከሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ በእርያም ክብር ራሱን በሱ ላይ ያንጸባርቃል፡ ያኔ ያደረጋቸውን ተመሳሳይ ስራዎች በእርሱ ደግሞ ያደርጋል፥ ያንኑ ወንጌል ይገልጣል፡ ያንኑ ቃል ይሰብካል፡ ያን ጊዜ ይገለጥ በነበረው ልክ ቃሉ በተማሳሳይ መለኪያ ይገለጣል፡ ልክ በጴንጤቆስጤ ላይ እንደነበረው እንዲሁ ይመለሣል። ኦህ፡ ማይ!

304 “የምህረት መክደኛ።” ሕዝቅኤል እና ዮሐንስ ሁለቱም ተመሳሳይ ነገሮችን አይተዋል። አሁን፡ አስተውሉ፡ አሁን ከአፍታ በኋላ፡ ወደ መጨረሻው ልንደርስ ነው። አሁን፡ የሆነ ነገር እንድታገኙ የምፈልገው እዚህ ጋር ነው። ኦህ፡ እባካችሁ እያምልጣችሁ! አሁን፡ እነዚያ ኪሩቤሎች **ሕያዋን ፍጡራን** እንጂ አውሬዎች እንዳልነበሩ ሰንቶች አውቃችኋል? ከፍተኛ… ስልጣን ነበራቸው።

305 አሁን፡ የመልአክ ሰልጣን ከሰው ይልቃል ወይስ ያንሣል? እሺ፡ ወዳጄ። የቱ ይበልጣል፡ የእግዚአብሔር ልጅ ወይስ መልአክ? የእግዚአብሔር ልጅ ይበልጣል! እግዚአብሔር የትኛውን አብልጦ ይሰማል፡ በፊቱ ቆሞ ስለ አንድ ነገር የሚማጸል መልአክ፡ ወይስ ከእናንተ የሚማጸን አንዱ? ከእናንተ አንዱን ነው! እያችሁ፡ ወንዶች እና ሴቶች ልጆች ስለሆናችሁ ነው። እነርሱ—አገልጋዮች ናቸው። እያችሁ? አገልጋዮች ናቸው፡ እናንተ ግን ወንዶች እና ሴቶች ልጆች ናችሁ። ስለዚህ ምን አይነት ሰልጣን እንዳላችሁ ተመልከቱ፡ ይሄን ለመጠቀም እንፈራለን።

306 አሁን፡ እዚህ ጋር ይህ እጅግ ድንቅ መሆኑ፡ እንድታስተውሉ እፈልጋለሁ። ኦህ፡ ማይ! ወደዚህ መድረስ እንድችል አንዳንድ ነገሮችን ልለፋቸው እና ወደዚህ ልግባ። ብዕራችሁን በደንብ ያዙ፡ እንድትስሉት የምፈልገው ነገር ይህ ነው። [ወንድም ብራንሃም በሰሌዳው ላይ ሳለ—እርታዒ።] ምናልባት አነስ ባደርገው ይሻለኛል። አሁን፡ እስራኤል በጉዞ ላይ በነበሩ ጊዜ፡ አሰፋፈራቸው፡ ይህን በደንብ ተከታተሉ፡ እንዲህ ይሰፍሩ ነበር፥ አንድ፡ ሁለት፡ ሶስት፡ አራት። (አይደለም፡ ተሳስቻለሁ መሰለኝ።) አንድ፡ ሁለት፡ ሶስት፥ አንድ፡ ሁለት፡ ሶስት፥ አንድ፡ ሁለት፡ ሶስት፥ አንድ፡ ሁለት፡ ሶስት፥ በምህረት መክደኛው ዙሪያ አሰፋፈራቸው በዚህ መንገድ ነው። አሁን፡ ሁላችሁም፡ እንደምታውቁት አውቃለሁ፡ ከብሉይ ኪዳን አይታችሁ አንብባችሁታል።

307 አሁን፡ በምስራቅ በኩል፡ ምስራቃዊው ወገን፡ **በዚህ** በኩል ነበረ፡ በደንብ መያዛችሁን ለማረጋገጥ ዝቅ አደርግላችኋለሁ። ምሥራቅ፡ በምሥራቁ በኩል ሁልጊዜ የይሁዳ ወገን ነበር። በሩ ይህ ነው፡ J-u-d-a፡ ይሁዳ ነው። ከይሁዳ ጋርም… ሰንደቃቸውን ይዘው የሶስት ነገድ አለቃ ነበር፡ የይሁዳ ሰንደቅ፡ ሰንደቅ ዓላማቸው የያዙ ሦስት ነገዶች ነበሩ። ታስታውሳላችሁ… **አሰርቱን ትዕዛዛት፡** የሲሴል ዲማይል **አሰርቱ ትዕዛዛት** ሰንቶች አይታችሁታል? በጣም ጥሩ። ወይስ፡ እዚህ በቃሉ ውስጥ አንብባችኋል፡ ማለቴ፡ በዚያ በቅዱስ ቃል ውስጥ፡ በምሥራቅ በኩል ይሁዳ ነበረ። መልካም።

308 **በዚህ**፡ በምዕራብ በኩል፡ (በደንብ ያዙ፡ አንብባችሁታል አይደል… ዘጸአት ውስጥ፡ የነበረ፡ ሲወጡ በነበሩ ጊዜ ነው።) እና ኤፍሬም ነበረ፡ E-p-h። ሰንደቃቸውን የያዙ ሦስት ነገዶች ከእርሱ ጋር ነበሩ። መልካም፡ ኤፍሬም።

309 አሁን፡ በደቡብ በኩል ሮቤል ነበረ፡ R-u-b፡ ከሦስት ነገዶች፡ ከነ ሰንደቃቸው ጋር።

310 በሰሜንም በኩል ዳን ነው፡ ዳንም ሦስት ነገዶች ነበሩት፡ ሦስት ነገዶችና ሰንደቃቸው ይዘው ነበር። በጣም ጥሩ።

311 ስለዚህ፡ አሰፋፈራቸው እንዲህ ነበር። አሁን፡ አስታውሱ፡ ይህንን በትክክል እንድንረዳው ከቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እናንብብ። በሰባተኛው ቁጥር እጀምራለሁ፦

> **ፊተኛውም... አውሬ አንበሳን** ይመስላል፡ **ሁለተኛውም አውሬ... ጥጃን** ይመስላል፡ **(ወይም ወጣት በሬ) ሦስተኛውም አውሬ** እንደ **ሰው ፊት ነበረው፡** አራተኛውም... **አውሬ... አረተኛውም የሚበረውን ንስር** ይመስላል።
>
> **አራቱም አውሬዎች** እያንዳንዳቸው **ስድስት ክንፎች አሉአቸው፥ በዙሪያቸውና በውስጣቸውም ዓይኖች ሞልተውባቸዋል፥ ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅዱስ፡... የነበረውና፡** ያለ፡ የሚመጣውም፡ **ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ እያሉ፡ ቀንና ሌሊት አያርፉም።**
>
> **አውሬዎቹ**ም **በዙፋን ላይ ለተቀመጠው ከዘላለምም እስከ ዘላለም በሕይወት ለሚኖረው ለእርሱ ክብርና ውዳሴ ምስጋናም** በሰጡት **ጊዜ፡**
>
> **ሀያ አራቱ ሽማግሌዎች በዙፋን ላይ በተቀመጠው ፊት** ወድቀው፡ **ከዘላለም እስከ ዘላለም በሕይወት ለሚኖረው** እየሰገዱ፡ **አክሊላቸውን—በዙፋኑ ፊት አክሊላቸውን ያኖራሉ፡ እንዲህ እያሉ፡**
>
> **ጌታችንና አምላካችን ሆይ፡ አንተ ክብር... ውዳሴ... ኃይልም፡ ልትቀበል ይገባሃል፥ ሁሉን ፈጥረሃል**ና፡ **ስለ ፈቃድህም ሆነዋል**ና... **ተፈጥረውማል**ና።

312 አሁን፡ አሁን፡ እዩ። በምስራቅ በኩል—በምስራቅ በኩል፡ ምን አይነት ፊት አየ? ልብ ካላችሁ፡ አንበሳ ነበር፡ l-i-o-n፡ ሰንድቃቸው ይህ ነበር። የይሁዳ ሰንደቅ ዓላማ—ያ ነበር። ምክንያቱም እሱ... ኢየሱስ ከዚያ መጣ... በትክክል! እርሱም የይሁዳ ነገድ አንበሳ ነው።

313 እስኪ፡ ዞድያክን አይታችሁ የምታውቁ ሰንቶች ናችሁ? ብዙዎቻችሁ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ፥ ኮከቡ። አያችሁ? የእግዚአብሔር የመጀመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ ይህ ነበር። አሁን፡ ከዞዲያክ በቅደም ተከተል፡ ቀድሞ የሚመጣው ምስል፡ የቱ ነው? ድንግል ናት! ልክ ነው? በመጨረሻውስ ምንድን ነው? አንበሳው፡ ሊዮ ነው። የክርስቶስ የመጀመሪያ ምጽአት እና ዳግም ምጽአቱ፡ በዚያ ይታያል። ከዚያም የተመሳቀለ ካንሠር የሚሉት አለ... ወይም የተመሳቀለ ዘመን ብለው የሚጠሩት የተመሳቀለው ዓሳ፡ የካንሠር ዘመን ይሉታል፡ እኛም እየኖርንበት እንገኛለን።

314 በሄኖክ ዘመን፡ ፒራሚዱን በሚሰራ ጊዜ፡ እያንድናዷ ድንጋይ በዚያ እንደነበረች አስተውሉ። ነገሮችን በትክክል በመለካት ጦርነቱን እና ነገሮችን መተንበይ ይችላሉ። ከመአዝንን ራስ ድንጋይ በቀር ሁሉም በቦታቸው ነበሩ።

እንዴት? ዶላራችሁ ላይ ያለውን አስተውላችኋል? የመአዘን ራሱን፡ አውጡት እና እዩት። እንዴት? በፍጹም በመአዝን ራስ አልተሸፈነም ነበር። የተጠላ የመአዝን ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ነው፡ የተጠላው የመአዝን ራስ ድንጋይ እርሱ ነበር። በቅርብ ጊዜ ይመጣል። ድሮ በሉተራን ዘመን የነበረችው፡ ቤተክርስትያንን ተመልከቷት፡ ከወደ ሰር አከባቢ ሰፋ ያለች ነበረች፥ ከዚያም እናሳ እየሆነች ሄደች፡ የጴንጤቆስጤው ዘመን ካለፈ በኋላ፡ እስከዚህ ድረስ፡ እጅግ ብሶባት እናሳ ሆነች፡ እና ከላይ የሚቀመጠውን የመአዘን ራስ፡ ከሌሎች ድንጋዮች ጋር መግጠም እስኪችል ድረስ አነሱ፡ እነዚህም ኢየሱስን ትላንትናም፡ ዛሬም፡ እስከ ለዘላለም ያው እንደሆነ የምታሳይ ቤተ ክርስቲያን ናቸው። በተቻለ መጠን በፍጹምነት!

ስለዚህ፡ እርሱ የይሁዳ ነገድ አንበሳ ነበር።

315 አሁን፡ መጽሐፍ ቅዱስን ያነበበ ማንኛውም ሰው የዳን ቁጥር ምን እንደሆነ፡ ወይም ምን እንደሆነ ያውቃል—ዳን ምን ነበር… ኦህ፡ አዎን፡ ይህ ዳን፡ ምን ነበረ ማለቴ ነው? እርሱ፡ ንስር ነበር። በትክክል። ንስር ነበር። መጽሐፍ ቅዱሱን ለሚያነብ። ንስር ነበር።

316 አሁን፡ ሮቤል ደግሞ ሰው ነበር። ይሄኛው የሁሉም በኩር ነበረ፡ ከሌሎቹ ሁሉ ይልቅ ደካማ እርሱ ነበር። ያዕቆብ—በዘፍጥረት 49 ላይ እንዲሁ አላለምን? "ሮቤል፡ አንተ የኃይሌ መጀመሪያ ነህ፥ ነገር ግን እንደ ውኃ፡ በአልጋዬ ላይ ወጣህ አልጋዬንም አረከሰከው፡" ከአባቱም ቁባት ጋር ተኝቷልና። አያችሁ፡ የሰው ልጆች የሰነ ምግባር ጉድለት እነዚህ ናቸው። አያችሁ? እንሰሶች እንዲህ አይነት ሥነ ምግባር የጎደለው የላቸውም፡ እነ አንበሳ፡ እንዲህ አይነቱ ነገር በመካከላቸው የለም፥ ሰው ግን እንዲሁ ነው፡ ከጎረቤት ሚስቱ ጋር ይተኛል። ልክ እንደ… ልክ ተመሳሳይ ነገር ነው፡ ሁሉም ነገር ተፈጽሟል።

317 አሁን፡ ይህ እዚህ ጋር ያለው፡ **ይሄኛው**፡ ማለት ዳን ንስር ነበረ። እና፡ **ይሄኛው**፡ ሮቤል ደግሞ የሰው ፊት ነበረ። ኤፍሬም ደግሞ በሬ። አሁን፡ ምሰሉን ይዛችሁታል? ኤፍሬም… በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ አሰፋፈራቸው በዚህ መንገድ ነበር።

318 እንግዲህ፡ ልብ ብላችሁ ብትመለከቱ፡ ዳን የሦስት ነገድ አለቆች፡ ይሁዳም የሦስት ነገድ አለቃ ነው፡ ሮቤል የሦስት ነገድ አለቃ ነው፡ ኤፍሬምም የሦስት ነገድ አለቃ ነው። ሦስት ጊዜ አራት አሥራ ሁለት ነው፡ አሥራ ሁለት የእስራኤል ነገድ ናቸው። አያችሁ፡ እያንዳንዳቸው ከነሰንደቃቸው፡ የይሁዳ ሰንድቅ አንበሳ፥ የሮቤል ሰንደቅ፡ ሰው፥ የኤፍሬም ሰንደቅ፡ በሬ፡ የ—የ—ዳን ሰንደቅ ንስር ነበር።

319 እንግዲህ፡ ዮሐንስ የተናገረውን መለስ ብላችሁ ተመልከቱ፡ "አንደኛው ፊቱ… " እስኪ አሁን እናንብበውና፡ በሰማያት ጋር ከነበረው ጋር አንድ አይነት ካልሆነ እንየው፦

> … **ፊተኛው አውሬ አንበሳ ይመስላል፡** (ይሁዳ)… **ሁለተኛው አውሬ ጥጃን ይመስላል፡** (ይህም ወጣት በሬ ነው) … **ሦስተኛውም አውሬ** የ**ሰው ፊት** ነበረ**፡ አራተኛውም አውሬ… የሚበር ንስር ነበር።**

320 ልክ የእስራኤል ነገዶች በሰፈሩት ዙርያ፡ ይጋርዱ ነበር፡ በምድር ላይ ወደ ወደ ታቦቱ መግቢያ መንገድ የሚጋርዱ እነርሱ ነበሩ። ኦህ፡ ሃሌሉያ! አይታያችሁም ወይ?

321 እዚህ ጋር! ወደ ምህረት፡ m-e-r-c-y s-e-a-t፡ "የምህረት መክደኛው።" እነዚያን ነገዶች ሳይሻገር ወደዚያ መጠጋት የሚችል ማንም የለም። ምን በመሻገር? አንበሳው፥ ሰውን በመሻገር፡ የሰው አእምሯዊ ብቃት፥ እና የስራ ፈረስ የሆነውን፡ በሬ በመሻገር፥ ወይም ንስርን በመሻገር፡ ፈጣንነቱ። አያችሁ? በሰማይ፡ በምድር፡ በመኃል፡ በዙርያው ሁሉ፡ አያችሁ፡ ጠባቂዎች ነበሩ። ከበላዩም የእሳት ዓምድ ነበረ። ወንድሜ፡ እነርሱን ሳይነካ ወደ ምሕረት መክደኛው የሚጠጋ ማንም የለም...

322 ወደዚያ መቅረብ የሚቻልበት ብቸኛው መንገድ ደግሞ በደሙ ብቻ ነው። አሮን በአመት አንዴ ደም ይዞ ወደዚያ ይገባ ነበር። አሁንስ አያችሁት? አሁን፡ ተከታተሉ። ከእያንዳንዱ ወገን ሦስት ነገዶች የምሕረት መክደኛውን፡ የብሉይ ኪዳንን የምሕረት መክደኛ ይጋርዳሉ። አሁንስ፡ ሁላችሁ፡ ይሄን ገልብጣችኋል? አሁን ደግሞ፡ ወንድሜ ሆይ፡ ለየት-ያለው ነገር እነሆ። ይሄን አድምጡኝ፡ እና እንቀጥላለን። አሁን፡ አስታውሱ፡ ያ የብሉይ ኪዳኑን የሚጋርዱ ናቸው። ከመጽሐፍ ቅዱስ ያነበባችሁ፡ ይህ እውነት እንደሆነ ታውቃላችሁ? አያችሁ፡ የብሉይ ኪዳን ጠባቂዎች ናቸው።

323 አሁን የምንኖረው በሌላ ዘመን ነው። ክብር ይሁን! ኦህ፡ ይህንን ዘመን እወደዋለሁ! እናንተስ? አሁን፡ እግዚአብሔር ዛሬም የሚጋረድ የምሕረት መክደኛ አለው። ይሄን ታምናላችሁ? የምህረት መክደኛው የት ይገኛል? በሰው ልብ ውስጥ። ወደ ሰው ልብ ውስጥ መቼ መጣ? መንፈስ ቅዱስ (እርሱም እግዚአብሔር) ወደ ሰው ልብ በመጣበት በበዓለ ሃምሳ ቀን። ልክ ነው? አሁን፡ ይህን በማስታወሻ እንያዘውና፡ እስኪ ከፈለጋችሁ ይሄኛውም እንሳለው። ጴንጤቆስጤ፡ P-e-n-t፡ ጴንጤቆስጤ እለዋለሁ። ይሄኛው የምሕረት መክደኛ ነው፡ መንፈስ ቅዱስ። እዚህ ጋር አደርገዋለሁ... እንደውም በተሻለ፡ የሚገልጸውን አሳያችኋለሁ፡ እዚህ ጋር "እርግብ" እንሳል... ይህ ማለት ወፍ ነው፡ አያችሁ። በጣም ጥሩ፡ አሁንም እግዚአብሔር የምሕረት መክደኛውን የሚጋርዱ፡ የምሕረት መክደኛው ጠባቂዎች አሉትን? እንግዲህ... አሁን፡ እንዴት በሚያምር መልኩ እንደተሳለ ተመልከቱ።

324 በቀደም ተቀምጬ ሳለሁ ይሄን አየሁት፡ እና ብድግ ብዬ ዘለልኩ እና ወንበሩን ዞርኩ ደጋግሜ ዞርኩ ዞርኩ፡ ዞርኩት፡ "ክብር! ክብር! ክብር! ክብር! ክብር፡" እያልኩ፡ ዞርኩት። ቻርሊ፡ አንዳንድ ጊዜ በጫካ ውስጥ ከምሆነው የባሰ ሆንኩኝ። እህት ኔሊ፡ እንደዛ ባደርግ፡ በፍጥነት ከቤትሽ ታስወጪኛለሽ። ሃህ? ኦህ፡ ድንቅ ጊዜ እንዳሳለፍኩ። አሁን፡ ምን እንደነበረ፡ ጌታም ያደረገውን ተመልከቱ።

325 ስለዚህ፡ ጴንጤቆስጤ፡ ከጴንጤቆስጤ በኋላ፡ (ምን? ) የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የሆነው፡ የሐዋርያት ስራ መጽሐፍ ተጻፈ A-c-t-s። ልክ ነው? መዳንን ለማግኘት የመጀመሪያው ነገር፡ የሐዋርያት ሥራ በምን ይጀምራል? የሐዋርያት ሥራ 2፡38። የመጨረሻው ዙሪያ፡ ይህ ነው። ልክ ነው? "ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ እና በሌሎች ልሳኖች መናገር ጀመሩ። ጴጥሮስም ተነሥቶ

ሰብከት ሰበከላቸው። 'ምን እናድርግ? ወደዚያ እንዴት እንገባለን፡' ጠየቁ? የሐዋርያት ሥራ 2:38፣ 'ንሰሐ ግቡ፡ እያንዳንዳችሁም፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም ተጠመቁ።'"

326 አሁን፡ አስታውሱ፡ እግዚአብሔር ያንን የምሕረት መክደኛውን—የሚጋርዱ ጠባቂዎች አሉት። የሚጋርዱት የምሕረት መክደኛ ምንድነው? መልካም። M-a-t-h፡ በምስራቅ በኩል፡ ማቴዎስ ነው፥ ሉቃስ፡ ሉቃስ፡ ማርቆስ፥ እና ዮሐንስ። ሁሉም አራቱም ወንጌሎቻቸው የሚመጣውን የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ያጸድቃሉ፡ ማየት በፈለጋችሁ ሁሉ ይጋርዱታል።

327 እስኪ አንዱን ብቻ እንውሰድ፡ አንዱን ብቻ፡ ጊዜ የለንም። ሃያ ወይም ከዚያ በላይ ጽፌያለሁ፡ ግን በዚህ ጉዳይ ላይ አንዱን ሰለ መዳን ብቻ እንውሰድ። ለመጸለይ ጊዜ ሊኖረን ይችላል? አይኖረንም፡ አንድ ሰዓት ነው፡ ስለዚህ ሁላችሁም ለታመሙ መጸለይ ካልፈለጋችሁ በስተቀር አይኖረንም ብዬ እገምታለሁ። አሁን፡ በቂ... በቂ ጊዜ አለኝ። አያችሁ? መልካም።

328 አሁን፡ ይህን አስተውሉ! ማቴዎስ፡ ማርቆስ፡ ሉቃስና፡ ዮሐንስ፡ ምንድን ናቸው? የወንጌል፡ የምድር ቁጥር፡ አራት ናቸው። መልካም፡ አስተውሉ።

329 አሁን፣ ማቴዎስ 28:19፣ 28፣ ማለት፡ እናንተ የሥላሴ አማኞች ወንድሞች የምትወስዱበት፡ ይህ ነው፡ 28፡19። መልካም። ማቴዎስ፡ በምዕራፉ፡ በመጨረሻ ክፍል ላይ እንዲህ ይላል፡ "እንግዲህ ሂዱና፡ አሕዛብን ሁሉ፡ በአባት፡ በልጅ፡ በመንፈስ ቅዱስ ሰም እያጠመቃችኋቸው አስተምሩ"፥ እንደገና በዚህ በጴንጤቆስጤ በኩል፡ ጴጥሮስ መጣና "ንሰሐ ግቡ፡ በኢየሱስ ሰም ተጠመቁ" አለ።

330 በዚህ ወስጥ የሆነ ችግር አለ። "ማቴዎስ ሆይ፡ የምስራቅ በር ጠባቂ አንተ ነህን? "

331 በሩ እንዴት ነው? በሩ ምንድን ነው? ኢየሱስ። ኢየሱስም "በሩ ውኃው ነው፡" አለ። ልክ ነው? ፊደል ሲዘረዘር... ፊደሉ እንዴት ይዘረዘራል s-t-r-a-i-t ወይስ s-t-r-a-i-g-h-t? **S-t-r-a-i-t** ማለት "ውሃ፡" "ደጁ ውሃ ነው።" በምን መልኩ ትገባላችሁ? "ንሰሓ ግቡ፡ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስም ሰም ተጠመቁ፡" በሮችን ይከፍትላችኋል። አይ! ዋው!

332 "ኦህ፡ ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ ግን፡ ማቴዎስ 28፡19 እዚህ ጋር አለ።" በትክክል እውነት ነው። "ግን፡ ማቴዎስ ሆይ፡ የምትጋርደው አንተ ነህን? "

"ያለጥርጥር፡ በሙሉ እጋርዳለሁ።"

333 አሁን የማቴዎስ ወንጌል 1፡18 ክፈቱና የሚናገረውን ተመልከቱ፡ ይህን ይጋርድ—ይጋርድ እንደሆነ እዩ። ማቴዎስ 1... 1፡18 ማቴዎስ 28ን እና የሐዋርያት ሥራ 2:38 ከጋረደ እዩ። ይጋርድ እንደሆነ ተመልከቱ!

**የኢየሱስ ክርስቶስም ልደት እንደዚህ ነበረ፡...**

"እዚህ ጋር እግዚአብሔር አብ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡" ለማለት ይሞክራሉ።

**... የኢየሱስ ክርስቶስም ልደት እንዲህ ነበረ፥ እናቱ ማርያም... ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ፡** ሳይገናኙ፡ የ**መንፈስ ቅዱስ ልጅ ፀንሳ ተገኘች።**

ከሁለቱ የትኛው ነው? ይህ ነገር ሁለቱንም አንድ ያደርጋቸዋል!

እና **እንግዲህ... ይህ ሁሉ... ሆነ፡ ማለት... እነሆም፡...**

አሁን **እጮኛዋ ዮሴፍም፡ ጻድቅ ሆኖ፡... በህዝብ ፊት መቀጣጫ ሊያደርጋት** ስላልወደደ፡ እንዲህ **በሰውር ሊተዋት አሰበ።**

**... እነሆ፡ የጌታ መልአክ በሕልም ታየው፡** ወደ እርሱም፡ ወረደ (ታውቃላችሁ።) እንዲህም አለ፡ **የዳዊት ልጅ፡ ዮሴፍ ሆይ፡ እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ፥ ከእርሰዋ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና።** (አያችሁ? )

**ወንድ ልጅም ትወልዳለች፡... ሰሙን ኢየሱስ** ይሉታል፥...

**በነብዩ... የተነገረው፡ ይፈጸም ዘንድ...** ይህ **ሁሉ... እንዲህ ሆነ፡...**

የቱ፡ **ድንግል** ትፀንሳለች... ( ኢሳይያስ 9:6 )... **ድንግል** ትፀንሳለች፡ **ወንድ ልጅም... ትወልዳለች፡ ሰሙንም ማን ይሉታል**... [ጉባኤው "**አማኑኤል፡**" አለ።—እርታዒ።]

334 ጋረደው አይደል? "አባት፡ ልጅ፡ እና መንፈስ ቅዱስ፡" አባት፡ ልጅ፡ እና መንፈስ ቅዱስ፡ እንዲህ ናቸው፦ የአንዱ ሰም መገለጫዎች ናቸው። ስለዚህ ጠባቂው ያን ለመደገፍ በዚያ ይቆማል። ገባችሁ? ኦህ፡ ማይ! አሁን፡ ይህን ሰንቶች ታውቂታላችሁ? እነሆ! የሚጋርድ ነው።

335 አሁን፡ እንግዲህ... ስለ መዳን ሌላ ብዙ ነገር ይዣለሁ፡ እነዚህን ሌሎችን ጻፉ። ይሁን እንጂ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ምናልባት ለአሰር ደቂቃዎች፡ የጸሎት መሰመር የምናደርግ ከሆነ ግን ለጥቂት ደቂቃ ሌላ ነገር እንሞክር። አሁን ጥቂት ጥቅሶች እንውሰድ። የቱ ጋር ነው የጻፍኳቸው? ይኸው። መልካም።

336 አሁን እዚህ ያለው ማቴዎሰ ሰለ መለኮታዊ ፈውሰም ይጋርደው እንደሆነ እንክፈት እና እንይ። ይህን የምትጽፉ ሰዎች፡ ብዕራችሁን እና ነገሮቻችሁን ይዛችኋል? መልካም። ማቴዎሰን እዩት... የሚጋርድ እንደሆነ እዩ። ማቴዎሰ 10፡ 1 እንውሰድ።

337 ዮሐንሰን እንውሰድና እንይ... አንድ ወይም ሁለት ብቻ፡ ከእነዚህ ውስጥ ሁለቱን፡ አንድ ወይም ሁለትን እንውሰድ፡ ዮሐንሰ 14፡12፣ እና 15፡7።

338 በእግዚአብሔር ዙፋን ዙሪያ መለኮታዊ ፈውሰ እየጋረዱ እንደሆነ ተመልከቱ! ማርቆሰ 16፣ ማርቆሰ 11፡21 እና 22።

ሉቃሰ 10፡1 እሰከ 12፣ እና ሉቃሰ 11፡29 እሰከ 31። ጥቂቶቹን እንፈትሻቸው፡ የሚጋርዱ እንደሆነ እንያቸው፡ በኢየሱሰ ሰም የመጠመቅን በር እንደጋረዱ የመለኮታዊ ፈውሰ መብትን የሚጋርዱ እንደሆነ እንይ። በእያንዳንዳቸው ልናየው እንችላለን። ትክክል።

339 አሁን ወደ ኋላ ተመልሰን ማቴዎሰ 10፡1ን እንይ። ሰለዚህ ወደ ኋላ እንመለሰ... ከዛ በኋላ ገፋ ቢል፡ ከአምሰት፡ እሰከ አሰር ደቂቃ ባለው ጊዜ ውስጥ፡ እንደ ጌታ ፈቃድ እንዘጋለን። እሺ፡ ማቴዎሰ 10ን እንግለጥ፡ ማቴዎሰ የሐዋርያትን ሥራ ይጋርድ እንደሆነ እንይ።

340 እግዚአብሔር በቃሉ ዙርያ ጠባቂ የማያኖር ይመስላችኋልን—እንዲህ ታስባላችሁን? በሬው፡ አንበሳው፡ ሰውም፡ ንስሩም አሁን በዚህ ምድር ላይ በእነዚያ በሮች ዘንድ ካልሆኑ ተመልከቱ? አራቱ ወንጌሎች፡ ወንጌሎቹ እነዚህ ናቸው። አያችሁ? እና ልብ በሉ፡ በሄዱበት ሁሉ በቀጥታ ወደፊት ይሄዳሉ። እርስ በእርስ አይቃረኑም፡ እርስ በእርስ ይደጋገፋሉ። አያችሁ? አንደኛው በሰው ብልሃት ይወጣል፥ ሌላኛው በንስር ፍጥነት ይጓዛል፥ አንዱ ፓስተር ነው... አንደኛው እንደ ወንጌላዊ የሚበረው፡ ወንጌላዊ ነው፡ አያችሁ፡ ሌላኛው ፓስተር ነው፥ ሌላኛው ጠንካራ፥ ሌላኛውም አስተዋይ ነው። እዩት፡ በሁሉም አቅጣጫ የተጋረደ ነው፡ እግዚአብሔር የመንፈስ ቅዱስን ወንጌል ይጋርደዋል! እመነው፡ ወንድሜ! መልካም።

341 አሁን ማቴዎስ 10፡1ን እንውሰድ።

> **አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርቱን ወደ እርሱ ጠርቶ፡ ሥልጣንን ሰጣቸው...** (እህም!)
>
> በሠገነቱ ላይ ተሰበሰቡ፡
> ሁሉም ሲጸልዩ በሰሙ፡
> በቅዱስ መንፈስ ተጠመቁ፡
> ኃይልም መጣ ለአገልግሎት፥
> ያን ቀን ያደረገላቸው ለእነርሱ
> በአንተም ዘንድ ያደርገዋል እርሱ፡
> አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

342 ኦህ፡ ለአንድ ደቂቃ ብቻ ህጸኑን አረጋጉልን። አሁን ሰሙ፡ በደንብ ሰሙ፡-

> ... **በርኩሳን መናፍስትም ላይ ሥልጣንን ሰጣቸው፡...**

343 ብዙ ፓስተሮች ርኩሳን መናፍስትን በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ እንዲቆዩ ዝም ይሉአቸዋል፥ የሴቶች አለባበስ፡ ድርጊት፡ የካርታ ጨዋታዎች፡ የቡንኮ ጨዋታዎች፡ ጭፈራዎች፡ የሾርባ እራት፡ ወዘተ... አቤቱ፡ ማረን!

> **... በርኩሳን መናፍስት ላይ፡ እንዲያወጧቸው፡ ሁሉንም አይነት ደዌን እና** በሽታዎችን **ሁሉ እንዲፈውሱ።**

344 እዚያ በሩ ላይ የተቀመጠ ጠባቂ አያችሁት? የተጻፈውን የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ እንዲደግፍ ወንጌሉ ይጋርዳል!

345 አሁን፡ በቅርብ ጊዜ አንድ ታላቅ አስተማሪ፡ እንዲህ አለ፡ አንድ... በጣም... ታላቅ ሰው ነው፡ መልካም ሰው፡ አገኘሁትና፡ እጅ ተጨባበጥን፡ በጣም ጥሩ ወንድም ነው። እና "የሐዋርያት ሰራ ግን ለቤተ ክርስቲያኒቱ የጠርዝ ቅርጽ ነው፡" አለ። አሃ! በሌላ አነጋገር፡ የጠርዝ ቅርጹ **እዚህ** ጋር ነው ማለቱ ነው፡ አያችሁ። በአንጻሩ ግን፡ የሐዋርያት ሰራ እዚህ በውስጥ በኩል ሲሆን፡ እነዚህ ወንጌሎች ደግሞ እሱን ለመጠበቅ እና አንድ ላይ ለማሰር የተሰሩ የጠርዝ ቅርጽ ናቸው። የ—የ—ሰው አእምሮ ማንኛውንም ነገር ማድረግ እንደሚችል ተመከቱ። ስለ እሱ ባይሆን ኖሮ እኔም ተመሳሳይ ነገር አስብ ነበር። አያችሁ?

346 የጠርዙ ቅርጽ፡ ጴንጤቆስጤ የወንጌል የጠርዝ ቅርጽ አልነበረም። አራቱ ወንጌሎች የጴንጤቆስጤ የጠርዝ ቅርጽ ናቸው! ይህ የጠርዝ ቅርጽ ካዘጋጁ በኋላ፡ ያን ጊዜ ጴንጤቆስጤ ወደ ሕልውና መጣ። ልክ ነው? በመጀመሪያ

የተጻፈው የቱ ነው፡ የሐዋርያት ሥራ ወይም የ—ሐዋርያት? ሐዋርያት። ኢየሱስም ሥራውን እየሠራ እና ወደፊት የሚመጣውንም፡ ስለ ማቴዎስ፡ ማርቆስ፡ ሉቃስና፡ ዮሐንስ እየተናገረ ሄደ፡ አራቱ ጠባቂዎች መጥተው ሲፈጸም ያዩትን እየጻፉ፡ በየተራ እንዴት እንደሚሆን፡ ምን እንደሚከሰት፡ በተፈጸመበት መንገድ እየጻፉ ተናገሩ። ከዚያ ሁሉም በአንድ ጊዜ ዙሪያውን በጠርዝ ቅርጽ አሰዋቡት፡ እነሆም ይህ ነው! አሜን! ማቴዎስ፡ ማርቆስ፡ ሉቃስ፡ እና ዮሐንስ፡ የጠርዝ ቅርጽ ናቸው፡ ወይም ዋናውን ቤተመቅደስ፡ ዙፋኑን፡ የጴንጤቆስጤ በረከትን የሚጋርዱ የጥበቃ ስራ ናቸው።

347 ወንድምና፡ እህቶች ሆይ፡ የጴንጤቆስጤ የሐይማኖት ተቋም አይደሉም፡ ከዚያ ነገር እጅግ የራቁ ናቸው፡ ኧሃ-ሃም፡ ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት እጅጉን የራቁ ናቸው። ሉተራኖች ከነበሩበት ይልቅ የራቁ ናቸው። በርግጥ ከሌሎች ይልቅ፡ ሉተራን በተሻለ መንገድ ጠብቀውታል፡ ይህም እውነት ነው። ጂን፡ ይህ በትክክል እውነት ነው፡ ምክንያቱ፡ አሁን፡ ኢየሱስን በሉተራን ቤተ ክርስቲያን ደጅ ቆሞ፡ ለመግባት ሲሞክር፡ አላየሁትም... ምክንያቱ በመጀምሪያም በዚያ የነበረ አይመስለኛም። በጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ግን ነበረ—ይሁን እንጂ እንዲወጣ ተደረገ። ትክክል።

አሁን፡ ማቴዎስ 10፡1።

348 አሁን ወደ ዮሐንስ 14፡12 እንሂድ እና ጴንጤቆስጤ ድንቅ ነገሮች የሚጋርድ መ—መ—መሆኑን እንየው። በዮሐንስ፡ ምእራፍ 14 ከቁጥር 12፣ ኢየሱስ ይናገራል፦

> **እውነት፡ እውነት፡ እላችኋለ፡ በእኔ የሚያምን፡ እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፥ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል፥ እኔ ወደ አብ** እሄዳለሁና፡፡

349 ኑህ፡ ወንድሜ ሆይ፡ ንስሩ የተቀመጠበት፡ ያንን በር ላይ ነው ምክንያቱ የወንጌላዊነት አገልግሎት እርሱ ነው፡ ታውቃላችሁ፡ እንደ ንስር የሚበር ነው። ፍጥነቱ፡ ወደ ትንቢታዊ ምድር መሻገሩ፡ እያችሁ፡ የነበረውንና፡ ያለውንና፡ የሚመጣውን አስቀድሞ አይቶ መናገር ይችላል። እያችሁ? ንስሩን ተመልከቱት፡ ጋርዶ በተቀመጠበት በዚታ ሆኖ፡ "እኔ የማደርገው ስራ!" ይላል፡ እያችሁ።

350 **እነሆ** አንበሳው ይህ ነው፡ አገልጋይ። ያን ሰልጣን የሰጣቸው ኢየሱስ ነው። እርሱም ይጠብቀዋል፡ ሐዋ 2፡38ን ይጠብቃል። አንበሳው፡ በዚያ በኩል ይጠብቃታል።

351 ይህ ደግሞ ከዚህ ንስር ጋር፡ በወንጌል ፍጥነት መጥቶ፡ እንዲህ ይላል፡ "እኔ የማደርገውን እነዚህን ሥራዎች እናንተ ደግሞ ታደርጋላችሁ። ከዚህ የበለጠ ታደርጋላችሁ፡" ይሄን ይዞ በዓለም ሁሉ በረረ! ይህም የጥንዷ ራስ እንደተቀነጠሰባት፡ ደሙንም በመሬት ላይ እየተረጨ፡ እንደተደፋባት እርግብ፡ ለምጻሙን አንጻው፡ "ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅድስና፡ ለእግዚአብሄር፡" ብላ እንደምትጮኸው ነው። አዎን።

352 አሁንም፡ ገና አንድ ይዣለሁ፡ ዮሐንስ 15፡7። በቀጥታ ወደ 15ኛው ምዕራፍ፡ 7ኛ ቁጥር ላይ እንሻገር፦

**በእኔ ብትኖሩ፡** እሁን፡ **ቃሎቼም**… (የሴሚናሪ ቃል አይደለም)… **ቃሎቼ በእናንተ ውስጥ ቢኖሩ፡ የምትሹትን ትጠይቃላ**ችሁ፡ **ይደረግላችሁማል።**

353 ልክ ነው? ስለዚህ ወንጌል እዚህ ውስጥ የተጋረደ ነው። ይህ የጴንጤቆስጤ በረከት በዮሐንስ እና በወንጌሉ የተጋረደ ነው፡ በማቴዎስ፡ በወንጌሉ የተጋረደ ነው።

354 አሁን፡ ወደ ቀጣዩ ወንጌል፡ ወደ ማርቆስ፡ ምዕራፍ 16 እንለፍ፡ ማርቆስም ይህን የጴንጤቆስጤ በረከት መጋረዱን እንይ። ማርቆስ፡ ምዕራፍ 16። አሁን፡ እዚህ እንጀምር… ከትንሣኤ በኋላ… ይናገራል። አሁን፡ ነጥቡን እስክናገኘው ድረስ ወደ ታች—ወደ ማርቆስ ወንጌል 16 እስከ 14ኛው ቁጥር እናንብብ፦

**በማዕድ ተቀምጠው ሳሉ ለአሥራ አንዱ ከተገለጠላቸው** በኋላ፡ **በአለማመናቸውና በልባቸውም ጥንካሬ ገሠጻቸው፡ ይህም ከሞት ከተነሣ በኋላ ያዩትን ሰላላመኑ ነው።**

355 እነዚያ መልእክቱን ሲነግራቸው የኖሩትም አላመኑም። እያችሁ፡ ዛሬም ያው ነው። የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት ተቀብለው የነበሩ፡ በሕዝብም "እርባናቢሶች፡ የማይረቡ ወንበር-ሰባሪዎ፡" ተብለው የነበሩ። ሰለ ልባቸው ጥንካሬ እና፡ እያችሁ፡ ሰለ አለማመናቸውም ገሠጻቸው፥ በትንሣኤው እርሱን አለማወቃቸው።

**ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፡ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ሰበኩ፡ አላቸው።**

356 ምኑ? ይህ አንዱ… እና… ብቸኛ የሆነ ወንጌል፥ አራት ጠባቂዎች የሆነው። "ይህንን ወንጌል ለፍጥረት ሁሉ ሰበኩ!" አሁን፡ ለሁሉም፡ ማለት ለአራቱም ጠባቂዎች እንደተናገራቸው አትርሱ፡ (ማቴዎስ፡ ማርቆስ፡ ሉቃስ፡ እና ዮሐንስ)፡ እያችሁ፡ "ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ሰበኩ!"

**ያመነ የተጠመቀም ይድናል፡ ያላመነም ይፈረድበታል።** (እያችሁ፡ ወደዚህ ጥምቀት መጠመቅ አለባችሁ።)

**ያመነ የተጠመቀም ይድናል፡… ያላመነ ይፈረድበታል።** (ኧረ፡ ወንድሜ ሆይ፡ እባክህ፡ እመን!)

**ም**… (የተቀሩትን ዓረፍተ ነገሮች አንድ ላይ የሚያጣምር፡ መሰተጻምር ነው።)… **ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፡…**

357 እሺ፡ አሁን፡ እንመልከት፡ ሜቶዲስቶች ምን ይላሉ? "ከጮህክ፡ ጥሩ ህይወት ትኖራለህ።" ባፕቲስቶችም "ብቻ እመኑ እና ተጠመቁ፡" ይላሉ። ኤጲስ ቆጶስያንም "እንደ ኤጲስ ቆጶስያን ቁሙ፡ ቅዳሴው ሲጀመር፡ እንዲህ ጎንበስ በሉ፡" ይላሉ። ካቶሊኮችም "ሰላም ለኪ፡ ማርያም በሉ፡" ይላሉ። ጴንጤቆስጤዎችም፡ "ወደ ተቋማችን ተቀላቀሉ። 'በአባት፡ በልጅ፡ እና መንፈስ ቅዱስ' ስም ተጠመቁ ይላሉ።" ይኸውላችሁ እንግዲህ። እያችሁ?

**… ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፡ በሰሜ**… (እህም። በዚህ ጉዳይ ላይ "አባት፡ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ"

አይሰራም።)... **በሰሜ አጋንንትን** ያወጣሉ፥ **በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፥**

**እባቦችን ይይዛሉ፥... የሚገድልም ነገር ቢጠጡ፡ አይጎዳቸውም፥** እጃቸውን **በድውዮች ላይ ይጭናሉ፡ እነርሱም ይድናሉ።** (አሜን! ኦህ፡ ወንድሜ!)

358 አሁን ወደ 11ኛው እንመለስ፡ እና ከዚያ ለመዝጋት እንዘጋጃለን። ማቴዎስ 11፡ እና ኢየሱስ የሚናገርበት፡ 20 እና 21ም ይዣለሁ። እነዚህ ሁሉ ኢየሱስ የተናገራቸው ናቸው፡ እንግዲህ፡ እያንዳንዳቸው፡ እርሱ ብቻ የተናገራቸው ናቸው።

**እና በማግስቱ፡ ሁሉም... ወደ ቢታንያ** በቀረቡ ጊዜ፡ **ተራበ፥**

**እና የበለሰን ዛፍ አይቶ...**

359 ማቴዎስ 21 ነው፡ ይቅርታ አርጉልኝ፡ የያዝኩት ፡12ን ነው። ዛፏን የረገማት ያኔ ነው፡ ማርቆስ 11፡21 እና 22፥

**ጴጥሮስም ትዝ ብሎት፡ መምህር ሆይ፡ እነሆ፡** በመንገድ ላይ **የረገምሃት በለስ ደርቃለች አለው...**

**ኢየሱስም** መልሶ እንዲህ አለው፡ **በእግዚአብሔር እመን።** (አያችሁ? )

**እውነት እላችኋለሁ፡** (ስለዚህ፡ ውስጣዊ ነው)... **እላችኋለሁ፡ ማንም ያለው ነገር እንዲደረግለት ቢያምን፡ በልቡ ሳይጠራጠር፡ ይህን ተራራ፡ ተነቅለህ ወደ ባሕር ተወርወር ቢል ይሆንለታል፡ ነገር ግን... ማንም ያለው ነገር እንዲደረግለት ቢያምን፡** ይሆንለታል... **የተናገረው ሁሉ ይሆንለታል።**

360 ወዳጄ፡ የደቡብ በርም በበሬ የተጋረደ ነው። የሰሜኑ በር በአንበሳ፡ ሰሜናዊው በር የሚጠበቀው... የምስራቁ በር ማለቴ ነው። የሰሜኑ ደጅም በበራሪው ንስር፡ በዮሐንስ፡ ወንጌላዊው ነው። ከዚያም **በዚህ** በኩል ያለው ሐኪሙ፡ ሉቃስ፡ ሰው ነው።

361 አሁን፣ ሉቃስ ምን እንደሚል እንመልከት። ሉቃስ፡ 1ኛው ምዕራፍ እንውሰድ-... ሉቃስ 10፡1 እስከ 12 ደርስ፡ ተልዕኮው—ይመስለኛል። ምን እንደሆነ ሁላችሁም ታውቃላችሁ፡ እሺ... ሉቃስ፡ 10ኛው ምዕራፍ፡ ከ1 እስከ 12። በጣም ጥሩ፡ ከዚያም አልፈንም ማንበብ እንችላለን፡ ይህን ለማድረግ ግን ጊዜ አይኖረንም። "ሂዱ... " ከ3ኛው ቁጥር እጀምራለሁ፡-

**ሂዱ፥ እነሆ፡ እኔ እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ።**

**ቦርሳ ወይም፡ ከረጢት አትያዙ...**

362 አያችሁ፡ "በአንድ የሐይማኖት ተቋም ስም አትሂዱ። እኔ እንደላኳችሁ ሂዱ።" አያችሁ? "በዚህ ሪቫይቫል አንድ መቶ ሺህ ዶላር አገኛለሁ የሚል ዋስትና ይዛችሁ አትውጡ፥ ካልሆነ፡ አልሄድም በሚል አትሂዱ። አያችሁ። ካምፔይኖችን ለማድረግ። "ወደምልካችሁ ሁሉ ሂዱ፡" አላቸው። አያችሁ።

**ሻንጣ ወይም፡ ከረጢት፡ ወይም ጫማ አትያዙ፥... በመንገድ ላይ ማንም ሰው ሰላም አትበሉ።**

363 “ቆማችሁም ‘እነዚህን እያለሁ... ምን እንደሚያደርጉ ልመልከት... እነዚህሰ... ’ አትበሉ፡ እኔ ወደምልካችሁ ሁሉ ሂዱ። ስለ ሌላ ነገር ግድ አትሰጡ።”

ወደ**ምትገቡበት ቤት ሁሉ፡ አስቀድማ**ችሁ፡... **ሰላም** ለዚህ **ቤት ይሁን በሉ።**

**... በዚያም የሰላም ልጅ ቢኖር፥ ሰላማችሁ ያድርበታል... አለዚያም** ይመለስላችኋል፥ **አለዚያ፡** ይመለስላችኋል።

**በዚያም** ጊዜ **ተቀመጡ፡ በዚያም ቤት** (ማለቴ ነው) **ከእነርሱ ዘንድ ካለው እየበላችሁና፡ እየጠጣችሁ ተቀመጡ፥** (እንግዲህ፡ እነዚያ ወሬዎች ሁሉ፡ “ስጋ እና ሌላ ነገሮች፡ ስለ አለመብላት።” አቤት፡ ጌታ ሆይ! አያችሁ?) **ለሠራተኛ ደመወዙ ይገባዋልና። ከቤት ወደ ቤት አትተላለፉ።**

364 ዛሬ እነ ጆንስ ጋር፡ እራት በልተህ፡ በነጋታው ደግሞ—ወደ ሌሎች ጥንዶች፡ ቀጣይ ጥንዶች ዘንድ በሚቀጥለው። “በዚያው ቆዩ!”

እኔ ወደ ጉባኤው በሄድኩ ቁጥር፡ እንደምታውቁት፡ ሆቴል ላይ አርፋለሁ፡ በዚያም እቆያለሁ፡ ሰላም የማገኛበት ቦታ ያ ነው። አያችሁ? ከቤት ወደ ቤት አትሂዱ!

ወደ**ምትገቡባትም ከተማ ሁሉ፡** በዚያም **ቢቀበሉአችሁ፡ ያቀረቡላች**ሁን **ብሉ፥**

**በእርሰዋም ያሉትን—ድውዮችን ፈውሱና፡ የእግዚአብሔር መንግሥት**... ወደ **እናንተ ቀረበች፡ በሉአቸው።**

365 አሁን ግን፡ መልካም፡ ቀጣዩን ጥቅሰ ላንብብ፦

**ነገር ግን ወደምትገቡባት ከተማ** ሁሉ፡ **ባይቀበሉአችሁ፡** ያን ቀን፡... **ወደ...** ከተማዋ **ወጥታችሁ...**

ወደ **ከተማዋ ዋና አደባባይ፡ በ—በእኛ ላይ** የተጣበቀብንን ምን... (እስኪ እንየው።)... **ምኑ...** ከ... **ከተማችሁ፡** የተጣበቀብንን **ትቢያ እንኳን፡ እናራግፍላችኋለን፥ የእግዚአብሔር መንግሥት ግን ወደ እናንተ እንደ ቀረበች፡ ይህን እወቁ በሉ።**

**እላችኋለሁ፡ በዚያን ቀን** ማለት በፍርድ ቀን **ከዚያች ከተማ ይልቅ፡ ለሰዶም ይቀልላታል።**

366 ኦህ፡ አንተ የተባረከውን ደህንነት የያዝከው፡ ወንድሜ ሆይ! ካላዩት፡ ካልተቀበሉህ፡ መንገድህን ቀጥል፡ እንዲህም በል፡ “እሺ፡ ካልፈለጋችሁኝ፡ አቧራውን፡ ከእግሬ አራግፌ፡ እቀጥላለሁ።” በሌላ አነጋገር፡ እንዲህ በል፡ “እኔ ምንም አልወሰድኩባችሁም፥ ምንም በልቼ እንደሆነ፡ እነሆ እከፍላለሁ፡ ብለህ ቀጥል።” “እውነት እላችኋለሁ... ” እንዳለም፡ እነርሱ ገብተውባቸው ያልተቀበሏቸው ከተሞች ሁሉ፡ ዛሬ የሉም ሁሉም ሰጥመዋልና። እነርሱን

የተቀበሉ—ከተሞች ሁሉ ግን፡ እነሆ እስከ ዛሬ ድረስ ጸንተው ኖረዋል። ይኸውላችሁ።

367 አሁን፡ አንድ ተጨማሪ፡ ከዚያ እንዘጋለን። እስኪ፡ 10ን አይተነዋል። 11፡29 እስከ 31፣ ሉቃስ 11፡29 እስከ 31፣ ከዚያ እንዘጋለን። ኦህ፡ ይሄ ደስ ይለኛል!

> **ብዙ ሕዝብም** በተሰበሰቡ **ጊዜ...**

368 ልክ ነኝ፡ እስቲ እንየው... ሉቃስ፡ ሉቃስ 11፡29 ነው? አዎን፡ እንደሚሆን እገምታለሁ። አዎን፥

> **ብዙ ሕዝብም በተሰበሰቡ ጊዜ፡ እንዲህ ይል ጀመር። ይህ ትውልድ ክፉ ነው፥ ምልክት** ይፈልጋል፥ **ከነቢዩም** ከዮናስ... **ምልክት በቀር፡ ምልክት... አይ... አይሰጠውም።**
>
> ዮናስ ለነነዌ **ሰዎች ምልክት እንደ ሆናቸው፡ እንዲሁ... ደግሞ የሰው ልጅ ለዚህ ትውልድ ምልክት ይሆናል።**
>
> **ንግሥተ አዜብ በፍርድ... ከዚህ ትውልድ ሰዎች ጋር... ተነሥታ፡** ትፈርድባቸዋለች፥ **የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ከምድር ዳር መጥታለችና፥ እነሆም፡ ከሰሎሞን የሚበልጥ፡ ከዚህ አለ።**
>
> **የነነዌ ሰዎች በፍርድ ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥተው፡ ይ... ይፈርዱበታል: በዮናስ ሰብከት ንሰሐ** ገብተዋልና፥ **እነሆም፡ ከዮናስ የሚበልጥ፡ ከዚህ አለ።**

369 አሁን ምን እያልኩ ነው? መዝጊያ ላይ፡ ሌላውን ሁሉ እተወዋለሁ። በመዝጊያ ላይ፡ ግን፡ እጅግ አቆይቻችኋለሁና እንዲህ እላለሁ። እዚህ ጋር ምን እያለን ነው? "ክፉ፡ እና አመንዝራ ትውልድ የሚሆንበት ቀን ይመጣል፡" (አሁን አስታውሱ!) "ምልክት ይፈልጋል። ይህም ክፉና አመንዝራ ትውልድ ነው።" እርሱ "ያ ትውልድ እነሆ ምልክትን ይቀበላል፡" አለ። ከሌላው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፡ ማለትም ከዮናስ ምልክት ጋር እንዴት እንደሚመሳሰል ተመልከቱ። "ዮናስ በዓሣ አንበሪ ሆድ ውስጥ ሦስት ቀንና ሌሊት ነበረ፥ እንዲሁም የሰው ልጅ ደግሞ በ—በምድር ሆድ ውስጥ ሦስት ቀንና ሌሊት ይሆናል።" ምን ይደረጋል? የትንሳኤው ምልክት። አያችሁ? የትንሣኤው ምልክት በክፉና አመንዝራ ትውልድ ዘንድ ይደረጋል፡ በሐዋርያት ሥራም ተጽፎአል። ኢየሱስ ከሙታን ተነሳ፡ ወደ ጴጥሮስና፡ ያዕቆብ፡ ወደ ዮሐንስ፡ ወደ ሐዋርያትም መጣ፡ ይህን የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ አደረጉ (ይህም የሐዋርያት ሥራ አልነበረም)፡ በሐዋርያት **ውስጥ** የሚሠራው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እንጂ።

370 ዛሬም ስራውን የሚሰራው መንፈስ ቅዱስ፡ በሰው፡ ወይም በሰዎች በኩል የሚሰራው ስራ እንጂ፡ አያችሁ፡ ሰው አይደለም። ሰውዬው አይደለም፡ ሰውዬው ዕቃ ብቻ ነው፡ አያችሁ፡ መንፈስ ቅዱስ ግን በዚያ ዕቃ ውስጥ ያለው ዘይት ነው። አያችሁ?

371 እና ያደረጉትን ተመልከቱ፡ በኢየሱስ ያደረጉትን ምልክቶችን ተመልከቱ። ጴጥሮስና ዮሐንስ፡ ዕውቀት የሌላቸው፡ ያልተማሩ ሰ—ሰለ—ነበሩ፡ ትኩረታቸውን ሰበው ነበር፡ ከኢየሱስ ጋር እንደነበሩ ግን፡ አስተዋሉ! እርሱ ያደረጋቸውን ነገሮች አደረጉ። ስለዚህ፡ አያችሁ፡ የመጽሐፍ ቅዱስ፡ እያንዳንዱ

መጽሀፍ... አራቱ መጻሕፍቶች፡ አራቱ ወንጌሎች የጴንጤቆስጤ በረከትን በሁሉም ቅዱሳት መጻህፍት በተናገሩት መንገድ ይጋርዱታል። አሁን ደግሞ የሐዋርያት ሥራ ዛሬ በአራቱ ወንጌሎች ይረጋገጣል ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትናም፡ ዛሬም፡ እስከ ለዘለአለምም ያው እንደሆነ ነው። ትወዱታላችሁ?

በሠገነቱ ላይ ተሰብሰበው፡
ሁሉም ሲጸልዩ በሰሙ፡
በቅዱስ መንፈስ ተጠመቁ፡
ኃይልም መጣ ለአገልግሎት፥
ያን ቀን ያደረገላቸው ለእነርሱ
በአንተም ዘንድ ያደርገዋል እርሱ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

372 እስቲ ልዘምረው፡-

በሠገነቱ ላይ ተሰብሰበው፡
ሁሉም ሲጸልዩ በሰሙ፡
በቅዱስ መንፈስ ተጠመቁ፡
ኃይልም መጣ ለአገልግሎት፥ (ዛሬ የምንፈልገው ያ ነው።)
ያን ቀን ያደረገላቸው ለእነርሱ
በአንተም ዘንድ ያደርገዋል እርሱ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

እነዚህ ሰዎች ባይማሩም፡ (ልክ... እንደ ጴጥሮስ፡ ያዕቆብ፡
እና ዮሐንስ።)
ወይ በዓለማዊ ዝና ባይመኩም፡
ሁሉም ጲንጤቆስጤን ተቀብለዋል፡
በኢየሱስ ስም ተጠመቀው፡
አሁንም በቅርብ በሩቅም ላሉ፡ ያበሰራሉ፡
ህኃይሉ አሁንም ያው ነው እያሉ፡ (ልክ እንደ ድሮው ነው።)
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

አንዱ ነኝ፡ እኔም አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ፥
አንዱ ነኝ፡ እኔም አንዱ ነኝ፡
ኦህ፡ አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

ወንድሞች ሆይ፡ ኑ፡ ይህን በረከት፡ ፈልጉ
ልባችሁን ከኃጢአት ያነጻል፡
የደስታ-ደወሎች ያሰማል
ነፍሳችሁን ያነቃቃል፥
እነሆ፡ በልቤ ውስጥ ይነዳል፡
ኦህ፡ ክብር ለሰሙ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ፥ (ሃለሉያ!)
አንዱ ነኝ፡ እኔም አንዱ ነኝ፡

እንዴ ነኝ፡ እንዴ ነኝ፡

373 [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—እርታዒ።] ብዙ ሰዎችን ያስታል። እ... በየጎዳናው ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሄዱበት ብዙ ሰዎች፡ የአብያተ ክርስቲያናት ናቸው፡ ሄዋን ያኔ በመጀመሪያ እንደተታለለች የተታለሉ ናቸው። የተለየ ነገር አያውቁም።

374 ኦህ፡ ኑና የሕይወትን ዛፍ ተቀበሉ! አሁን፡ በኪሩቤል ፈንታ... አሁን አንድ ነገር ማለት እፈልጋለሁ። ኪሩቤሎች ይህን ዙፋን በመጋረድ ፈንታ፡ አሁን ሰዎችን እያደኑ፡ ወደ ዙፋኑ ለመጋረድ፡ በበሩ በኩል ሊያመጧቸው፡ ፍለጋ ወጥተዋል፡ ይህን ይወሰዱ ዘንድ ወደ ሕይወት ዛፍ ተመልሰዋል። ኢየሱስም፡ "እኔ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚመጣው የሕይወት እንጀራ ነኝ። ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።" ትክክል ነው። ኦህ፡ በጣም ደስ ብሎኛል!

375 በክፍሉ ውስጥ ስንት የታመማችሁ አላችሁ? እጃችሁን እንይ፡ እጃችሁን እንነሡ። መልካም። ካርድ የያዛችሁ ካላችሁ... እንዲህ ነው... ልክ—ልክ ነኝ ቢሊ? የት አለ? የጸሎት ካርዶች ሰጠ? ሰጥተሃል... ? [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—እርታዒ።] እሺ፡ የያዘ ማን ነው... [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ።]

376 አሁን፡ ሁላችሁ፡ ወደዚህ ተመልከቱ። አሁን፡ ይህ ማለት በክብር ታጅቦ ሲመጣ እንደማለት ነው፡ እያችሁ። እያችሁ? እያችሁ? የሚመጣው... ይህ ከላይ ያለው ብርሃን ነው። እየተንቀሳቀሳችሁ ነው፡ እያችሁ። አሁን፡ ተመልከቱ፡ ይህ—ይህ ነገር ነጸብራቅ፡ ነጸብራቅ፡ ብቻ ነው፡ እያችሁ። ብርሃን አይደለም። እነሆ ብርሃኑ እዚህ ጋር አብርቷል፡ እያችሁ፡ እዚህች ሴት ላይ አለ። ድንገት ገባሁና አየሁት እና በአንድ ሰው ላይ ነው ብዬ አሰቤ ነበር።

377 አሁን፡ እናንተ የምታዩት አንደኛውን ብቻ ሲሆን እኔ ግን ሁለቱንም አያቸዋለሁ። አንደኛው ተፈጥሮአዊው ነው፡ ሌላኛው ግን መለኮታዊው ነው። በዚህ ከውጭ በኩል የተቀመጠ ሰው አለ፡ በዚህ መሰመር በኩል ሆኖ ወደዚያ ብርሃን እያየ ነው። እሱ ላይ አብርቷል። ከሴይሞር፡ ኢንዲያና ነው፡ ችግሩ... ስትሮክ ነው። ወዳጄ፡ ካመንክ፡ እግዚአብሔር ከዚያ ስትሮክ ይፈውስሃል። አሜን! አሁን እመን!

378 በሙሉ ልብሽ ታምኛለሽ? ታዲያ የሰማይና የምድር ፈጣሪ የሆነው፡ ጌታ እግዚአብሔር መሆኑን ሊያረጋግጥልሽ፡ አንድ ነገር ላደርግልሽ ቢፈቅድልኝ፡ በፍጹም ልብሽ ታምኛለሽ? ችግርሽ—መውለጃ ጊዜ ከማለፍ ጋር ተያይዞ የመጣ—የ—ጭንቀት ችግር ነው። እግዚአብሔር እንደሚፈውስሽ ታምኛለሽ? አንቺም ከዚህ አይደለሽም።

379 [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—እርታዒ።]... ችግርህ ምንድን ነው? እና፡ እንዲህ በማድረግ፡ እንዲያድንሽ? [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ።] ... ? ... ይድናል፡ ምክንያቱም ፈውሱን የፈለግሽው ለአንቺ አይደለም፡ ለልጅሽ ነው። አየሽ? በቨርጂኒያ ይገኛል። በእግዚአብሔር እርዳታ፡ ምን ችግር እንዳለበት ልነግርሽ እንደምችል ታምኛለሽ? አልሰር አለበት። በትክክል። ሌላም ችግር አለበት፡ አልዳነም። አንቺም እየጸለይሽለት ነው። ስለዚህ፡ ወ.ሮ ቤከር፡ በሙሉ ልብሽ እያመንሽ፡ ወደ ሱመርሴት ተመለሺ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ይፈውሰዋል። [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ።]... ? ... እርሱ ይፈውስሃል፡ እርሱን ፈዋሽህ አድርገህ ትቀበለዋለህ?

ከቻልክ... [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ።]... ፈዋሽ። ጳውሎስ አንድ ጊዜ ተናግሯል... [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ።]

380 በቀኑ እስከዚህ ድረስ በትኩረት ያዳመጠ ይህ የህዝብ ጉባኤ፡ ጌታ ሆይ፡ አሁንም፡ ጌታ አምላክ ሆይ፡ ምሕረትህና ቸርነትህ ያድርባቸው ዘንድ እጸልያለሁ።

381 ሰይጣን ሆይ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እቃወምሃለሁ፡ ከእነዚህ ሰዎች ውጣ! ወንጌልን ሲያዳምጡ ቆይቷል። ከአሁን በኋላ እነሱን መያዝ አትችልም። እነዚህን ሰዎች ያሰረ የሰይጣን ሃይል፡ ይጥፋ!

61-0108 ራዕይ፡ ምዕራፍ አራት ክፍል 3
ብራንሃም ተበርናክል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org